አዲስ አድማስ

**በሊቢያ በአሸባሪው ቡድን በተገደሉት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለፅን ለቤተሰቦቻቸውና ለመላው ኢትዮጵያውያን መፅናናትን እንመኛለን!**

**የሰው ልጅ አውሬነትና የሰው ልጅ ቅዱስነት በሊቢያ!**

ገፅ 11

ቅፅ 15 ቁጥር 797 | ቅዳሜ ሚያዝያ 17 ቀን 2007 ዓ.ም | ብር 8.00


# የኢትዮጵያውያን ሃዘን እጥፍ ድርብ ሆኗል

ኤልሳቤት ዕቁባይ

በደቡብ አፍሪካ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ በደረሰው ዘረኛ ጥቃት ማግስት፣ በሊቢያ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ላይ የተፈፀመው የአሸባሪ ቡድኑ አይኤስአይኤስ ዘግናኝ ግድያ፤ የኢትዮጵያውያንን ሐዘንና ቁጭት መራር አድርጎታል፡፡ እስካሁን የዘጠኙ ሟቾች ማንነት የታወቀ ሲሆን ቤተሰቦች መርዶ ተነግሯቸው፣ ለቅሶ መቀመጣቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ወላጆችና ቤተሰብ፣ ወንድምና እህት፣ ጎረቤትና ወዳጆች ሁሉ ውስጥን በሚያደማ ቅፅበታዊ ሐዘን ተመተዋል።

በሊቢያ የአሸባሪው ቡድን 'አይኤስአይኤስ' ታጣቂዎች '30 ኢትዮጵያዊያን ክርስትያኖችን ገድለናል' ብለው አሰቃቂ የግድያ ቪዲዮና ፎቶ ማሰራጨታቸውን ተከትሎ፣ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች መርዶ ሲደርሳቸው ነው የሰነበቱት። እስካሁን በደረሰን መረጃ፤ በሊቢያ ከተገደሉት ውስጥ 5ቱ የጨርቆስ ወጣቶች ሲሆኑ ከትግራይ አንድ፣ከወለጋ ሁለት እንዲሁም ከሐረርጌ አንድ ኢትዮጵያውያን መገደላቸው ታውቋል፡፡ ከወለጋ የመንግስቱ ጋሼና የአወቀ ገመቹን እንዲሁም ከሐረርጌ "ከክርስቲያን ወገኖቼ አልለይም" በማለቱ አብሯቸው ተገድሏል የተባለውን የጀማል ራህማን ቤተሰቦች ለማግኘት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡፡

ባለፈው ሰኞ የጓደኛሞቹ ኢያሱ ይኩኖአምላክ


አቶ ተጫኔ ዘለቀ - የኤልያስ አባት

እና ባልቻ በለጠ መርዶ የተነገረ ሲሆን በቀጣዮቹ ቀናት የሌሎች ሦስት ወጣቶች መርዶ ለየቤተሰቦቻቸው ተነግሯል፡፡ ሟቾቹ ኤልያስ ተጫኔ፣ ብሩክ ካሣና በቀለ ታጠቁ ናቸው፡፡ በሰላሳዎቹ ዕድሜ ላይ የነበሩት ኢያሱና ባልቻ፤ጨርቆስ ውስጥ ያደጉ ጎረቤታሞች ሲሆኑ ከሁለት ወራት በፊት በሊቢያ አድርገው ወደ አውሮፓ ለመሻገር ወጥነው ነበር ጉዞ የጀመሩት፡፡ ነገር ግን በሊቢያ አሸባሪ ቡድን 'አይኤስአይኤስ' በግፍ ተገደሉ፡፡

**በሊቢያ ከተገደሉት ውስጥ 5ቱ የጨርቆስ ወጣቶች ናቸው**

**ልጆቻቸው ሊቢያ የሄዱባቸው ወላጆች በጭንቀት ተወጥረዋል**


ወ/ሮ አኸዛ ካህሳይ - የእያሱ እናት


እያሱ እና ባልቻ

አቶ ካሳ አግና የ24 አመቱ ወጣት ብሩክ ካሳ አባት ናቸው፡፡ ልጃቸው ከቤት ከወጣ ሶስት ወር እንደሞላው ይናገራሉ፡፡ "ተግባረእድ መማር ጀምሮ ነበር፤ሆኖም ስድስት ወር ሳይሞላው ተወውና ከኔ ጋር ሱቅ መስራት ጀመረ፡፡ አንድ ቀን ሱቅ ሲሰራ ውሎ ማታ የዘጋበትን ቁልፍ እንኳን ሳይሰጠን ጠፋ። መተማ ሲደርስ ነው የነገረን፤ ሱዳን ላይ ደወለ፣ ከዚያም ሊቢያ ሲደርስ ስልክ ሰጥቶኝ ስለነበር ስደውልለት ገንዘብ ያስፈልገኛል አለኝና ላኩለት፤ ከዚያ በኋላ ግን አልደወለም፡፡" ይላሉ የሟች ብሩክ አባት፡፡

አቶ ካሣ ባለፈው ረቡዕ የአሸባሪው ቡድን 'አይኤስአይኤስ' ን አረመኔያዊ ተግባር ለማውገዝ በተጠራው ሰልፍ ላይ ተገኝተው ነበር፡፡ እዚያው ሳሉ ከልጃቸው ጋር ሊቢያ የሄደው ጓደኛው ሞቷል ተብሎ ተነገራቸውና ሰልፉን አቋርጠው ወደ ሰፈር ሄዱ፡፡ "እዚያ ስደርስ የእኔንም ልጅ መርዶ ነገሩኝ"

ሃዘን ወደ ገፅ 2 ዞሯል


ብሩክ ካሳ - እድሜ 24


በቀለ ታጠቁ - እድሜ 20


ኤልያስ ተጫኔ - እድሜ 24


ዳንኤል ሀዱሽ - እድሜ 25

## በሊቢያው የጀልባ አደጋ አንድ ኢትዮጵያዊ መሞቱ ተረጋገጠ

አለማየሁ አንበሴ

ባለፈው እሁድ ከሊቢያ ወደ ጣሊያን ከ900 በላይ የተለያዩ አገራት ስደተኞችን አሳፍራ ስትጓዝ በሜዲትራኒያን ባህር የመስጠም አደጋ በደረሰባት ጀልባ ከሞቱት መካከል አንዱ በአዲስ አበባ የኮተቤ ነዋሪ የነበረው እንዳልካቸው አሰፋው ይገኝበታል፡፡

በታክሲ ረዳትነትና ሹፌርነት ይተዳደር የነበረው እንዳልካቸው፤ ኑሮን ለማሸነፍ የተሻለ ስራ ፍለጋ የዛሬ 6 ዓመት ወደ ሱዳን ማቅናቱንና እዚያ ለ5 ዓመታት ከቆየ በኋላ ከዓመት በፊት ሊቢያ መድረሱን ደውሎ እንዳሳወቃቸው ቤተሰቦቹ ለአዲስ አድማስ ገልፀዋል፡፡

"ለረጅም ጊዜ ድምፁ ጠፍቶብን ነበር" የሚሉት ቤተሰቦቹ፤ በሊቢያ ያለው ሁኔታ አስጨናቂ እየሆነ ከመጣበት ጊዜ አንስቶ በሃሳብና በሰቀቀን ‹እንዴት ሆኖ ይሆን?› እያሉ ድምፁን ለመስማት በመናፈቅ ወደ ፈጣሪያቸው ይለማመኑ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ በመጨረሻው ባልጠበቀው ሁኔታ እንደወጣ የቀረውን የእንዳልካቸውን ህልፈት የሰሙት ባለፈው ረቡዕ መሆኑን ወንድሙ

አደጋ ወደ ገፅ 22 ዞሯል


እንዳልካቸው አሰፋው

## ወደ ሳውዲ የተላከችው ወጣት ደብዛ መጥፋት እያወዛገበ ነው

- ከ2 ዓመት በላይ ወጣቷ የት እንደገባች አልታወቀም
- ኤጀንሲው የተጣለበት የፈቃድ እገዳ ተግባራዊ አልሆነም

መታሠቢያ ካሣዬ

ከሁለት ዓመት በፊት አል-ኢስማኤል በተባለ የውጪ አገር የግል ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ በኩል በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ኮንትራት ውሏ ፀድቆ ወደ ሳውዲ አረቢያ የተላከችው ወጣት ደብዛ መጥፋት እያወዛገበ ነው፡፡ ወጣቷ ላለፉት 27 ወራት የት እንደገባች የሚያመለክት አንዳችም ፍንጭ አልተገኘም፡፡

ሀያት አሊ መሐመድ በሚል ስም የካቲት 27 ቀን 2005 ዓ.ም ወደ ሳውዲ የተጓዘችው ወጣቷ፤ ከአገር

ወጣት ወደ ገፅ 22 ዞሯል

# የረቡዕ እለቱ ሰልፍ በአለም አቀፍ ሚዲያዎች ትኩረት ተሰጥቶታል

## ሰማያዊ ፓርቲ ከመንግስት የቀረበበትን ውንጀላ ተቃውሟል

አለማየሁ አንበሴ

በአሸባሪው ቡድን Isls ታጣቂዎች አሰቃቂ ግድያ የተገፀመባቸው ኢትዮጵያውያን ሰማዕታትን ለመዘከርና ሽብርተኝነትን ለማውገዝ ባለፈው ረቡዕ መንግስት በጠራው ህዝባዊ ሰልፍ ላይ ተቃዋሚ ከፀጥታ ሃይሎች ጋር የፈጠሩት ግጭት የዓለም አቀፍ ሚዲጠያዎችን ትኩረት ስቧል፡፡


በእለቱ በአልጀዚራ በተላለፈ ዘገባ፤ ህዝቡ በከፍተኛ ጩኸትና ቁጣ መንግስትን የሚተቹ መፈክሮችን እያሰማ ባለበት፣ በፀጥታ ሀይሎች የተወሰደው እርምጃ ታይቷል፡፡ ሰልፈኞች ሲደበደቡ የሚያሳዩ የተለያዩ ምስሎችም ተሰራጭቷል፡፡

የኢትዮጵያውያኑን በISIS ታጣቂዎች የመገደል አሰቃቂ ትዕይንት በተደጋጋሚ በምስል አስደግፎ ሲያቀርብ የነበረው ዩሮ ኒውስ፤ ረቡዕ እለት ምሽት ጀምሮ ሰልፉ ሲጀመር የነበረውን ሁኔታና በሰልፉ ማጠናቀቂያ ላይ ፖሊስ ከሰልፈኛው ጋር የተጋጨበትን ትዕይንት አሳይቷል፡፡

በዚህ አጭር የቪዲዮ ትዕይንት፤ መሬት ላይ የወደቁ ወጣት ሴቶች በፖሊስ ሲደበደቡ እንዲሁም አንድን ወጣት በርካታ ፖሊሶች መሬት ላይ በወደቀበት ሲደበድቡ ተስውሏል፡፡ ለረቡዕ እለቱ ሰላማዊ ሰልፍ ትኩረት ሰጥቶ የዘገበው ቢቢሲ በበኩሉ፤ ሰልፈኛው ያሰማውን ተቃውሞና በመጨረሻም ፖሊስ የሃይል እርምጃ ሲወስድ የሚያሳይ ዘገባ አስተላልፏል፡፡

የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር አቶ ሬድዋን ሁሴን ሰልፉ ከተከናወነ ከሰአታት በኋላ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ የታሰበው ሰልፍ በስኬት መጠናቀቁን ጠቁመው አንዳንድ ህገ ወጦች በሰልፉ ላይ ረብሻ ማስነሳታቸውንና ከዚህ ጀርባም የሰማያዊ ፓርቲ እጅ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ረብሻውን ተከትሎ በ7 የፌደራል ፖሊስ አባላት ላይ የመቁሰል አደጋ መድረሱን የጠቆሙት




ሚኒስትሩ፤ በሰልፉ የተሳተፉ ሰዎች ላይ ጉዳት ስለመድረሱ የተናገሩት ነገር የለም፡፡ በእለቱ ሪፖርተራችን በመስቀል አደባባይ ተገኝቶ እንደተመለከተው፤ በተለይ በቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤት አካባቢ በቡድን የተደራጁ ወጣቶች በከፍተኛ ጩኸት መንግስትን የሚያወግዙ መፈክሮች እያሰሙ ሲቃወሙ እንደነበር ለመታዘብ ተችሏል፡፡

በሰላማዊ ሰልፉ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ፤ ሽብርተኝነትን የሚያወግዘውን ንግግር እያደረጉ ሳለም ከፍተኛ ጩኸትና ተቃውሞ የተስተጋባ ሲሆን አንዳንዶችም ከፖሊስ ጋር ግጭት ፈጥረዋል፡፡

በመንግስት የተጠራውን ሰልፍ ተከትሎ፣ አብዛኞቹ የግልና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ዝግ የነበሩ ሲሆን በከተማው አንዳንድ አካባቢዎች የታክሲ እጥረት ተፈጥሮ እንደነበርም ታውቋል፡፡

ፖሊስ ሰልፉን ለመበተን አስለቃሽ ጭስ የተጠቀመ ሲሆን በርካቶች በግርግርና በትርምስ መሃል ወድቀው ለጉዳት ተዳርገዋል፡፡ የቀይ መስቀል አምቡላንሶችም ተጎጂዎችን ወደ ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ሲያመላልሱ የነበረ ሲሆን ቀላል ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦች ከሰዓት በኋላ እየታከሙ ከሆስፒታል ወጥተዋል፡፡

ፖሊስ በረብሻው መሃል ያገኛቸውን በርካታ ግለሰቦች በየቦታው በቡድን በቡድን ከሰበሰበ በኋላ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሲያመላልስ እንደነበር የአይን እማኞች ለአዲስ አድማስ ተናግረዋል፡፡

መንግስት ተቃውሞውን አደራጅቷል ሲል የወነጀለው ሰማያዊ ፓርቲ፤ ረቡዕ ዕለት ማምሻውን ባወጣው መግለጫ፣ መንግስት የጠራውን ሰልፍ በመደገፍ አባላቱና ደጋፊዎቹ በሰልፉ ላይ እንዲገኙ ጥሪ ማስተላለፉንና ጥሪውን ተከትሎ እንደማንኛውም ዜጋ በሰልፉ ላይ የሄዱ የፓርቲው አመራሮችና አባላት ገና ወደ መስቀል አደባባይ ከመድረሳቸው በፊት እየታደኑ መታሰራቸውን አስታውቋል፡፡ ፓርቲው "መንግስታዊ ሽብር የህዝብን ቁጣ ያባብሳል እንጂ መፍትሄ አይሆንም" በሚል ባወጣው መግለጫው፤ "መንግስት በዜጎች ላይ የወሰደው የጭካኔ እርምጃ በእጅጉ የሚያሳዝንና በጥብቅ ሊወገዝ የሚገባው ነው" ብሏል፡፡

መንግስት፤ ረብሻውን ያነሳሳው ሰማያዊ ፓርቲ ነው ማለቱን አጥብቆ የተቃወመው ፓርቲው፤ "የመንግስትን ቸልተኝነት በተቃወሙ ሰዎች ላይ የተወሰደው እርምጃ ሳያንስ፣ ጉዳዩን ከአንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አዛምዶ ተቃውሟቸውን ማጠልሸት በፍፁም ተቀባይነት የሌለው አፀያፊ ተግባር ነው፤ መንግስት ነኝ ከሚል አካል በፍፁም የማይጠበቅ ስህተት ነው" ብሏል፡፡ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች የተገኙት እንደማንኛውም ዜጋ በሰልፉ ለመሳተፍ እንደሆነም ፓርቲው አስታውቋል፡፡

በእለቱም 8 ያህል የአመራር አባላቱ ከሰልፉ በፊት እና በኋላ ተደብድበው መታሰራቸውን ፓርቲው አስታውቆ፤ በየፖሊስ ጣቢያውም በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች መታሰራቸውን ለማረጋገጥ ችያለሁ ብሏል፡፡

ሁለት የፓርቲው እጩ የምርጫ ተወዳዳሪዎችም ፖሊስ ጣቢያ ለታሰሩት የፓርቲው አመራሮች እራት ለማድረስና ለመጠየቅ በሄዱበት ወቅት መታሰራቸውን ፓርቲው አስታውቋል፡፡

ሃዘን ከገፅ 1 የዞረ

ያሉት አቶ ካሣ፤ "እኔ አይቼ አላረጋገጥኩም፤ የሰፈር ልጆች ግን አብረውት ስለሚውሉ እሱ መሆኑን በፌስ ቡክ ማረጋገጣቸውን ነግረውኛል" ብለዋል፡፡

ከትናንት በስቲያ በለቅሶው ላይ የተገኙ አንድ የሰፈሩ ነዋሪ፣ የብሩክ እናት ከአንድ ወር በፊት ጠበል ሊቀምሱ መጥተው ሰዉን "እባካችሁ ሆዴ እየተረበሸ ነው፤ ልጄ ብድግ ብሎ ሄዷል፤ በፀሎታችሁ አትርሱኝ" ማለታቸውን በሀዘን ያስታውሳሉ፡፡

አቶ ተጫኔ ዘለቀ የ24 አመቱ ወጣት ኤልያስ አባት ናቸው፡፡ እድሜያቸው የገፉ አዛውንት ሲሆኑ እሳቸውም ልክ እንደ አቶ ካሳ የሰፈር ልጆች "በመልክ ለይተን ምስሉን አግኝተናል" ባሏቸው መሰረት የልጃቸውን ሞት እንደተረዱ ይናገራሉ፡፡ ልጃቸው ከአገር ለመውጣት ማሰቡን ሲነግራቸው፣"በዚህ በእርጅና እድሜዬ ምነው ጥለኸኝ ትሄዳለህ" አሉት፤ "አይ እሄዳለሁ፤ እዚህ ምንም አላለፈልንም፤ እዛ ሄጄ ትንሽ እሞክራለሁ" ብሎ መሄዱን አባት ተናግረዋል። ሊቢያ እስኪገባ ድረስ በስልክ እንገናኝ ነበር፤ በኋላ ግን ጠፋብን ፤ልጆቼ በፌስቡክ ቢፈልጉትም ሊያገኙት አልቻሉም፤ ያለበትን እያፈላለግን ሳለ ይሄ መአት ወረደብን" ብለዋል በሃዘን ተውጠው፡፡

አሸናፊ ቦጋለና ውድነህ ታደሰ የሚኾቹ የኤሊያስና የብሩክ አብሮ አደጎች ናቸው፡፡ ከመሄዳቸው አንድ ቀን በፊት ማታ ብሩክን ወደ ቤት ሲገባ አግኝተነው፤ "እንዲህ -- ሰምተናል" ስንለው፣ "አዎ አስቤያለሁ" አለን፡፡ ኤሊያስ ግን እንደሚሄድ ነግሮን፣ መልካሙን ሁሉ ተመኝተንለት ነበር የተሰናበትነው፡፡ ደስታና ሀዘን አብረን ያሳለፍን ጓደኞቻችን ናቸው፤ረቡዕ ጠዋት ሰለማዊ ሰልፉን ለመውጣት ስንዘጋጅ አንድ የሰፈራችን ልጅ፣ "ሁለቱ ልጆች በአይኤስአይኤስ ቡድን ሲገደሉ በግልፅ የሚያሳይ ምስል አየሁ" ብሎ አሳየን፤ግን አላመነውም፤ ሌላ የሰፈራችን ልጅ ፊልሙን በኮምፒዩተሩ ይዞ መጥቶ "ይህ ጓደኛችሁ አይደለም ወይ?" ብሎ አሳየን፡፡ መጀመሪያ



ኤሊያስን አየነው፡፡ ቀጥሎ ሁሌም አቀርቅሮ በመሄድ የሚታወቀው ብሩክ፤ በምስሉም ላይ ከገዳዮቹ ስር አቀርቅሮ አየነው፤ብለዋል፡፡

"በጓደኞቻችን ላይ የተፈጠረው ነገር ልባችንን እጅግ ሰብሮታል፤ ቃላት ከሚገልፁት በላይ አዝነናል። አይደለም በምንወዳቸው፣ ጥምቀትን አብረን የምናሳልፍ ጓደኞቻችን ላይ ቀርቶ በግብፃውያኑ ላይ የተፈጠረውም እጅግ አሳዝኖናል፡፡ ኤሊያስም ሆነ ብሩክ ብዙም የመሄዱ ሀሳብ አልነበራቸው፤ እገሌ እዚህ ገባ፣ እከሌ እዚህ ደረሰ የሚሉ ወሬዎች አነሳስተዋቸው መሆን አለበት" ብለዋል የሚኾቹ ጓደኞች፡፡

ከጉራጌ አካባቢ መጥቶ ጨርቆስ ያደገው በቀለ ታጠቁ ወይም በቀለ አርሴማ እድሜው 20 መሆኑን የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ፡፡ በቀለ እዚያው ጨርቆስ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ በሚገኝ የሞባይል ቤት ተቀጥሮ ይሰራ ነበር፡፡ የበቀለ ቤት ከኤሊያስና ከብሩክ መኖሪያ ብዙም ባይርቅም ከአገር አብረው ባይወጡም ስደት ላይ ተገናኝተዋል፡፡ የበቀለ መርዶም ቤተሰቦቹ ወዳሉበት ጉራጌ ዞን ደርሷል፡፡

ለጨርቆስ ነዋሪዎች የሰሞኑ መርዶ እርም ማውጣት ብቻ አይደለም፤ "ቀጥሎ ማን ይሆን ተረኛ?" የሚል ስጋት ያዘለ ነው፤ ይላሉ ነዋሪዎች። ሀዘንተኞቹ ቤት እየመጡ ከሚያለቅሱ የሰፈሩ ሰዎች በርካታዎቹ የልጆቻቸውን ቁርጥ አላወቁም-ይኑሩ ይሙቱ በጥርጣሬ ውስጥ ናቸው፡፡ ወሬው ሁሉ የስጋት ነው፡፡ "እከሌ ሄዷል፤ እዚህ ፎቶ ላይ አልታየም ነገርግን ድምፁ ከጠፋ ቆይቷል፤ የእከሌ መርዶ ሊነገር ነበር ፤ ፎቶውን እርግጠኛ ስላልሆንን ተውነው፤የእከሌ ልጅ ካምፕ ነኝ ብሏል፤ እነእከሌን ግን ማግኘት አልቻለም" እያሉ ጥርጣሬያቸውን ይተነፍሳሉ፡፡

ልጆቻቸው ወደ ሊቢያ የተሰደዱባቸው ቤተሰቦች፣ ነገን በስጋትና በፍርሃት ነው የሚጠብቋት፡፡ ምን ይዛላቸው እንደምትመጣ እርግጠኛ አይደሉም፡፡ ከሁሉም አሳዛኙ ደግሞ ልጆቻቸው በስደት መሞታቸው እየታወቀ ቢነገራቸው በድንጋጤ አንድ ነገር እንዳይሆኑ በሚል ፍራቻ ፤ከዛሬ ነገ የልጄን ድምፅ እሰማለሁ እያሉ በተስፋ የሚኖሩ ወላጆች መኖራቸው ነው፡፡

በትግራይ ክልል በማእከላዊ ዞን አህፈሮም ወረዳ በምትገኘው የእንትጮ ከተማ ነዋሪ የነበረው ዳንኤል ሀዱሽ ሌላው የሊቢያው አሸባሪ ቡድን የጥፋት ሰለባ ነው፡፡ የ25 አመቱ ወጣት ዳንኤል፣ ባለፈው አመት ከጅማ ዩኒቨርሲቲ በኮምፒዩተር ሳይንስ ተመርቋል። በተማረበት ሙያ ሥራ ሲያፈላልግ እንደነበር ቤተሰቦቹ ይናገራሉ፡፡ በመጨረሻ ለወላጅ እናቱ ለወይዘሮ ዛፉ ገብረእየሱስ፣ ሁመራ ስኳር ፋብሪካ ስራ እንዳገኘ በመንገር ነበር ጥር 25 ቀን 2007 ዓ.ም የተለያቸው፡፡ ከቀናት በኋላም "ያለሁበት ቦታ የኔትወርክ ችግር ስላለ እኔ ካልደወልኩኝ አታገኙኝም" ማለቱን፣ ከዚያም ሊቢያ መግባቱን ለእናቱ ደውሎ እንደነገረ ቤተሰቡ ይገልጻል፡፡ የዳንኤልን መልክ በፎቶ ለመለየት የሚያስቸግር እንዳልሆነ የተናገሩት ምንጮቻችን፤ ከትላንት በስቲያ ለእናቱና ሌሎች ቤተሰቦቹ መርዶው ተነግሮ፣ በእንትጮ ማርያም ደብረገነት ፍትሀት እንደተደረገለትም ጠቁመዋል፡፡

በፌስቡክ ምስል በማየት ሞትን ማርዳት ልጆቻቸውን ያጡትንም ሆነ ሌሎች በስጋት ላይ ያሉትን ሙሉ በሙሉ ላያሳምን ይችላል የሚል ጥርጣሬ ቢፈጠርም ወላጆች የሰፈር ልጆች አይተናል ባሉት የምስል መረጃ ነው ሀዘን የተቀመጡት፡፡ አንድ የመቀሌ ወጣት ከሚኾቹ አንዱ እንደሆነ ተደርጎ በፌስቡክ የተለጠፈውን ፎቶውን እያስተባበለ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡ ሆኖም በስደት ላይ ያለ ሰው ለማፈላለግ ከፌስቡክ የተሻለ መንገድ አልተገኘም፡፡ በዚህም የተነሳ ወደ ሊቢያ የሄደ ሰው ያላቸው ቤተሰቦች በፌስቡክ ፎቶውን በመለጠፍ አፈላልጉን እያሉ ነው፡፡

# ኢትዮጵያም ስለ ልጆቿ አለቀሰች!

## የስቅሶና የዋይታ ድምፅ በደቡብ አፍሪካ፣ በየመን፣ በሊቢያ...

በዲ/ን ተረፈ ወርቁ nikodimos.wise7@gmail.com



*«. . . ዓይኔ በእንባ ደከመ፣ አንጀቴም ታወከ፡ ስለ ወገኔ ሴት ልጅ ቅጥቃጤ አንጀቴ በምድር ላይ ተዘረገፈ፡፡ አቤቱ የሆነብንን አስብ፣ ተመልከት ስድባችንንም እይ . . .፡፡» (ሰቆ. ፪፡፲፩ ፤ ፭፡፩)*

ይህን ቃል የተናገረው በመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ዘንድ *«አልቃሻው፣ ባለ ሙሾው ነቢይ»* በመባል የሚታወቀው አይሁዳዊው ነቢዩ ኤርምያስ ነው፡፡ ይህንን ነቢይ እንዲህ እንደ ርጉሩኋ እናት አንጀቱን ያላወሰው፣ እንባው እንደ ክረምት ጎርፍ እንዲፈስ ያደረገውና ነፍሱ ድረስ ዘልቆ ብርቱ ኀዘንና ቅጥቃጤን የፈጠረበት ምክንያቱም፡- ኢየሩሳሌም በጠላቶቿ ተማርካ፣ ሕዝቦቿም ተዋርደው፣ ከአገራቸውና ከምድረ ርስታቸው ተነቅለው፣ ያ እጅጉን ያከብሩትና ይፈሩት የነበረው መቅደሳቸው ፈርሶ፣ በግዞት ውስጥ የነበሩትን የሕዝቡን ሰቆቃና መከራ በዓይኑ በማየትና የመከራቸውም ተካፋይ በመሆኑ ነበር፡፡፡

ጸሎተኛውና ኀዘንተኛው ኤርምያስ ስለ ኢየሩሳሌም ኃጢአትና በደል፣ በዚህም ስለደረሰባት ከባድ ውርደትና መከራ፣ ዓይኔ ምነው የእንባ ምንጮች ፈሳሽ በሆኑልኝ በማለት የተመኘ፣ በብርቱ የጸለየ፣ የተማጸነና የማለደ የሀገሩ፣ የሕዝቡ ውርደትና ጭንቀት፣ መከራና አበሳ፣ ሰቆቃና ዋይታ እንቅልፍ፣ እረፍት የነሳው ብርቱ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር፡፡

ከረሃብ የተነሳ እናቶች የአብራካቸውን ክፋይ ልጆቻቸውን የበሉበትን፣ በቅምጥልነት የኖሩ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅትና ደናግል በጠላቶቻቸው ብርቱና ጨካኝ ክንድ ከሰውነት ክብር ተዋርደው፣ ከመፈራትና ከመወደድ የክብር ሰገነት ላይ ተሽቀንጥረው፣ ተንቀውና ተጥለው በጎዳና ያለ ምንም ተስፋ ሲንከራተቱና የሁሉም መጫወቻና ማላገጫ ሲሆኑ ሕፃናት በእናቶቻቸው ደረቅ ጡት ላይ አፋቸው ተጣብቆ በጣእረ ሞት ተይዘው ሲጨነቁ፣ አባቶችና እናቶች የጥንቱን የበረከትና የድሎት ኑሮአቸውን እያሰቡ እንባ ሲቀድማቸው፣ ከክፉ ጠኔ የተነሳ ወላዶች የማኅፀናቸውን ፍሬ እንኳን ለመብላት ያስጨከናቸውን ያን ክፉ ቀናት የታዘበ ነቢዩ፤ ስለ ቅድስት ምድሩና ሕዝቡ ሰቆቃና መከራ እንዲህ ጸለየ፡-

«እግዚአብሔር ከሰማይ እስኪጎበኝና እስኪመለከት ድረስ ዓይኔ ሳታቋርጥ ዝም ሳትል እንባን ታፈሳለች፡፡» (ሰቆ ፫፡፵፱፡፶) በማለት በመጮኽና በመቃተት ስለ አገሩ ውርደት፣ ስለ ሕዝቡ መከራ ሌት ተቀን በእንባ ባሕር እንደዋኘ ውሎ የሚያድር ኀዘንተኛና ሙሾ የሚደረድር ነቢይ ነበር፤ አይሁዳዊው የእግዚአብሔር ሰው ኤርምያስ።

ሰሞኑን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እንደ አይሁዳዊው ነቢይ ኤርምያስ አንገታችንን የሚያስደፋና በሃፍረት የሚያሸማቅቅ፣ ጆሮን ጭው የሚደርግ፣ የወላድ እናቶችን አንጀት የሚያላውስና በእንባ ጎርፍ እንዲታጠቡ የሚያደርግ ሌላ የሞት፣ ሌላ የውርደት፣ መሪር መርዶ፣ ሰቅጣጭና ክፉ ዜና ለእናት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ምድር፣ ከሊቢያ፣ ከደቡብ አፍሪካ፣ ከሀገረ የመን ተሰምቷል፡፡

በእርግጥ የአገራችንና የወገናችን ውርደትና መከራ ገና ዛሬ የተጀመረ አይደለም። በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ዓለምን ሁሉ እግዚኦ ካሰኘ ድርቅ፣ የረሃብ/የጠኔ እልቂት እስከ የወንድማማቾች የእርስ በርስ ደም መፋሰስ፣ ዘግናኝ ጦርነትና ፍጅት ድረስ የሕዝባችን ስደት፣ መከራና ውርደት የአገራችን ዋንኛ መለያ ሆኖ አብሮን ለዓመታት ዘልቋል። በዓለም ሁሉ ፊት ኢትዮጵያዊነት ብዙዎችን እንዲሳቀቁ ያደረጋቸው "አሳፋሪ" ማንነት የሆነበትን ጥቁር ታሪካችንን ዛሬም ገና በቅጡ ልንላቀቀው እንዳልቻልን እያየን፣ እያስተዋልን ነው፡፡

ስደትና ውርደት፣ መከራና ሞት የሕዝባችን ዕጣ ፈንታ እንዲሆን የተፈረደበት ይመስል ዛሬም ምስኪን ሕዝባችን በሚሰቀጥጥ ሁኔታ የአውሬ፣ የበረሃና የባሕር ሲሳይ እየሆነ ነው፡፡ በለስ ቀንቶት ወደ ባዕድ ምድር የገባው ሕዝባችንም ከእንስሳ በወረደ ሁኔታ ሰብአዊ ክብሩ ተደፍሮና ተዋርዶ፣ የሞት ሞት እንዲሞት የተደረገበትን አጋጣሚዎችንም ደግመን ደጋግመን ታዝበናል፡፡ በሳውዲ አረቢያ ሊያውም በአገራችን ኤምባሲ ፊት ለፊት አስከሬኗ በመኪና መሬት ለመሬት እንዲጎተት የተደረገበትን ያን አንገታችንን ያስደፋንን የወገናችንን ውርደት መርሳት እንዴት ይቻለናል?!

በመካከለኛው ምሥራቅ ከፎቅ ላይ የሚወረወሩ፣ የፈላ ውሃ የሚደፋባቸው፣ አሰቃቂ የሆነ ግፍና ውርደት የሚፈጸምባቸው... የእህቶቻችን ሰቆቃና መከራ ዛሬም ማብቂያ የተገኘለት አይመስልም። በኬንያ፣ በታንዛንያ፣ በማላዊና በሞዛምቢክ እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ "ሕገ ወጥ" ናችሁ በሚል ሰበብ በእስር ቤት ታጉረው ፍዳ መከራቸውን እየቆጠሩና "የወገን ያለህ ደረሱልን" እያሉ የሚገኙ ወገኖቻችን ቁጥርም ቀላል አይደለም።

በቅርቡም በደቡብ አፍሪካ ምድር ወገኖቻችን በቁማቸው በእሳት እንዲጋዩ፣ በቆንጨራና በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ ተፈረደባቸው። ጥረው ግረው፣ ለፍተውና ደክመው ያከማቹት ሀብት ንብረታቸውም የዘራፊዎች ሲሳይ ሆነ። ይሄ ያደረሰብንን ጥልቅ ሃዘን በቅጡ ሳንወጣ ዳግመኛ ልባችንን በኀዘን ጦር የወጋ፣ ጆሮን ጭው የሚያደርግ ክፉ ወሬ ከወደ ሊቢያ ምድር ሰማን፡፡ 28 የሚሆኑ ወገኖቻችን በሊቢያ በረሃ ዘግናኝ በሆነ አኳኋን በግፍ ታርደው ሰማዕትነትን መቀበላቸውን ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን አረዱን፡፡

በንጉሥ ሄሮድስ ዘመን ለተፈጁት 14 ሺ

ኢትዮጵያ ወደ ገፅ 9 ዞሯል

# በአይሲስ የተጣሰው የቁርአን ቃል

## "ሙስሊም ባልሆኑ ንፁሃን ሰዎች ላይ ግድያ የፈፀመ ሰው የጀነትን እጣን አያሸትም"

ኑርሁሴን እንድሪስ

በሁለቱ ታላላቅ እምነቶች ውስጥ (ክርስትና እና እስልምናን ማለቴ ነው) ለሰው ዘር በሙሉ የተላለፈ አንድ መለኮታዊ መልዕክት አለ፡፡ ይህ መልዕክት በሁለት ቅዱሳን መፃህፍት ውስጥ ቢገኝም መልዕክቱ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ የሰው ልጅን ነፍስ ማጥፋት የተወገዘ ተግባር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እና ቁርአን ያወሳሉ፡፡ ይህን መልዕክት ለሰው ልጆች የላከው ደግሞ የሰማይና የምድር ፈጣሪ እንዲሁም የሰው ልጆችን ጨምሮ በሁለቱ መካከል ያሉትን በሙሉ ያስገኘው አምላክ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ምዕራፎቹ ውስጥ የሰው ልጅ ግድያን ይከለክላል፡፡ በማቲዎስ 5፡21፣ ምፅአት 20፡13፣ ሮሜ 13፡14፣ ዘፍጥረት 9፡5-6 ... ወዘተ፤ በጣም ብዙ አንቀፆች ሰውን መግደል የማይፈቀድ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በማቲዎስ 5፡21 ውስጥ የሰፈረው ቃል እንዲህ ይላል፡-

"... አትግደል፤ የገደለ ሰው ይፈረድበታል ..."

በቅዱስ ቁርአን ውስጥም የሰው ልጅን ነፍስ ማጥፋት ትልቅ ሀጢአት መሆኑ በብዙ አንቀፆች ውስጥ ሰፍሮአል፡፡ በአል-ሙምታሐና፡8፣ በአል-ኒሳ 89—91፣ በአል-በቀራ፡ 190፣ በአል-አንኢም፡151... ውስጥ የመግደልን አስከፊነት ያነሳል፡፡ በአል-ማኢዳ፡ 32 ውስጥ የሰፈረው እንዲህ ይነበባል፡-

"... አንድ ነፍስን የገደለ ሰው መላውን የሰው ዘር እንዳጠፋ ይቆጠራል፤ አንድ ነፍስን ያዳነ ሰው መላውን የሰው ዘር እንዳዳነ ይቆጠራል..."

በእስልምናም ሆነ በክርስትና እምነቶች ውስጥ የመግደልን አስከፊነት የሚገልፁ የአምላክ ቃላቶች ተቀምጠዋል፡፡ ምዕመናን ከዚህ ክፉ ተግባር እንዲቆጠቡም ሐያሉ አምላክ አዟል፡፡

ነገር ግን በእስልምናም ሆነ በክርስትና ሐይማኖት ተከታዮች በርካታ የግድያና የሽብር ተግባሮች መፈፀማቸውን ታሪክ ይነግረናል፡፡ እንደ ፖለቲካ ተመራማሪዎች ከሆነ፤ የሽብርተኝነት ዋና አላማ በመንግስት አልያም በሆነ አካል ላይ ተፅዕኖና ማስገደድን መፍጠር ነው፡፡ ሽብርተኝነት ከማንኛውም ሀይማኖት ጋር የሚገናኝ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ፍትህ ያጡ ግለሰቦች የሚከተሉት ተግባር ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ የፖለቲካ አላማን ያነገቡ ቡድኖች የሚፈፅሙት ነው፡፡

ሃይማኖቶች መግደል ክልክል መሆኑን የሚገልፁ ከሆነ ታዲያ ለምንድነው ሃይማኖተኞች የሚገድሉት? ግድያና ሽብር ማካሄድ የሚገናኘው ከሃይማኖት ጋር ነው ወይስ ከፖለቲካ?

የተለያዩ እምነቶችን የሚያራምዱ የአለማችን ሰዎች በደርዘን የሚቆጠሩ ግድያና ሽብሮችን በንፁሐን ዜጎች ላይ ፈፅመዋል፡፡ ለምሳሌ በ2011 ዓ.ም የቀኝ ክንፍ ክርስቲያን አክራሪ የሆነው አንደርስ ብሪቬክ በኖርዌይ 77 ሰዎችን ገድሏል፡፡ ብሪቬክ ከፍተኛ የሆነ የእስልምና ሃይማኖት ጥላቻ እንደነበረው በወቅቱ ተገልጿል፡፡

- በ2013 ዓ.ም የሶማሊያ ሙስሊሞች በዌስትጌት የገበያ ሞል ውስጥ ቦንብ አፈንድተው የ67 ሰዎችን ህይወት ቀጥፈዋል፡፡
- በ1955 ዓ.ም በኦክላሐማ ከተማ ውስጥ የፈነዳው ቦንብ 166 ንፁሐንን ገድሏል፡፡ ድርጊቱን የፈፀሙት ደግሞ ቲሞቲ እና ቴሪ የተባሉ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡
- በ2002 ዓ.ም በባሊ ደሴት ላይ የፈነዳው ቦንብ የ202 ዜጎችን ነፍስ በልቷል፡፡ ድርጊቱን የፈፀሙት ጀማህ ኢስላሚያ የተባሉ የእስልምና ተከታዮች ናቸው፡፡
- በ2004 ዓ.ም የሰሜን ምስራቅ ህንድ ክርስቲያኖች ድርጅት 44 ሰዎችን ገድሏል፡፡
- በ2001 ዓ.ም የተጠለፈ አውሮፕላን በዓለም የንግድ ድርጅት ህንፃ ላይ ተጋጭቶ 3000 ንፁሐንን ገድሏል፡፡ ተግባሩን የፈፀሙት የአልቃኢዳ ሙስሊሞች ነበሩ፡፡
- በ2015 በጋሪሳ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የአል-ሻባብ ሙስሊሞች 148 ኬንያውያንን ገድለዋል፡፡
- በ1972 ዓ.ም የካቶሊክ እምነት ተከታዮች የሆኑት የአይሪሽ ሪፐብሊካን አርሚ ቡድኖች በለንደን 47 ሰዎችን በቦንብ ፈጅተዋል፡፡

እነዚህን የመሰሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሽብርና ግድያዎችን በሁለቱም እምነቶች ውስጥ የሚገኙ ቡድኖችና ግለሰቦች ፈፅመዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ ሽብርና ግድያ ባለቤትነቱ የማንም ሃይማኖት አለመሆኑን ነው፡፡

የቀድሞ የግብፅ ሙፍቲ ሼክ አሊ ጎማኢ እንደተናገሩት፤ "ሽብርተኝነት ሃይማኖት የሚወልደው ጉዳይ አይደለም፡፡ ሽብርተኝነት የብልሹ አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡ ሽብርተኝነት፣ የእብሪተኝነትና አጥፊነት መገለጫ ነው፡፡ ብልሹነት፣ እብሪተኝነትና አጥፊነት ከመለኮታዊ ልቦና ጋር የሚገናኙ አይደሉም፡፡"


ራሱን የእስልምና መገለጫ አድርጎ የሚንቀሳቀሰው አይሲስም የግብፁ ሙፍቲ በተናገሩት ውስጥ የሚፈረጅ መሆኑን ተግባራቱ ያሳያሉ፡፡ ባለፈው እሁድ በ28 ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈፀመው አሰቃቂ ግድያ አላማው ግልፅ አይደለም፡፡ አይሲስ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ምን አይነት ቅያሜ ውስጥ ቢገባ ይሆን 28 ዜጎቿን የፈጀው? ለሚለው ጥያቄም መልስ የለውም። አይሲስ የገደላቸው ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ ነው እንዳንል በማግስቱ 24 የኢራቅ ሙስሊሞችን ገድሏል፡፡ ለዚህም ነው የአይሲስ አላማና መገለጫ የግብፁ ሙፍቲ ከተናገሩት ጋር ይገናኛል ያልኩት፡፡ አይሲስ ሙስሊም ክርስቲያን ሳይል በሰው ዘር ላይ የዘመተ አረመኔ ቡድን መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

አይሲስ የሸሪአ ተከታይ ነው ከተባለ ለምንድነው ታዲያ በቁርአን ውስጥ የሚገኘውን አል-ማኢዳ፡32 የጣሰው? "አንድ ነፍስን ያጠፋ መላውን የሰው ዘር እንዳጠፋ ይቆጠራል፤ አንድ ነፍስን ያዳነ መላውን የሰው ዘር እንዳዳነ ይቆጠራል፡፡" የሚለው መለኮታዊ ቃል ለምንድነው በአይሲስ ያልተከበረው?

የሰው ነፍስን አጥፍቶ ጀነትን መመኘት የዋህነት ይመስለኛል፡፡ በታላቁ መምህር በነብዩ ሙሀመድ የህይወት ፈለግ ውስጥ የዚህ አይነቱ ርዕዮት በፍፁም የተወገዘ ነው፡፡ በቡካሪ ሐዲስ ውስጥ ነብዩ ሙሀመድ የተናገሩት ይህን ይመስላል፡-

"ሙስሊም ባልሆኑ ንፁሐን ሰዎች ላይ ግድያ የፈፀመ ሰው የጀነትን እጣን አያሸትም"

ንፁሐን ሰዎች ላይ ግድያ ፈፅመን ጀነት መግባት የምንመኝ ከሆነ ካሁኑ እርማችንን ማውጣት አለብን፤ ነብይ ሽታውን እንኳን እንደማናገኘው አርድተውናልና፡፡ በእስልምና ሐይማኖት ውስጥ ጥልቅ እውቀት ያለው አይሲስ ወይስ መልእክተኛው ሙሐመድ? አይሲስ የሚያራምደው እስልምና ከየት የመጣ ይሆን? ነብዩ ካስተማሩትና ካዘዙት የእስልምና እውቀት ውጭ ከየት ሊመጣ!


ሜታ አቦ ቢራ አ/ማህበር፣ በቅርቡ በሽብርተኞች እጅ
በአሰቃቂ ሁኔታ ህይወታቸውን ላጡ ንጹህ ኢትዮጵያውያን፣
እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ በተከሰተው አሳዛኝ ችግር
ህይወታቸውን ላጡ ኢትዮጵያውን ቤተሰቦች፣ ወዳጆች
እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በዚህ እጅግ አሳዛኝ
እና አስቸጋሪ ጊዜ ከልብ የተሰማውን ሐዘን ይገልጻል።

# “መዋጮዬ ከማንም ያልበለጠ ቢሆንም መንገዱ በሥሜ ተጠርቷል” - ቀኛዝማች ዘውዴ ብራቱ

*በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ሰዎች ሥም የሚጠሩ መንደሮችና መንገዶች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡ “ወርቁ ሠፈር፣ የሺ ደበሌ ማዞሪያ፣ አባ ቦራ ቅያስ፣ ሞላ ማሩ አካባቢ፣ አባ ኮራን መንደር...” የሚባሉትን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የመንደርና የመንገዶቹ ስሞች በመንግስት የሚሰጡበት ጊዜ አለ፤ እንደ፣ “ቸርች ል ጎዳና”፡፡ በአካባቢው ታዋቂ ሥራ ከሚሰራ ተቋም ወይም ግለሰብ ጋር በተያያዘ ስያሜውን ያገኘ ይኖራል፤ እንደ “ባሻ ወልዴ ችሎት”፡፡ ህብረተሰቡም አብረውት ከሚኖሩት መሐል የተለየ አክብሮ ለለገሰው ሰው መጠሪያ እንዲሆን ዕውቅና የሚሰጠው አለ፤ እንደ “ዘውዴ ብራቱ መንገድ፡፡” ከክፍለ ሀገር አውቶቢስ ተራ ወደ አብነት በሚያስኬደው አውራ ጎዳና ወደ አዲስ ከተማ መንደሮች ከሚያስገቡት ቅያሶች አንዱ በስማቸው የሚጠራው ቀኛዝማች ዘውዴ ብራቱ፤ መንገዱ እንዴት በስማቸው ሊጠራ እንደቻለ “የሕይወቴ ጉዞ” በሚል ርዕስ ካዘጋጁት የሕይወት ታሪክ ጥቂቱን ሊጋዜጣ በሚያመች መልኩ አሳጥረን አቅርበነዋል፡፡*

ወላጅ አባቴ ፊውራሪ ብራቱ ደጋጋ በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች በተለያዩ ቦታዎች ህዝብና አገራቸውን አገልግለዋል፡፡ በማይጨው ጦርነት ተሳትፈዋል፡፡ የራስ አበበ አረጋይ ንብረት እንደራሴ ባለ አደራ ሆነው ነበር፡፡ ለራስ ሙሉጌታ ድረው በወንበርነት ሰርተዋል፡፡ “ወንበር” ማለት በፍርድ ቤት ወይም በአስተዳዳሪ ተሰይሞ የሚሰራ ሹመኛ ማለት ነው፡፡ በዚህ ሹመት በተለያዩ ክፍላጸ ሀገራት በመዘዋወር አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ ከፍርድ ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ በመውሰድ በሙያው ሰርተዋል፡፡ በትውልድ መንደራቸው በአይመለል ክስታኔ ጉራጌ ዞን በግብርና ሥራ የተዳደሩበት ታሪክም አላቸው። እናቴ እመት ግምጃ ኢላላ የቤት እቤት ነበሩ፡፡ ወላጆቼ በትዳራቸው ካፈሯቸው ሸባጽ ልጆች እኔ ሦስተኛው ልጅ ነኝ፡፡

የተወለድኩት በአዲስ አበባ ከተማ፣ ሰባ ደረጃ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ፣ ከራስ መኮንን ከፍ ብሎ ከሚገኘው “አባታችን ሰፈር” ውስጥ ሲሆን ዕለቱ ሚያዚያ 23 ቀን 1920 ዓ.ም ነው፡፡ በአሁን ወቅት በ87 ዓመት ዕድሜ ላይ እገኛለሁ፡፡ የተወለድኩበት መንደር “አባታችን ሰፈር” የሚል መጠሪያ ያገኘው የጳጳሳት መኖሪያ አካባቢ በመሆኑ ነበር፡፡

ትውልዴ አዲስ አበባ ቢሆንም በአባቴ አገር ሚልኮ የቤተክህነት ትምህርት መከታተሉን በ7 ዓመቴ ጀምሬ በተለያዩ ደረጃዎች በማለፍ 12 ዓመት ሲሞላኝ በሚልኮ ጥንታዊት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በድቁና ማገልገል ጀመርኩ፡፡

ከድቁና አገልግሎቴ ጎን ለጎን ቤተሰቦቼን በስራ እረዳ ነበር፡፡ የ17 ዓመት ወጣት ሳለሁ ከዛሬዋ ባለቤቴ ከወ/ሮ ትክክልወርቅ ሞጆ ጋር ጥር 7 ቀን 1937 ዓ.ም ትዳር መሰረትኩ። ትዳራችን 70 ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ አባቴ በሰጠኝ መሬት ላይ የራሴን ጎጆ ቀልሼ ትዳሬን ማስተዳደር ብችልም ተጨማሪ ትምህርትና ዕውቀት ማግኘት ስለምችልበት ሁኔታ ዘወትር በማሰብ እተጋ ነበር፡፡



ቀኛዝማች ዘውዴ ብራቱ

ወ/ሮ ትክክልወርቅ ሞጆ

በ1941 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሆኜ ዘመናዊ ትምህርት እንድማር እንዲፈቅዱልኝ አባቴን በሽማግሌ ሳስጠይቃቸው፤ “ሚስቱን የት አድርጎ ነው የሚማረው?” ብለው ተቃውሞ አቅርበው ነበር፡፡ ባለቤቴ ወ/ሮ ትክክልወርቅ ሞጆ፤ አዲስ አበባ መጥታ መኖር ትፈልግ ስለነበር፣ የአባቴን ተቃውሞ ስትሰማ “ይማር እኔ እናቱ ጋ አገር ቤት እቀመጣለሁ” በማለቷ ትምህርት ቤት የመግባት ፍላጎቴ ተሳካ፡፡

በአዲስ አበባ ትምህርት የጀመርኩት በሊሴ ገብረ ማርያም ትምህርት ቤት ሲሆን በወር 5 ብር እከፍል ነበር፡፡ በዕድሜዬ፣ በቁመቴና በዕውቀቴ ተገምግሜ ሁለተኛ ክፍል በመመደብ ነበር ትምህርት የጀመርኩት፡፡ በቀኑ ክፍለ ጊዜ በሊሴ ገብረ ማርያም ፈረንሳይኛ እየተማርኩ፣ በማታው ክፍለ ጊዜ እንግሊዝኛ ቋንቋ ለመማር ካቴድራል ትምህርት ቤት ገባሁ፡፡ በቀጣዩ ዓመት ልዑል ወሰንሰገድ ትምህርት ቤት 3ኛ ክፍል በመግባት የዕውቀት ጥሜን ለማርካት ጥረቴን ቀጠልኩ፡፡ ከክፍል ወደ ክፍል በደብል እያለፍኩ በ1944 ዓ.ም 8ኛ ክፍል ደረስኩ፡፡

እኔ በአዲስ አበባ ሆኜ ትምህርቴን እንድከታተል ፈቃደኛ የሆነችው ባለቤቴ ወ/ሮ ትክክልወርቅ ሞጆን ማገዝ እንዳለብኝ ስለተሰማኝና አብረን መኖር እንዳለብን ስለወሰንኩ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ ተወዳድሬ በስታቲስቲክ ክፍል ተቀጥሬ በወር 40 ብር እየተከፈለኝ መስራት ጀመርኩ፡፡ ከዚህ በኋላ ባለቤቴም አዲስ አበባ መጥታ አብረን መኖር ጀመርን፡፡

ከአገር ግዛት ሚኒስቴር በኋላ በቡታጅራ፣ በሱሉልታ፣ በአዲስ ኣለም፣ በአቃቂ በሰቃ፣ በሆለታ ገነትና መሰል ቦታዎች በመዘዋወር በተለያየ የኃላፊነት ቦታ እስከ 1957 ዓ.ም ድረስ ካገለገልኩ በኋላ በግል የጥብቅና ሙያ ለመስማራት ስለወሰንኩ፤ እራሴን ከቅጥር ሥራ አሰናብቼ በ1958 ዓ.ም ከፍርድ ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ ወስጄ መስራት ጀመርኩ፡፡ በዚህ ዘርፍ ያለኝን ዕውቀት ለማሻሻልም ወደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፋኩልቲ በመግባት የህግ ትምህርት ተከታትዬ፣ ሐምሌ 8 ቀን 1961 ዓ.ም ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እጅ በህግ ሰርተፍኬት ተቀብያለሁ፡፡

በ1962 ዓ.ም ፓርላማ መግባት የቻልኩት ምዕራብ አዲስ አበባን ወክዬ በመወዳደር በአንደኛ ደረጃ ማሸነፍ ስለቻልኩ ነበር፡፡ በውድድር ወቅት ለህብረተሰቡ ቃል በገባሁት መሰረት የህዝቡ ችግሮች ናቸው ያልኳቸውን ጉዳዮች በተደጋጋሚ ለፓርላማው አቅርቤያለሁ። ለምሳሌ በየጎዳናው ላይ ሱቅ በደረቴ የሚሰሩ ነጋዴዎች፤ ያለ አማራጭ የሥራ ቦታ በየዕለቱ እንዲባረሩ መደረጉ ስህተት መሆኑን ለፓርላማው አሳውቄ፣ ፓርላማውም አቤቱታውን ተቀብሎ መፍትሔ ይፈለግለት ብሎ አጽድቆታል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ዳቦ ሳይጠግብ በቁማር ሱስ እንዲጠመድ እየተደረገ ነው በማለት በአዲስ አበባ ከተማ የተስፋፋውን የቁማር ማጫወቻ ቤቶችና ማሽን ብዛት በማመልከት ለፓርላማው ያቀረብኩት አቤቱታም ምክር ቤቱ የጉዳዩን አስከፊነት ከተቸበት በኋላ የቁማር መጫወቻ ማሽኖች በ24 ሰዓት ውስጥ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያሳለፈውን ውሳኔ የመወሰኛ ምክር ቤትም ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡

በ1963 ዓ.ም ህዝቡን አስተባብሬ ኮሚቴ በማቋቋም ከአዲስ ከተማ ሰፈር እስከ አማኑኤል ቶታል እና ወደ ኮካኮላ የሚያስኬደው መንገድ ድረስ በማገኛኘት አስፓልት ሆኖ የተሰራ ሲሆን፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበሩት ዶ/ር ኃይለጊዮርጊስ ወርቅነህ እንዲመርቁልን አድርገናል፡፡ ህዝቡ በዚህ የመንገድ ስራ ወቅት አደርግ የነበረውን ጥረት አይቶ ወጪ ወራጁ ሁሉ “ዘውዴ ብራቱ መንገድ” ብሎ ሰይሞታል፡፡ መዋጮዬ ከማንም ያልበለጠ ቢሆንም፤ መንገዱ በስሜ ሲጠራ ስሰማ ደስ ይለኛል፡፡

የደርግ መንግስት በስልጣን ማብቂያው ዋዜማ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጠርቶ በኢሰፓ አዳራሽ ሀገር አቀፍ ስብሰባ ባደረገበት ወቅት፤ ማን እንደጠቆመኝ ባላውቅም ምዕራብ አዲስ አበባን ወክዬ በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ሰብሳቢነት በተካሄደው ጉባኤ ለአራት ቀናት ተሳትፌያለሁ፡፡

ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላም የሰላም እና መረጋጋት ኮሚቴ ሲቋቋም፣ የኮሚቴው ሊቀመንበር ሆኜ እንዳገለግል ህዝብ ስለመረጠኝ የተደረገልኝን ጥሪ ተቀብዬ በኃላፊነት የተሳተፍኩ ሲሆን ሰላምና መረጋጋት ሲረጋገጥ ወደ ተለመደው የሙያ ሥራዬ ተመልሻለሁ፡፡

በደቡብ ክልላዊ መንግሥት በጉራጌ ዞን ለሚገኘው የአይመለል ክስታኔ ህዝብ በልማት ዙሪያ የተለያዩ አስተዋጽኦዎች ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡፡ የክስታኔ ጉራጌ ህዝብ የጎርዳና ሸንጎ ሊቀመንበር ሆኜ አገልግያለሁ፡፡ በመንገድ ሥራ፣ በጤና ጣቢያ ግንባታ፣ በአብያተ ክርስቲያናት ህንፃ ግንባታ፣ በትምህርት ቤት ማስፋፋት ሥራ ላደረግሁት አስተዋጽኦም ህዝቡ የቀኛዝማችነት ማዕረግ የሰጠኝ ሲሆን የልማት ስራዎቹን የረዱ የተለያዩ ተቋማትም የምስጋና የምስክር ወረቀት ሰጥተውኛል፡፡

በማህበራዊ ተሳትፎም አባል በሆንኩባቸው የተለያዩ ዕድሮች ውስጥ በኃላፊነት በመመረጥ አገልግያለሁ፡፡ ለዕድሮቹ ዕድገትም በህግ እውቀቴ ያለኝን ልምድ በማካፈል ለመርዳት ሞክሬያለሁ። የጥብቅና ሙያን መተዳደሪያዬ አድርጌ እስከ 1998 ድረስ በመስራት እኔንና ቤተሰቤን ብቻ ሳይሆን አገርና ሕዝብን ጠቅሜበታለሁ፡፡

በ1937 ዓ.ም ተመስርቶ 70 ዓመታት ባስቆጠረው ትዳራችንም 14 ልጆችን ያፈራን ሲሆን በርካታ የዘመድ ልጆችንም አሳድገናል። የልጅ ልጆችንም አይተናል፡፡ ልጆቻችን ተምረው ዶክተር፣ አካውንታንት፣ ነርስ፣ ፀሐፊ፣ ማርኬቲንግ ኦፊሰር... ሆነዋል፡፡ በህይወቴ የገጠመኝ መሪር ሀዘን ቢኖር በልጄ ቢኒያም ዘውዴ ሞት የደረሰብኝ ስቃይ ነው፡፡ በህክምና ትምህርት በዶክትሬት ለመመረቅ ሁለት ወር ሲቀረው ሚያዚያ 5 ቀን 1998 ዓ.ም በሞት ስለተለየኝ ጥልቅ ሀዘን ተሰምቶኛል፡፡

በአሁኑ ጊዜ እኔም ሆንኩ ባለቤቴ በአንፃራዊነት ጤናማ በሆነ ሁኔታ ላይ ነው የምንገኘው፡፡ ለዚህ የበቃሁትና ይህንን የታደልኩት ባለቤቴ ወ/ሮ ትክክልወርቅ ሞጆን ከመሰለች መልካም ጠባይና የዋህ ተፈጥሮ ካላት ሴት ጋር እግዚአብሔር ስላገናኘኝ ነው፡፡ 70 ዓመታት አብሮ መኖር መቻል ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው የሚገኝ ዕድል አይደለም፡፡ እኔም ኑሮዬ ተሟልቶ የመገኘቱ ምክንያት የባለቤቴ መልካም መሆን አስተዋጽኦ እንዳለበት እገነዘባለሁ፡፡ “መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት” የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በተግባር አሳይታኛለች፡፡

ከባለቤቴ ከወ/ሮ ትክክልወርቅ ሞጆ ጋር ለመንፈሳዊ ጉዞ ከአገር ውጭ ኢየሩሳሌም ቅዱስ መድኀኒዓለም ቤተክርስቲያን የሄድን ሲሆን በአገር ውስጥም በአራቱም ማዕዘን ወደተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተጉዘናል። ልጆቻችን ወዳሉበት የአሜሪካን የተለያዩ ግዛቶች በመሄድ ለመጎብኘት ዕድል አግኝተናል።

የወር ደሞዝተኛ በነበርኩበት ጊዜ ሆነ በግል ሥራም ተሰማርቼ ስሰራ በየዕለቱ የሚገኘውን ገቢ በእቅድ የመምራት ችሎታ ስለነበረኝ፤ ኑሮዬ ሳይዛባ ለዛሬ ደርሻለሁ፡፡ በትዳር አጋሬ ብቻ ሳይሆን በልጆቼም ተባርኬያለሁ፡፡ ልጆቼ አስቀይመውኝ አያውቁም፤ ልጆቻቸውም የተባረኩ እንዲሆኑላቸው እመኝላቸዋለሁ። እኔንና ቤተሰቤን ጠብቆ ለዚህ ያደረሰን እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ህዝቧንም ይባርክ!!”

ርዕሰ አንቀፅ

# እናዝናለን ... እንፅናናለን ... እንፀናለን!!

አያዩት ግፍ የለ፤
አይሰሙት ጉድ የለ!
ካራ በዕርግብ አንገት፣ ለዕርድ እየሳለ
"ሠይጣን ሰለጠነ"፣ በደም ተኳኳለ!!!
ሌላነት(Otherness) የሚሉት አዲስ ሾተል አለው
ፀረ-ሰው ለመሆን፣ ማልዶ የሞረደው፡፡
"ዕወቁኝ" ነው የሚል፣ ይህ የገዳይ ቢላ
ሌላም ቋንቋ የለው፣ ወትሮም ለሰው- በላ፡፡
(ይሄን በላዔ-ሰብ፣ ማነው ስሙ? አትበሉ
ስሙን መጥራት ለሱ፣ ነውና እኩይ ድሉ፡፡
ይሄን በላዔ - ሰብ፣ ምን ዓለመ? አትበሉ፡፡
ከጀርባው ያለው ኃይል፣ ያው ደሞ እንዳመሉ
እኔ ነኝ ይለናል፣ ሲሞላለት ውሉ!)

*     *     *

አወይ ያገሬ ልጅ!
ወገኔማ ምን ያርግ፣ አደለም በውዱ
ግድ ሆኖበት እንጂ ነጥፎበት ማዕዱ
ቀን ቢወጣ ብሎ፣ ካገር መሰደዱ፡
ነው እንጂ እንዳቅሙ፣ ጎጆ እስከሚሠራ
የጎሸ ቀን በስሎ፣ ጠሎ እስከሚጠራ
መቼ ጥሞ ያቃል፣ የስደት እንጀራ?!
ወዮ የእናቴ ልጅ! ያ ሁሉ መከራ
ጉሮሮውን ሲያስብ አንገቱን ለካራ!!

*     *     *

ያንድ ቀን አይደለም፣ የጨካኝ ጉድ ጓዙ
ቀበቶን ማጥበቅ ነው፣ የቆራጥ ሰው ደርዙ!
የዚህን ሁሉ ግፍ
የመከራ ምዕራፍ
ገፆቹን ለማጠፍ፤
ራስ በራስ ቆመን፣ ጨክነን በዕርጋታ
ችግሩን ከሥሩ፣ የነቀልን ለታ
ሞት እዬዬ ይላል፣ ሆኖ በ'ኛ ቦታ!!
ከመቀደም መማር፣ ትልቅ ዋጋ እንዳለው
መቼም ቀን ወደፊት፣ አለመቀደም ነው!!

*(በስደት ላይ ሳሉ ልጆቻቸው በአረመኔዎች ለተጨፈጨፉባቸው ወላጆችና በሐዘን ላይ ላለው የኢትዮጵያ ህዝብ)*

*(ሚያዚያ 13 ቀን 2007)*

# "እንዳስጨነቋቸው መጠን እንዲሁ በዙ፣ እጅግም ጸኑ" ዘጸ1:12

ቅድስት ቤተክርስቲያን በሊቢያ ለተሰውት ወንድሞቻችን በቅዱስ ሲኖዶስ ደረጃ በቀኖናዋ የምትሰጠውን ስያሜና ክብር ስንጠባበቅ ነበር። ባለፈው ማክሰኞ ማታ ቤተ ክርስቲያኗ በEBC በሰጠችው መግለጫ፤ "ስለ ሃይማኖት የተጋደሉ መስተጋድላን" ብላቸዋለች።

በዘመናችን የሰማዕትነት ወግ ያሳዩንን የሃይማኖት ጀግኖች፤ ሠዓሊና የግራፊክስ ባለሙያ ወንድማችን ዘሪሁን ገ/ወልድ፤ በኢትዮጵያዊ የአሳሳል ዘዬ "በከመ ተወክፎሙ እግዚእነ ለሰማዕታተ ሊቢያ ዘተመትሩ በእንተ ስሙ" (ስለስሙ የተገደሉትን የሊቢያ ሰማዕታት ጌታችን እንደተቀበላቸው) የሚያሳይ ስዕል አዘጋጅቶልናል፡፡ ከቁጭታችን የተነሳ አሰቃቂ የሆነውን የሰማዕታቱን ቪዲዮና ፎቶዎች ፖስት ከማድረግ ይልቅ ይህንን ምስል መጠቀም እንችላለን። በደም የታጠቡት ምስሎች መሰራጨታቸው ለገዳዮቹ የፈለጉትን የማስታወቂያ ሥራ የሚሰራ ሲሆን ለሰማዕታቱ ቤተሰቦችና የቅርብ ወዳጆች ግን ከፍተኛ ሰቀቀን መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። ሰሞኑን ሁለቱ ሰማዕታት ከኤርትራ ናቸው የሚል ዜና ተሰምቷል፡፡ ከኤርትራ ቀርቶ ከየትም ቢሆኑ ቤተክርስቲያን ምስክርነታቸውን እንጂ ፓስፖርታቸውን አትመለከትም፡፡ ቤተክርስቲያን በስንክሳር አምነው ሳይጠመቁ ለሰማዕትነት የበቁና በደማቸው የተጠመቁ ብዙ ሰማዕታት አሏት፡፡

የሰማዕታቱ ደምና መከራ ቅድስት ቤተክርስቲያናችንን ወደ መንፈሳዊ ተጋድሎ ዘመንዋ የሚመልሳትና አንድ የሚያደርጋት ይሁንልን፡፡ ከሃይማኖት የወጡ በምግባርም ያፈነገጡ፣ እረኛን በማጣት የተበተኑ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ልጆችንም የሰማዕታቱን ደም ምክንያት አድርጎ ወደ በረቱ ይመልስልን!

*ተመስገን ዘገየ (አዲስ አበባ)*

# እግዜር ያተረፋት ነፍስ ምስክርነት

ከማልታ ባገኘሁት መረጃ፤ በቀደም ከተሰውት ወንድሞቻችን ጋር የነበረ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት አምልጦ ትሪፖሊ የገባ ወንድም አግኝቼ ነበር፡፡ እርሱ እንደነገረኝ፤ "በአጅዛቢያና ቤንጋዚ መንገድ ላይ የአይሲስ አራጆች የሊቢያ መንግሥት ወታደሮችን ዩኒፎርም ለብሰው በዚያ የሚያልፉትን ለመያዝ ይጠብቃሉ፡፡

በአካባቢው ወደ ትሪፖሊ የሚጓዙ መንገደኞችን ሲያገኙ ይይዛሉ፡፡ ሱዳኖችና ሶማሊያውያን ሙስሊሞች ናቸው ብለው ስለሚያስቡ ወዲያው እንዲሄዱ ይለቋቸዋል። ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያንን ግን ለብቻ ይይዛሉ፡፡ ከዚያም ሙስሊሞችን ለብቻ፣ ክርስቲያኖችን ለብቻ ያሰልፏቸዋል፡፡ በመቀጠልም ክርስቲያኖችን በኮንቴይነር ውስጥ ከትተው ወዳልታወቀ ስፍራ ይወስዷቸዋል። ምግብ የሚሰጧቸው በየሦስት ቀን ነው፡፡ ሙስሊሞችን ደግሞ ይለቋቸዋል፡፡

በቀደም እለት አይሲስ በባህር ዳርቻ የሰዋቸው ክርስቲያኖች የመስቀል ማህተብ የነበረባቸውን መርጦ ነው፡፡ እነርሱን በተለየ ኮንቴይነር አስቀምጧቸው ነበር።" ይሄንን መረጃ የነገረኝ ሰው ሊገደሉ ተመርጠው ከተለዩት ወገን ነበረ፡፡ ሌሎች በኮንቴይነር ያስቀመጣቸው ክርስቲያኖችም አሉ። ምናልባት ከዚህ የከፋ ዜና እንሰማ ይሆናል። አምላክ ይጠብቀን።

አሁንም የአይሲስ አራጆች የመንግሥት ወታደሮችን ልብስ ለብሰው ሌሎች ስደተኞችን እየያዙ ነው፡፡ይሄ መረጃውን ያደረሰኝ ሰው ሊያመልጥ የቻለው ሌሎች ክርስቲያኖችን በጨለማ ወደ ኮንቴይነሩ ለማስገባት ኮንቴይነሩን በከፈቱበት ጊዜ ነው፡፡ የተወሰኑ ተያዦች አምልጠው ነበር። አንዳንዶች ተያዙ፡፡ ሦስቱ ግን አመለጡ። ሁለቱ የት እንደደረሱ አያውቅም፤ እርሱ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት አምልጦ ትሪፖሊ ገብቷል፡፡

እባካችሁ ሰሞኑን ለመጓዝ የተነሱት ቢያንስ ለጊዜው ይታገሱ፡፡ ሱዳን ያሉትም ከሱዳን አይውጡ። መንገዱ በአይሲስ አራጆች ተይዟል። ለማታለልም የመንግሥት ወታደሮችን ልብስ ለብሰው ድንበር ጠባቂ ይመስላሉ፡፡

እግዚአብሔር በእጃቸው የተያዙትን እንዲታደግ እንፀልይ!!

*(ዲ/ን ዳንኤል ክብረት ከፌስ ቡክ የተገኘ)*


አዲስ አድማስ

ሥራ አስኪያጅ:- ገነት ጎሳዬ
(ልደታ ክ/ከ ቀበሌ 04/06 የቤ.ቁ.581) ስልክ 0911-936787
ዋና አዘጋጅ:- ነቢይ መኮንን
(ቂ/ክ/ከ ቀበሌ 08/09 የቤት.ቁ.213)
ም/ዋና አዘጋጅ:- ኢዮብ ካሣ
ከፍተኛ አዘጋጅ:- ሰለሞን ገ/እግዚአብሔር
አዘጋጅ:- ኤልሳቤት ዕቁባይ

ታኅሣሥ 29 ቀን 1992 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡ ዘወትር ቅዳሜ የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ
አሣታሚ ፡- አድማስ አድቨርታይዚንግ ኃ.የተ.የግ.ማ.
አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17 / የቤት ቁ.984

ከፍተኛ ሪፖርተሮች:- መንግስቱ አበበ፣ ግሩም ሠይፉ፣
አበባየሁ ገበያው ፣ መታሰቢያ ካሳዬ፣ናፍቆት ዮሴፍ፣ አለማየሁ አንበሴ
ሌይ አውት ዲዛይነር :- ኮከ አሰፋ፣ ንግሥት ብርሃነ
አርቲስት :- ሠርፀድንግል ጣሰው
ሽያጭና ስርጭት :- ሰለሞን ካሣ
ፎቶግራፈር :- አንተነህ አክሊሉ
ዌብፔጅ :- አስቴር ጎሳዬ
ኮምፒውተር ጽሑፍ :- የወብዳር ካሣ፣ ሃና ገ/ሚካኤል

አድራሻ:- ካዛንችስ፤ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ገባ ብሎ፣ ከጤና ጣቢያው ጀርባ
ቂርቆስ ክ/ከ ቀበሌ 31 ፤ የቤት ቁ.376
ስልክ፡- 0115-155-222/ 0115-153-660 ሞባይል፡- 0921-622-040/
0911-201-357 / 0935-98-74-44 / 0118699024
ፋክስ፡- 0115-547373 ፖ.ሳ.ቁ 12324
E-mail :- admassadvert@gmail.com/ addisadmass@ethionet.et
website www.addisadmassnews.com



ኤፍሬም እንዳለ

# ጽናቱን ይስጠን...



እንዴት ሰነበታችሁሳ!

*"እኔም ተመለስሁ፣ ከፀሐይ በታችም የሚደረገውን ግፍ ሁሉ አየሁ፡ እነሆም የተገፉት ሰዎች እንባ ነበረ፣ የሚያጽናናቸውም አልነበረም፣ በሚገፉአቸውም እጅ ኃይል ነበረ፣ እነርሱን ግን የሚያጽናናቸው አልነበረም፣"*

ይላል መጽሐፈ መክብብ:: የተገፉትን እንባ ያድርቅልን::

*ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ*
*ከዛ ነው አፈሩ የእማማ ያባባ*
*ስሳብ እሄዳለሁ ቢሰበርም እግሬ*
*አለብኝ ቀጠሮ ከትውልድ አገሬ*
*አለብኝ ቀጠሮ*
*ከትውልድ አገሬ ካሳደገኝ ጓሮ::*

ብሎ ነበር ገብረ ክርስቶስ ደስታ:: ከትውልድ አገራቸው ጋር 'ቀጠሮ ያላቸው' ሚሊዮኖች ወገኖቻችን በየአገሩ እየተንከራተቱ ነው:: ማንም ከማንም የማይለይባት፣ ከልጅ ልጅ የማይመረጥባት የተስፋይቱ ምድር ከሆነች አገራቸው ጋር ቀጠሮ ያለባቸው ብዙዎች አሉ::

ከትውልድ አገራቸው ጋር የነበራቸው ቀጠሮ በአጭሩ የተቀጨባቸው ወገኖቻችንን እግዚአብሔር በሰማይ ቤት ነፍሳቸውን በገነት ያኑርልን::

ይሄ ሰሞን ለኢትዮጵያውያን የመከራ ሰሞን ነው:: በተከታታይ ቀናት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ባሉ ወገኖቻችን ላይ የደረሱ ሰቆቃዎች ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው እንኳን ሊቀበላቸው፣ ይሆናሉ ብሎ የሚያስባቸው አይደሉም:: በሌላ በኩል የሰው ልጅ እውነትም ከእንስሳት ሁሉ በባሰ ጨካኝ ሊሆን እንደሚችል ማሳያ ናቸው:: በሊቢያ ከሰው ጋር ሊመደቡ የማይችሉ አውሬዎች በንጹሀን ወገኖቻችን ላይ የፈጸሙት ጭካኔ በምን አይነት ቃላት መግለጽ እንደሚቻል አንድዬ ይወቀው:: የክፋትም፡ የጨካኝነትም፣ የአውሬነትም፣ የነውረኝነትም የሆኑ መስመሮች አሉ:: የእነኚህኞቹ ግን በምን አይነት መለኪያ ላይ የሚቀመጥ አይደለም::

*ድንግል አገሬ ሆይ ጥንተ ደናግሎ*
*ሕፃናቱም ታርደው ያንቺም ልብ ቆስሎ*
*ልጅሽ ተሰደደ አንቺን ተከትሎ*
*የህፃናቱን ደም አዘከሪ ኩሎ፤*

ይላል ዮሐንስ አድማሱ::

በሀዘን ስሜትም ውስጥ ሆነን ግን ጊዜው ራሳችንን መልሶ መመልከቻ መሆን አለበት:: ጓዳ ጎድጓዳችንን የምንፈትሽበት ጊዜ ነው:: ወገኖቻችንን "ለምን ይሰደዳሉ?" የሚል ጥያቄ ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል:: ለምን እንደሚሰደዱ ግልጽ ነውና::

ከሳውዲ ዓረቢያ ከዛ ሁሉ ሰቆቃ በኋላ ወደ አገር ቤት ተመልሰው የነበሩ ብዙዎቹ እንደገና በህገ ወጥና እጅግ አደገኛ በሆኑ መንገዶች ለመሄድ የሚሞክሩት ለምን እንደሆነ እውነቱን ፊት ለፊት መጋፈጥ አለብን። ተስፋ ቢያጡ፣ የደከሙ እናት አባቶቻቸውን መደገፍ ቢያቅታቸው፣ ቤተሰቦቻቸውን አብልቶ ማሳደር ቢያቅታቸው፣ መልካም ኑሮ የመኖር ህልማቸውን ለማሳካት መንገዱ ሁሉ እሾህና ጋሬጣ ቢሆንባቸው... መአት ምክንያቶች መደርደር ይቻላል::

በአሁኑ ጊዜ ወገኖቻችን በቀይ ባህርና በሜዲቴራንያን ውሀ ስለመበላታቸው፣ በየበረሀው የአውሬና የወሮበላ ሲሳይ ስለመሆናቸው እየሰማን፣ በራሳቸውም ይሁን በአሠሪዎቻቸው ከፎቅ እየተወረወሩ ሬሳቸው አስፋልት ላይ ተዘርግቶ በማህበራዊ ድረ ገፆች እያየን፣ በየመንና በሌሎችም ስፍራዎች የድረሱልን ጥሪያቸውን እየሰማን ባለንበት ወቅት... የስደትን አስከፊነት የማያውቅ ይኖራል ማለት አስቸጋሪ ይሆናል:: ችግሩ በቀጥታም በተዘዋዋሪም የአብዛኛውን ህዝብ በር አንኳኩቷልና!

የደረስንበት ደረጃ ስለ ስደት አስከፊነት ለበርካታ ዓመታት ሲሰጡ የነበሩ ትንታኔዎችን በመድገም ጊዜ የምናባክንበት አይደለም:: ይልቁንም ይህን ለመገመት እንኳን አስቸጋሪ ሆኖ የመጣውን መጠነ ሰፊ ስደት ለማቆም ምን መደረግ እንዳለበት መምከር ነው ያለብን::

የኢትዮጵያ ልጆች ሰቆቃ የዓለም ቴሌቪዥን ጣቢያዎች የምሽት ዓበይት ዜናዎች ማጀቢያ መሆኑ መቆም አለበት:: ግን በፉከራ የሚቆም ነገር አይደለም... በ"በለው በለውና አሳጣው መድረሻ..." የሚለወጥ ነገር አይኖርም::

ይልቁንም ግን ለምንድነው በዚሁ ሁሉ ስቃይ መሀል ወጣቱም፣ አዛውንቱም የሚተመው ብለን እውነት፣ እውነቱን የማየት ድፍረት ያስፈልጋል:: ከፖለቲካ የነጻ፣ ከዘር የነጻ፣ ከኃይማኖት የነፃ፣ ከበቀልና ከቁርሾ የነፃ፣ ከጥላቻ የነፃ አተያይ ያስፈልገናል:: በቃላትና በመዝሙር፣ በትልልቅ ባንዲራና በአሼሼ ገዳሜ እየሸፋፈንን የምናልፋቸውን ነገሮች አደባባይ አውጥተን እውነቱን የማየት ድፍረት ያስፈልገናል::

አንዲት ከሳውዲ ዐረቢያ ተመልሳ መጥታ የነበረች ወጣት እንደገና እሄዳለሁ ስትል "እዛ ሰዉ ሲሞት እያየሽ እንዴት እሄዳለሁ ትያለሽ?" ስትባል የመለሰችው መልስ አስደንጋጭም ምናልባትም የብዙዎቹን ድምዳሜ የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይችላል። "እዚህም እኮ ሞት አለ..." ነው ያለችው። አገር እንዲህ ማለት ሲጀምር በእጅግም አስቸጋሪ ዘመን ውስጥ መሆናችንን ማሳያ ነው::

እንደሚባለው ሁሉ እውን የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ለሁሉም አለ ወይ ብለን መጠየቅ አለብን:: እውን ከፖለቲካ አመለካከት ሙሉ ለሙሉ የነጻና 'የተመቻቸ' የሥራ ሁኔታ በአገሪቱ በሙሉ አለ ወይ ብለን መጠየቅ አለብን:: እውን ከዘርና ከጎሳ ጠባብ አመለካከት ሙሉ ለሙሉ የነጻና 'የተመቻቸ' የሥራ ሁኔታ በአገሪቱ በሙሉ አለ ወይ ብለን መጠየቅ አለብን::

ሰፋ ካለው ዘር የጠበበ በመንደር መሰባሰብ እየተለመደ ባለበት ጊዜ፣ ጠባብነት ወደ አምቻና ጋብቻ እየወረደ ባለበት ጊዜ እውን ከአድልዎ የነጻና 'የተመቻቸ' የሥራ ሁኔታ አለ ወይ ብለን መጠየቅ አለብን:: የኮሌጅ ዲግሪያቸውን ይዘው ሥራ ለማግኘት አራትና አምስት ዓመታት የሚንከራተቱ በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ባሉበት ሁኔታ እንደሚባለው እውን ለሁሉም እኩል የሆነና 'የተመቻቸ' የሥራ ሁኔታ አለ ወይ ብለን መጠየቅ አለብን::

*መከራ ተረግዞ ተወልዶ ችግር*
*ሥቃይ ተሞሽራ ሲዘፈን በአገር*
*ኃዘን ስትዘፍን አታሞ ስትመታ*
*ድህነት ሲሸልል እየገፋ እምቢልታ*
*ረሀብ ሲያቅራራ በጣለው ሰለባ*
*ቀጠና ደረሰ ድምጹ እያስተጋባ*
*ቡትትም አጊጣ ከድሪቶ ጋራ*
*ዝተትና ማቅም ሆነው በየተራ*
*መጡ ከእኔ ዘንዳ አብረውኝ ሊኖሩ*
*ተስማምተው ደረሱ እየተባባሩ*

ብሏል ዮሐንስ አድማሱ:: እንዲህ አይነት እንጉርጉሮ የማንሰማበት፣ ረሃብ የማያቅራራበት፣ ሥቃይ የማትሞሽርበት፣ ድህነት የማይሸልልበት ዘመን ማምጣት የምንችለው እኛ ብቻ ነን:: ለዚህ ደግሞ ልባችንን ክፍትና ንጹህ አድርገን ራሳችንን መፈተሽ አለብን:: መለወጥ ያለብንን ለውጠን፣ መያዝ ያለብንን ይዘን ለመቀጠል በኢትዮጵያ ስም መማማል አለብን::

*እንዴት ነው ነገሩ?*
*ብንሄድ ብንሄድ ጎዳናው አያልቅም*
*ሸቅብ ብናንጋጥጥ ጀንበር አትጠልቅም*
*ጊዜ ቆሟል መሰል አይነቃነቅም*
*ጋሪያችን ይሮጣል እኛ አንንቀሳቀቅም*
*እንዴት ነው ነገሩ?*

ብሏል ኑረዲን ኢሳ በአንድ ግጥሙ:: ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ ችግሮቻችንን መልካቸው እየቀየሩ ሲሄዱብን... "እንዴት ነው ነገሩ?" እያልን ነው:: እንደ ትናንትና እንደ ትናንት ወዲያው ሁሉ ዛሬም ስደታችን ሲበዛ፣ ፍልሰታችን ሲበዛ፣ ችግሮቻችን ካሉበት ፈቅ ሳይሉ ሲቀሩ..."ጊዜ ቆሟል መሰል..." እያልን ነው::

ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ የነበረው ግፍ በሀያኛው ክፍለ ዘመን ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ነው:: ድፍን አፍሪካ ለመብታቸው ሲታገሉላቸው የኖሩ ህዝቦች፣ በተለይም ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ በፖለቲካውም ሆነ በስፖርቱ ሽንጧን ገትራ ስትሟገትላቸው የነበሩ ህዝቦች የጭካኔ ስለታቸውን ውለታ በዋለችላቸው አገር ህዝቦች ላይ ሲሰነዝሩ እጅግ፣ እጅግ አሳፋሪና ድፍን ደቡብ አፍሪካን አንገት ማስደፋት የሚገባው ድርጊት ነው::

ጥቃቶቹ ገና እንደተጀመሩ መቆጣጠር እየተቻለ በአገሪቱ ወሳኝ ሰዎች በነበረ ዳተኝነት ከሚገባው በላይ ጥፋት ደርሷል:: እንደእነ ናይጄርያ ጥግ ባንሄድም የአገሪቱ መንግሥት በግዛቱ ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ የሌሎች አገሮች ስደተኞች ደህንነት የመጠበቅ ዓለም አቀፍ ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለበት ጮክ ብለን መናገር ይገባን ነበር::

ሪቻርድ ዳውደን የተባለ እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ ከሰባት ዓመታት ገደማ በፊት ስለ አፍሪካ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ስለ ደቡብ አፍሪካ ሲያሰፍር... *"ደቡብ አፍሪካ እንደ ሌላ የአፍሪካ ሀገር አይደለችም፣..."* ይልና *"...ደቡብ አፍሪካ የሰው ልጅን ህልሞች የተሸከመች መሆኗ አይገርምም..."* ሲል ያንቆለጳጵሳታል::

ይህ እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ የሰሞኑን ድርጊት ሲያይ ምን ብሎ ይሆን! እኛ የምንለው ግን ግልጽ ነው..."የሰው ልጅን ህልሞች የተሸከመች..." ባላት አገር ያየነው የሰው ልጅን የጭካኔ ጥግ ነው!

ስለ አገራችን ያለን አመለካከት መጥራት አለበት። የራሱን ቤተሰብ እስከ አያቱ እንኳን መጥራት የማይችለው ሁሉ የሺዎች ዘመን ታሪካችንን ለማጠልሸት የሚያደርገውን እኩይ ተግባር በማስረጃ ጭጭ ማሰኘት መቻል አለብን::

ይቺ አገር የሉሲ አገር ናት፣ የቅዱስ ያሬድ አገር ናት፣ የዘርአያዕቆብ አገር ናት፣ አክሱምን ያቆሙ፣ ላሊበላን የፈለፈሉ ጠቢባን አገር ናት:: ይቺ አገር አፍሪካ ከእንቅልፏ ሳትነሳ ነጭ ወራሪዎችን ምሳቸውን ሰጥታ የጥቁር ህዝብ ምሳሌ የሆነች አገር ነች::

አንድ ነገር አለ:: እነ እከሌ አይወዱንም ምናምን ስንል ዝም ብሎ የሚመጣ ነገር አይደለም:: መታበይም አይደለም:: የዚችን አገር ታሪክ በደንብ ላስተዋለ በእርግጥም ጠላቶቿ በርካታ መሆናቸውን ይገነዘባል:: ጊዜ የሚጠብቁላት መአት እንዳሉ ምስጢርም ሊሆን አይችልም:: እነኚህ 'ቱባ፣ ቱባ' መገናኛ ብዙኃን ስለ አገራችን ባወሩ ጊዜ ሁሉ የቃላት አደራደራቸውንና አጽንኦት የሚሰጡበትን ነጥብ ነገሬ ብሎ ማየት ይበቃል::

እንደምንም ብለው የአገራችንን ገጽታ ምን ጊዜም ከበርካታ አሥርት ዓመታት በፊት ከነበረው ረሀብ ጋር በማስተሳሰር ትልቁን ስዕል ለመሸፈን ይሞክራሉ:: አዲስ አበባ የባቡር ሀዲድ እየተዘረጋ መሆኑን በሚዘግቡበት ዜና ላይ የወሎ ድርቅን ምስሎች የሚደረድሩት ዝም ብለው አይደለም። በዓለም ላይ በየዘመናቱ ሚለዮኖች በረሀብ የረገፉባቸው አገራት እያሉ አገራችንን በመዝገበ ቃላታቸው 'የረሀብ ምሳሌ' ማድረጋቸው ዝም ብለው አይደለም:: አወሮፓም በተራበ ጊዜ እኛም እኮ ለተራቡ አውሮፓውያን የአቅማችንን እርዳታ ልከናል:: ምነው ወደኋላ ሄደው እነሱም እንደ እኛ

ጽናት ወደ ገፅ 9 ዞሯል


# VACANCY ANNOUNCEMENT

I. Sr. Automotive Mechanic

| | | |
|---|---|---|
| Qualification | : | Diploma in Automotive Technology - level IV |
| Experience | : | 5+ years |
| Requirement | : | 2 (Two) |

&

II. Sr. Auto-Electrician

| | | |
|---|---|---|
| Qualification | : | Diploma in Auto- Electrician – level IV |
| Experience | : | 5+ years |
| Requirement | : | 2 (Two) |

&

III. Spare Parts Assistant Manager

| | | |
|---|---|---|
| Qualification | : | Degree in Automotive Technology |
| Experience | : | Fresh but quick to learn OR |
| Experience | : | Diploma in Automotive Technology 5 years in Spare Parts |
| FOR ABOVE | : | Place of work : Addis Ababa<br>Employment : Permanent<br>Salary : Negotiable |

Interested applicants can submit their CVs & non returnable photocopies of their credentials in person or as per the under communication means within 10 working days from the date of issuance of the Vacancy.

Address: HR Office
PAUL RIES & SONS (ETH) LTD.,
Dej, Ummar Street (Sumale Terra)
or by mail P.O.box 3659
or e-mail at yeshimebet.z@paulriesethiopia.com
or yeshiyazb@yahoo.com

# የአዲግራቱ የምሽት ፓርቲ ያስከተለው ጣጣ!

(ከዘሥሩግ ከጫናዱግ)

አዲግራት በቀድሞ አጠራሩ የዐጋመ አውራጃ፣ በአሁኑ ደግሞ የምሥራቅ ትግራይ ዞን ዋና ከተማ ናት፡፡ አዲግራት ከተራራ ሥር የተመሠረተችና እንደወርቅና ዕንቁ የምታበራ ከተማ ናት፡፡ አዲ ግራት ማለት የእርሻ ቦታ እንደማለት ነው፡፡ ነዋሪዎችም ከሁሉም ሰው ጋር በቀላሉ የሚግባቡ፣ ፈጣኖችና እንግዳ አክባሪዎች፣ ለእውነትና ለሀቅ የሚሞቱ ናቸው፡፡

ለሁልጊዜም ከልቤ የማትጠፋውንና ስሟ ሲጠራ በፍቅርዋና በውበትዋ የምትማርከኝን ይህችን ነፋሻማና ለኑሮ ተስማሚ የሆነችውን ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት በ1973 ዓ.ም ነው፡፡ ሞቅና ደመቅ ወደአለችው ወደ አዲግራት ከተማ የገባሁት በህዳር ወር መጀመሪያ ላይ ሲሆን አዲግራት በገባሁ በሦስተኛው ቀን የጫናዱግን አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛና 12ኛ ክፍል መምህር ሆኜ እንዳስተምር ተነገረኝና ሥራዬን ጀመርኩ፡፡ በወቅቱ የነበረው የቀበሌ አመራርም የምኖርበት የቆጠባ ቤት ሰጠኝ፡፡ የእኔ ቤት በርካታ የቆጠባ ቤቶችና ነዋሪዎች በሚኖሩበት አንድ ግቢ ውስጥ ሲሆን ምንም ዓይነት አጥር በሌለው ግቢ ውስጥ ልብስ ታጥቦና ውጭ ተሰጥቶ ቢውል ቢያድርና ወር ሙሉ ቢቀመጥ የሚሰርቀው ምንም ዓይነት ሌባ አለመኖሩ ሁልጊዜ ሲደንቀኝ ይኖራል፡፡

የከተማዋን ኑሮ ስለማመድ "ባላምባራስ" የሚለው ቃል እየተደጋገመ ሲጠራ ሰማሁ፡፡ ሕዝቡ ባላምባራስ ሐድጉ፣ ባላምባራስ ሥዩም፣ ባላምባራስ አሰፋ፣ ባላምባራስ ዋሴ... እያለ ሲናገር አንዱን የአዲግራት ተወላጅ መምህር፤ "አዲግራት የባላምባራሶች ሀገር ናት እንዴ? ባላምባራሶች ለምን በዙ? አልኩት"

እርሱም፤

"እንዴ አዲግራትኮ የራሶችና የደጃዝማቾችም ሀገር ናት፤ እነራስ ስብሐት እነ ..." እያለ ይደረድርልኝ ጀመር፡፡ ቀጠለና፤ እንዳልከው ባላምባራሶች ብዙ ናቸው አንድ ወቅት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ አሥመራ ሲሄዱ አዲግራት አርፈው ነበር፡፡ ያገሩ ባላባት ወዲ ሰባ ጋዲስ ይባላል፡፡ በአጠራሩም ገንታ አፈሹም ይባላል እናም ንጉሡ አዲግራት እንደደረሱ ለበርካታ ሰዎች የባለምባራስነት ማዕረግ ሰጥተዋል" አለኝ፡፡ ያ ጓደኛየ ቀጠለና፤ "ባላምባራስ ዋሴ ግን የአዲግራት ተወላጅ ሳይሆኑ ጎጃሜ ናቸው" አለ፡፡

"ጎጃሜው እንዴት እዚህ አገር መጥተው ኖሩ? እንዴትስ ባላምባራስ ተባሉ?" አልኩት

"አዲግራትኮ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀገር ናት" አለ፡፡

ሁለት ወር እንደሞላኝ የገና በዓል ደረሰ፡፡ እኔ ደግሞ በልማዴ የገና በዓልን የማከብረው ሌሊት ቤተክርስቲያን አድሬ በማስቀደስና ከቤቴ ውስጥ በመዝናናት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ወደ እንዳ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ሄጄ ለማደር ሐሳቡ ነበረኝ፡፡ ከመኻል የጫናዱግ ሁለተኛ ደረጃ የስፖርት መምህር ክንፈ አበራ፤ "ዘሥሩግ! የተወሰንን ሰዎች ፓርቲ አዘጋጅተን የገናን በዓል በኢትዮጵያ ሆቴል ተሰባስበን ለማክበር ስለአሰብን አንተንም ጋብዘንሃል" ይለኛል፡፡

"እኔ እንኳን እንደ ቂርቆስ ሄጄ ለማደር ነው የፈለግሁት" ስለው

"ቦታው ላንተ ይርቅሃል ደግሞ ገና እንግዳ ስለሆንክ አይመችም፡፡ ከእኛ ጋር ስትጫወት ብታድር ይሻላል፡፡ መዋጮው 50 ብር ነው፡፡ ብሩን እኔ ከፍየልሃለው" አለኝ፡፡

"የምሽት ፓርቲ አዘጋጅተናል ነው የምትለኝ?" እኔኮ ዳንስ አልችልም? አልኩት፡፡

"እንዴ? እንዴት የአዲስ አበባ ልጅ ሆነህ ዳንስ አልችልም ትላለህ?" አለና ቀለደብኝ፡፡ በፓርቲ ምሽቱ ላይ የጫናዱግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሒሳብ መምህር ኩምሳ፣ የባንክ ቤት ሠራተኛው ወንድወሰን፣ የግብርና ሠራተኛው ሐሰንና የኢትዮጵያ ሆቴል ባለቤት ፀሐየ እንዳሉበት ነገረኝ፡፡ በአጠቃላይ በፓርቲ ምሽቱ ላይ 6 ሰዎች እንደምንሳተፍ ነገረኝና በገና ዋዜማ ከምሽቱ 4 ሰዓት ጀምሮ በከፍተኛ የሙዚቃ ቅንብር ፓርቲው ተጀመረ፡፡ ስድስታችንም በቦታው ተገኘን፡፡ መጠጥ እየቀማመስን ለራት ስንዘጋጅ በአካል የማላውቃቸውና በአገር ባህል አለባበስ ያሸበረቁ 6 ልጃገረዶች ወደ ፓርቲው አዳራሽ ገቡ፡፡ ከእኔ በስተቀር ሌሎቹ ለካ የሴት ጓደኞቻቸውን አዘጋጅተው ጠርተው ኖረዋል፡፡ እያንዳንዱ ከአዘጋጀው የሴት ጓደኛው ጋር እየተነሳ ራት ወደተዘጋጀበት ቦታ ሲሄድ፣ ክንፈ ቀልጠፍ አለና የአንዷን ልጃገረድ እጅ ይዞ ወደእኔ መጣና "ተዋወቃት፤ የዛሬ የገና ስጦታህ ይህች ናት" አለኝ፡፡ ልጅቱ አጠር ከማለቷ በስተቀር በጣም ታምራለች፤ የጠይም ቆንጆ ናት፡፡

"እቴማንች እባላለሁ" ብላ ተዋወቀችኝ፡፡ እቴማንች በጣም ዓይናፋር ናት፡፡ በሐሰን የሴት ጓደኛ በለምለም ብትመረጥልኝም፣ እኔ በውበትዋና በፍቅርዋ ልማረክ አልቻልኩም፡፡ እንዲሁ ለስሜቴ እህቴ መሰለችኝ፡፡ ከበላን በኋላ አብረን ተቃቅፈን ብንደንስም ስሜቴን አልማረከችውም፡፡ ይልቁንም ልቤ በጊዜው ከተዋወቅኋት ከርግበ ጋር ስለነበር እቴማንችን አቅፌ ርግበ ነበረች ትዝ የምትለኝ፡፡

"ያገመ ኮረዳ ያፈሹም የገንታ፣
የምታስደነግጥ በዓይን ብሌን ገብታ፡፡
ዓይኗ ተወርዋሪ፣
ዓይኗ ተናጋሪ፣
ጽጌረዳ ከንፈር
የጣዝማ ንጣሪ ..." እያልኩ

ከአደነቅኋትና በጊዜው ከአፈቀርኳት ከርግበ ጋር ሌሊቱን ባሳልፈው እመኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ኃይለኛ የሆነ የቤተሰብ ቁጥጥር ስለነበረባት አዳር ቀርቶ ቀን ከእርሷ ጋር ለመገናኘት በጣም ከባድ ነበር፡፡ አንድ ዕለት ግሪክ ከመሰለችውና ዓይኗ እንደ ኮከብ ከሚያበራው ከርግበ ጋር ተገናኝተን ሽንቅጥ ወገቧን እቅፍ አድርጌ፣ ጡቷ ደረቴን እየወጋው ስደባብሳት

ምሽት ወደ ገፅ 20 ዞሯል

## ምሳሌያዊ አባባል

### የፐርሺያ ምሳሌያዊ አባባል

- ያለ ሰዓቱ ከተበረከተ ወርቅ፣ በሰዓቱ የተወረወረ ድንጋይ ይሻላል፡፡
- ችግር አንበሳን ቀበሮ ያደርጋል፡፡
- የተፈታ እንቆቅልሽ ቀላል ይመስላል፡፡
- ሁሉም ሰው የእንጀራው ንጉስ ነው፡፡
- ብልህ ሰው በራሱ ቀልድ መሳቅ ይችላል፡፡
- የበዛ ሙገሳ ከስድብ ይቆጠራል፡፡
- ገነት ያለው ከእናት እግር ሥር ነው፡፡
- ከባዕድ ጋር ኤደን ውስጥ ከመቀመጥ ከወዳጆቹ ጋር ወህኒ ቤት መታሰር ይሻላል፡፡
- ጓደኛና ግጥም አንድ ናቸው፡፡
- ህፃናት የገነት ድልድይ ናቸው፡፡
- ከጅል ጓደኛ ብልህ ጠላት ይሻላል፡፡
- ደምን በደም ማጠብ አይቻልም፡፡
- ጠብታ ሲጠራቀም ባህር ይሆናል፡፡
- እስከ ንጋት ድረስ የሚበራ ላምባ የለም፡፡
- ዓይነ ስውር በመላጣ ይስቃል፡፡
- ልብ ለሌላቸው ልብህን አትስጥ፡፡
- ድመት ልጆቿን መብላት ሲያምራት አይጦች ይመስላሉ ትላለች፡፡
- ጥሩ ዓመት በፀደይ ያስታውቃል፡፡
- ሁለት አዋላጆች የህፃን አንገት ይቀጫሉ፡፡



# የተገፉትን ማን ይጠይቅልን?

ባዩልኝ አያሌው

እኛ ላይ የሆነውንና እየሆነ ያለውን ሁሉ ሳስብ በታላቁ መጽሐፍ የሠፈረን አንድ አስገራሚ ታሪክ አስታወስኩ፡፡ ይኸውም ሙሴና እግዚአብሔር ስለእስራኤል ልጆች ያደረጉት ምልልስ ነው። በሙሴ እየተመሩ ከግብጽ የዘመናት ባርነት ነጻ የወጡት እስራኤላውያን በብዙ ምህረት ታድጎ ያወጣቸውን አምላካቸውን አብዝተው በደሉ፡፡ በዚህ የተቆጣው እግዚአብሔርም መሪያቸውን ሙሴን "ይህንን ህዝብ ላጠፋው ነው" አለው። ሙሴ ግን በታላቅ ቁጣ የተነሳውን አምላኩን እንዲህ አለው፤ "የህዝቡን ሐጢያት ይቅር በል፤ ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍ እባክህ ደምስሰኝ" ዘይገርም! ስለሚመራው ህዝብ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ታላቅ መሪ፡፡

ይህች ሀገርና ህዝቦቿ በረጅም ዘመናት ታሪካቸው እጅጉን ለስሜት የሚከብዱ ታላላቅ መከራዎችን አይተዋል፤ አሳልፈዋልም፡፡... ለነጻነታቸው እጅጉን ቀናኢ የነበሩት አባቶቻችን ድንበራችንን ደፍረውና አቋርጠው የእትብታችን ማረፊያ፣ የልጅነታችን ዓለም፣ የአዛውንትነታችን መተከዣ... የሆነውን ርስታችንን ሊነጥቁን፣ በባርነትም ሊገዙን ብረት ስለውና ቃታ ስበው ከመጡ ጠላቶቻችን ጋር ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ትንቅንቅ እጅግ የበዛ መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡

በአይበገሬነታችን ህልማቸው የጨነገፈባቸው ወራሪዎቻችንም እጃቸው የገቡትን አቅመ ደካማ ሽማግሌ፣ ሴት፣ ህጻን... ሳይሉ ቤት ውስጥ እያጎሩ በእሳት ፈጅተዋል፤ በጥይት ደብድበዋል። ማረከን ያሉትን ጥቂት ሠራዊትም አንገቱን ቆርጠው ሸልለዋል፡፡ በዚህም ሰልጥነናል ያሉት ነጮች፣ "ያልሰለጠነ ህዝብ ነው" ባሉት ህዝብ ላይ በፈጸሙት አረመኔያዊ ድርጊት ራሳቸው ከሰውም በታች እንስሶች መሆናቸውን ለዓለም አሳይተዋል፡፡

ተበዳዮቹ አባቶቻችን ግን በወቅቱ ይህንን አላደረጉም፡፡ የዚህች ሀገር መሪዎችና ህዝቦቿ ባህር ተሻግረው ለመጡትና በብዙ መስዋዕትነት ለማረኳቸው ወራሪዎቻቸው ያደረጉት በዚያን ዘመን እንኳንስ "አልሰለጠነም" ከሚሉት ህዝብ ቀርቶ በወቅቱ "ገናና ነን፤ ብዙ እናውቃለን" ከሚሉት ህዝቦች እንኳን የማይጠበቅ ነበር። የጠላቶቻቸውን ቁስል ጠርገውና አክመው፣ ስንቅ ቋጥረው... ሸኙ፡፡ በዚህም የሚዋጉት አስተሳሰብንና ርዕዮተ ዓለምን እንጂ ግለሰቦችን እንዳልሆነ ለዓለም አሳዩ፡፡ ሌላ ሌላውን ትተን የአድዋን ድል ብናነሳ እንኳን በጦር ሜዳ ከተገኘው ድል ባልተናነሰ በዲፕሎማሲው የተቀዳጀነው ድል ነው ወራሪዎቻችንን አንገት ያስደፋው፡፡ ኢትዮጵያዊ የሰው ልጅን ሰውነት የሚረዳና የሚያከብር ታላቅ ህዝብ!

በዚህም ጀግኖችና ቆራጦች፣ በነጻነታችን ላይ ለአፍታ እንኳን የማንደራደር ህዝቦች መሆናችንን ለዓለም አሳይተናል፡፡ ይህ ማንም ሊክደው የማይችለው ሀቅ ነው፡፡ ጠላቶቻችንም ሳይቀሩ እያነቃቸውም ቢሆን የሚመሰክሩት ሀቅ! ይህ እውነታችንም በየትኛውም ሥፍራ፣ ዘመንና ህዝብ ፊት በፍጹም የራስ መተማመን እንድንቆምና አንገታችንን ቀና አድርገን እንድንናገር አስችሎናል። "እኛ ማንም ሳንሆን ኢትዮጵያውያን ነን!" እስክንል ድረስ፡፡

ይህንን ማንነታችንን ለመንጠቅና እኛን አንገት ለማስደፋት ሠርክ የሚታትረው ድህነታችን ግን አባቶቻችን በከፈሉት ደማቅ መስዋዕትነት የቆመውን ክብራችንን ተገዳድሮ በዓለም ፊት የረሀብና ችግር ምሳሌ ተብለን እስክንጠቀስ አደረሰን፡፡ እናም ስለማንነታችንና ታሪካችን ልንናገር ስንቆም ብዙዎች ልናሸንፈው ያልቻልነውን ችግራችንን ቀድመው በመናገር ሊያሸማቅቁን ይተጋሉ፡፡... ሆኖም ግን ማንም ክብራችንን ሊደፍርም ሆነ ሊያዋርደን አይሞክርም፤ የሞከረም ሲቀጣ ኖሮአል፡፡

ቀደምት መሪዎቻችንም ቢሆኑ ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ከውጭ ጥቃት በመጠበቅ ረገድ የነበራቸው ቁርጠኝነት የሚታማ አይደለም፡፡ ብዙዎቹ ከህዝባቸውና ከሠራዊታቸው ቀድመው ለመውደቅ ያልሳሱ ነበሩ፡፡ ስለሆነም ከፊሉ ስለሀገሩና ህዝቡ ነጻነት አንገቱን አስቆርጦአል፡፡ ከፊሉም ቃታ ስቦ፣ ጥይት ጠጥቶ... ወድቆአል፡፡ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ህዝቦቿ!! በዚህም ኢትዮጵያዊ ሁሉ የትም፣ መቼም ተከብሮና ታፍሮ ኖሮአል፡፡ ዛሬስ?...

ይህ ህዝብ ድህነታችንና ሌሎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሰበቦች በፈጠሩት ግፊት ከፊሉ ወዙን አፍሶ በመሥራት ጥሪት ሊቋጥር፣ ከፊሉም ከፍቶትና የተሻለ ጊዜን መምጣት ተስፋ አድርጎ ከእናት ምድሩና ከወገኑ ርቆ በባዕድ ሀገር ተጠልሎአል፡፡ ድሮ ህንዶች የማይኖሩበት የዓለማችን ክፍል የለም ይባል ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ኢትዮጵያውያን የሌሉበት የዓለም ክፍል ያለ አይመስለኝም፡፡ የዚህች ምስኪን ሀገር ምስኪን ህዝብ እንጀራ ፍለጋ ከጽንፍ ጽንፍ በዓለም ተበትኖአል፡፡ ለምን? እንዴት?... ተጠያቂው ማንም ይሁን ጥያቄው መልስ ይሻል፡፡

መቼም (ሰበቡ ምንም ይሁን ምን) ማንም ያለምክንያት ከምድሩና ከወገኑ ተለይቶና ርቆ በባዕድ ሀገር አይኖርም፡፡ ይህንን በቅጡ አጥንቶ ማወቅ፣ በርግጥም ችግሩን ለመፍታት የመጀመሪያው ቁልፍ ነው፡፡... ያም ሆኖ ማንም ኢትዮጵያዊ (በምንም ምክንያት) የትም ይኑር የት ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ሌላውን ትተን ወንጀል ሠርቶና ሸሽቶ ቢሆን እንኳን የራቀው በወንጀሉ ይጠየቃል እንጂ ኢትዮጵያዊነቱ አይፋቅም፡፡ ምክንያቱም ዜግነቱና እሱን ተከትለው የሚያገኛቸው ከለላዎች እኛ ስለወደድን የምንሰጠውና ስለጠላነው የምንነጥቀው ቸሮታ አይደለምና፡፡

ከዚህም ሌላ ይህ ወገን በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ተከፍቶም ይሁን ወዶ ትቷት ለሄደው ሀገር የሚያበረክተው አያሌ አስተዋጽኦ አለ። ሌላ ሌላውን ትተን ወዙን አፍሶና ጉልበቱን አድክሞ ከሚያገኘው ገንዘብ ላይ በእናት ምድሩ ለሚደረጉ ልዩ ልዩ ጉዳዮች የበኩሉን ያዋጣል፡፡ ለቤተሰቦቹና ለወዳጆቹ በሚልከው ገንዘብም መንግስትና ሀገሪቱ በልዩ ልዩ መንገዶች ይጠቀማሉ፡፡ ይህን ሁሉ ባያደርግ እንኳን ቅሉ ዜጋ ነውና የእናት ሀገሩ መንግስት ባለበት ሀገር ሊጠብቀውና ሊያስጠብቀው ግድ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የአንድ መንግስት ሥራው ነውና፡፡

የአንድ ሀገር መንግስት በሌላ ሀገር ቆንስላ ጽ/ቤትም ሆነ ኤምባሲ ከሚያቆምበትና አምባሳደር ከሚሾምበት ዋና ምክንያቶች አንዱ በዚያ ሀገር የሚኖሩ ዜጎቹን መብትና ደህንነት ለማስከበርና ጥቃቶችም እንዳይደርሱባቸው ለመከላከል ነው፡፡ እንደሱ ይመስለናል፡፡ ስለሚመስለንም እንጠይቃለን። መጠየቅስ መብት አይደል?!

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያውያን ወዛቸውን አፍሰውና ጉልበታቸውን አድክመው በሚኖሩባቸው አንዳንድ ሀገሮች ያህላል የማይሉት መገፋትና እንግልት እየደረሰባቸው ነው፡፡ አልፎ ተርፎም በታላቅ ግፍ ህይወታቸውን እየተነጠቁ ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት የሆነውን ብቻ እናውቃለን። በአረብ ሀገራት እጅግ ዝቅተኛውን ሥራ ሠርተው ይኖሩ በነበሩ ወንድሞቻችንና

ግፉችንን ወደ ገፅ 19 ዞሯል

ኢትዮጵያ ከገፅ 3 የዞረ

አይሁዳውያን ሕፃናት ነቢዩ ኤርምያስ፡- ‹‹የጩኸት፣ የጣርና ሰቆቃ ድምፅ በራማ ተሰማ፣ ራሄል ስለ ልጆቿ አለቀሰች የሉምና፡፡›› እንዳለው ዛሬም ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከየመን፣ ከደቡብ አፍሪካ፣ ከሊቢያ... ምድር የልጆቿን ጩኸት፣ ሰቆቃና ዋይታ የሰማች እማማ ኢትዮጵያም ማቅ ለብሳ፣ ትቢያ ነስንሳ ሙሾን እያወረደች ነው፡፡ የልጆቿ ኀዘን፣ ሰቆቃና ዋይታ ገና በቅጡ ያልታበሰላት ምድር፤ ዛሬም ዕጣ ፈንታዋ ዕንባና ደም፣ ሰቆቃና ዋይታ ሆኗል፡፡

መንግሥት ሕዳሴዋ በደጅ ነው፣ ልማቷና ዕድገቷም እየተፋጠነ ነው ቢልም አገራችን ዛሬም ለልጆቿ ጥላና ከለላ ለመሆን የቻለች አይመስልም። ከሳዑዲ አረቢያ ውጡልን ተብለው ወደ እናት አገራቸው ተመልሰው ከነበሩ እህቶቻችን መካከል "ከዚህስ ኑሮ ብንሞትም ብንድንም እዚያው አረብ አገር ይሻለናል" በሚል ተስፋ ቆርጠው ዳግመኛ በመጡበት እግራቸው ሲመለሱ ታዘበናል፡፡

የብዙዎች ወገኖቻችን እንባና ደምም ለለውጥና ለአዲስ ተስፋ በሀገራችን ተራሮችና ሸንተረሮች እንደ ውሃ ፈሷል፡፡ የአንድ ማኅፀን አብራክ ክፋዮች እርስ በርሳቸው ተራርደዋል፣ ተላልቀዋል። ብዙዎቻችንም ነፍሳችን እስክትዝል ለሀገራችን ለውጥ በብዙ አንብተናል፣ ወጥተናል ወርደናል፡፡ የለውጥ ያለህ በሚል፣ ከልብ በሆነ ናፍቆትም ነደናል፣ ተቃጥለናልም፡፡ ዛሬም በናፍቆት እንደተቃጠልን፣ እንደ ሽንብራ እንደተርገበገብን፣ በናፍቆት ነፍሳችን



እንደዛለች መሽቶ ይነጋል፡፡

ይህችን በለውጥ ናፍቆት፣ የተስፋ ጭላንጭል ያለህ በሚል የዛለች ነፍሳችንን አይዞሽ የሚሏት፣ የውስጣችንን ጩኸት የሚመልሱ፣ ስብራታችንን የሚጠግኑልን፤ ታሪካችንን፣ የሚያድሱልንና ለነገ ብሩህ ተስፋ ሊያሳዩን የሚችሉ ደጋግ፣ ሁሉን በፍቅር የሚያዩ መሪዎች፣ ፖለቲከኞች፣ የሃይማኖት መሪዎችና መንፈሳዊ አባቶች እንዲኖሩን ደጋግመን ተመኝተናል፡፡

ግና እምብዛም አልተሳካልንም፡፡ ተስፋችን ያዝነው ስንለው እያመለጠን፣ ጉልበታችን ዝሎ ከዚሁ የዘመናት እንቆቅልሾቻችን፣ ያለ ቅጥ ከረዘመው የጨለማው ዘመን ዥንጉርጉር ታሪካችን፣ ጉስቁልናና ውርደት ከተሞላው አስከፊ ገጽታችን ጋር አብረን እየተጓዝን እዚህ ደርሰናል፡፡

*"አቤቱ እባክህ የሆነብንን አስብ፣ ተመልከት ስድባችንንም እይ . . .፡፡››*

*ሰላም! ሻሎም!*

## የፀሐፍት ጥግ

### (ስለ መጠጥ)

- *ወይን ጠጅ የታሸገ ግጥም ነው፡፡*
  *ሮበርት ሉዊስ ስቲቨንሰን*
- *ስጠጣ አስባለሁ፤ ሳስብ ደግሞ እጠጣለሁ፡፡*
  *ፍራንቶይስ ራቤላሲስ*
- *በቀን 24 ሰዓት፣ በሳጥን 24 ቢራ፡፡ ግጥምጥሞሽ ነው?*
  *ስቲቨን ራይት*
- *ወይን ጠጅ በሌለበት ፍቅር የለም፡፡*
  *ዩሪፒደስ*
- *እነሆ የአልኮል መጠጥ፡- የህይወት ችግሮች ሁሉ መንስኤና መፍትሄ፡፡*
  *The Simpsons*
- *አልኮል የሰው ልጅ አስከፊ ጠላት ሊሆን ይችላል፡፡ መፅሀፍ ቅዱስ ግን ጠላታችሁን ውደዱ ብሏል፡፡*
  *ፍራንክ ሲናትራ*
- *እውነታ በአልኮል እጥረት የሚፈጠር ቅዠት ነው፡፡*
  *ኤን.ኤፍ.ሲምፕሶን*
- *መጀመሪያ መጠጥ ትወስዳለህ፤ ከዚያ መጠጡ መጠጥ ይወስዳል፤ በመቀጠል መጠጡ አንተን ይወስዳል፡፡*
  *ኤፍ.ስኮት ፊትዝገራልድ*
- *የቢራ ዋጋን የጨመረ መንግስት ይወድቃል፡፡*
  *የቼኮች አባባል*
- *ውስኪና ቢራ የሰው ልጅ ክፉ ጠላቶች ናቸው፡፡ ከጠላቶቹ የሚሸሽ ግን ፈሪ ነው፡፡*
  *ዜካ ፓጎዲንሆ*
  *(ብራዚላዊ የዘፈን ግጥም ፀሐፊ)*
- *የአልኮልን ጣዕም አልወደውም፡፡ የምጠጣው ሬድ ቡል ነው፡፡*
  *ፓሪስ ሂልተን*
- *አልኮል የሰራተኛውን መደብና አያሌ ሰዎችን ይፈጃል፡፡*
  *ማርቲን ስኮርሴስ*
- *መጠጥ ቀኑን የማጠናቀቅያ መንገድ ነው፡፡*
  *ኧርነስት ሄሚንግዌይ*
- *ከስፖንጅ የበለጠ አልጠጣም፡፡*
  *ፍራንሶይስ ራቤላይስ*
- *የብልህ ሰው ብቸኛው መጠጥ ውሃ ነው፡፡*
  *ሔነሪ ዴቪድ ቶሪዮ*

ጽናት ከገፅ 7 የዞረ

እርቧቸው እንደነበር አያነሱም! አዲስ አበባ የመጣ ቱሪስት ጉራንጉር ገብቶ የቆሻሻ ክምሮችና የወደቁ ደሳሳ ጎጆዎችን የሚያነሳው አገሩ በሳሎኑ ግድግዳ ላይ ሊለጥፍ አይደለም፡፡

የሰሞኑ ጭካኔ ተግባራት መገናኛ ብዙኃን ላይ ብቅ ብለው የወረዱበትን ፍጥነት ነገሬ ላለ ይገባዋል።

ይሄን መገንዘብ አለብን፡፡ አዎ፣ ቢመራቸውም ይቺ አገር ታላቅ ነበረች፣ ታላቅም ትሆናለች፡፡

*"በደም ሥሮቹ ውስጥ በረዶ የሚፈስ ካልሆነ በስተቀር ኢትዮጵያን በችግሯ ሰዓት መርዳት የማይፈልግ፣ በኢትዮጵያ የነጮች ኢምፔሪያሊዝም ወረራን ድባቅ መምታት የማይፈልግ አንድም ኔግሮ አይኖርም፣"* ይላል በ1930ዎቹ የነበረ እውቅ ጥቁር አሜሪካዊ ጋዜጠኛና ደራሲ፡፡ *"ኢትዮጵያ በጣሊያኖች የምትሸነፍና የምትገዛ ከሆነ ለዓለም ጥቁር ህዝቦች ትልቅ ውድቀት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የተማረ ጥቁር አስተያየት ነው፡፡"*

እንዲህ የተባለላት ታላቅ የነበረችና... ለሚመራቸው ቢመራቸውም... ታላቅም የምትሆን አገር ናት፡፡ እስከዛው ግን የጨካኞችን ዓይኖች ከራሳችን ላይ ይንቀልልን፡፡

*ጊዜ ሆይ*
*ሕያው ጊዜ ሆይ*
*በማይምላው ገፅህ ላይ*
*የወጣችን ያቺን ቀን*
*ያቺን*
*የነቀርሳ እባጭ መሣይ*
*የመርዝ ከረጢት ሥራይ*
*ሥሯን በርብረህ ንቀል*
*ዕጯን ፈልገህ ግደል፤*

ብሏል ደበበ ሰይፉ፡፡
ለሁላችንም ጽናቱን ይስጠን፡፡
ደህና ሰንብቱልኝ!

# የጨለማው መሰላል

ብርሀን ጌታ

አየር ማረፊያ ልቀበላት ይገባኝ ነበር:: ግን አልቻልኩም:: ለዚህ ነበር ቀድሜ ከቤት ልጠብቅ ማቀዴ:: እሱም እንዳልተሳካልኝ የተረዳሁት በር ላያ የሚኪን መኪና ሳይ ነበር:: እሱ እንዲያመጣቸው ስለነገርኩት እንደቀደሙኝ እርግጠኛ ሆንኩ:: እንዴት ቶሎ ደረሱ? ከአሜሪካ የገቡት ጠዋት ነበር:: በእርግጥ እንዳይጉላሉ ወደ ባህር ዳር የሚያመጣቸው ትኬትም ቀድሜ አስይዤላቸው ነበር:: ቸልተኛ የሆንኩ እንዳይመስላቸው ሰጋሁ:: እርግጥ ቤት ውስጥ ተገቢው ነገር ሁሉ እንዲዘጋጅ አድርጌአለሁ:: እናቴና የህፃኗ እናትም መጥተው ስላደሩ የጎደለ ሊያሟሉ ይችላሉ:: ኧረ ሰራተኞቼም ለዚህ አይሰንፉም:: ብቻ ባታስብበት ነው ጥላን ስራ የሄደችው እንዳይሉኝ:: እኔ ደግሞ በህይወት እያለሁ ሥራዎቼን በጠዋት ካላየሁ ደስታ አይሰማኝም::

ሹፌሬ መኪናውን አቆሞ ፈጠን ብሎ በመውረድ ከኋላ የጫነውን ዊልቼሬን ፈጥኖ አቀረበልኝ:: እግሮቼ እንዳይራመዱ ሆነው የተልፈሰፈሱት ገና ህጻን እያለሁ ነው:: እናቴ “ስትወለጅ ደህና ነበርሽ፤ በአራስነትሽ ወድቀሽ ጀርባሽ ተጎድቶ ነው” ትላለች:: ብቻ እኔ ግን በእግሬ የሄድኩበትን ጊዜ አላስታውስም:: ሹፌሬ ለመቀበያ ያስጋገርኩትን ኬክ ይዞ ከኋላዬ እየተከተለ እኔ ዊልቸሬን እየገፋሁ ሳሎን ገባን:: ቤቴ በሰው ተሞልቷል:: አስፈላጊው ነገር ሁሉ ቀርቦ ግብዣው ደርቷል:: በከንቱ ተሳቀቅኩ! ቤቴ ሲመጡ በመጥፋቴ ጓጉቼ ባለመቀበሌ አልተቀየሙኝም::

እንደውም ከሞት ተርፌ ከውጭ የመጣሁትና እኔ እስኪመስለኝ ድረስ ሁሉም ቆመው በክብርና በደስታ ተቀበሉኝ:: ደነገጥኩ! የማየው የራሴን እህቶችና ወንድሞች ስለመሆኑ ተጠራጠርኩ:: እናትና አባቴ ሳይቀሩ ልጃቸውን፣ ያውም እኔን! ሳይሆን አንድ ባለስልጣን የሚቀበሉ መስለዋል:: ወንድሜም ገና ሲያየኝ በሮ እቅፌ ውስጥ ገባ::

“ውይ አፈር በበላሁ! ስራ አቋርጠሽ መጣሽ አለሜ? በርግጋ እንደተነሳች የተናገረችው እናቴ ነበረች::

“ምን አንገላታሽ ልጄ! የት እንኸድ ብለኝን ያው እንቆይሻለን? ነይ ነይ እስቲ ግቢ! አባቴም ተከትሏት እየተነሳ ተናገረ::

“እንዴዬ ኧረ ቁጭ በሉ? በገዛ ቤቴ እንግዳ አደረጋችሁኝ እኮ?” እውነትም ግራ እየተገባሁ አሳልፌ እንጉዳይን አቅፌ ሳምኳት:: እንጉዳይ የታላቅ ወንድሜ ልጅ ናት:: ከህጻንነቷ ጀምሮ በሽተኛ ነበረች:: የልብ ችግር እንዳለባትና ውጭ ካልታከመች እንደማትድን ያወቅነው ግን ከፍ ካለች በኋላ ነው::

“ተመስገን! ሁኔታዋን ሳይ ፈጣሪየን ቀና ብዬ አመሰገንኩት:: የወንድሜ ሚስት ልጇን ትታ እኔን መሳም ጀምራለች:: “ምን መናገር እንደፈለገች እንጃ እውነት...እው... እያለች ሳግ ሲያቀርጣት ይታያል:: ወላጆቼም የምርቃቱን ናዳ ያሸክሙኝ ጀምረዋል:: እኔ ግን የሁሉንም ሁኔታ ሳይ ‘ልብሴን ነውር በለው እንጅ እኔስ የቅድሙ ነኝ’ አሉ የሚባለው የአባ ገብረ ሃና ቀልድ መጣብኝ:: ዛሬ አፈር አይንካሽ የሚሉ ዘመዶቼን እንዴት እንዳሳደጉኝ ጭራሽ ትዝ የሚላቸው አይመስሉም:: ለካ የሰው ልጅ ክብሩንም ውርደቱንም የሚፈጥረው ራሱ ነው:: እንዳስቀመጡኝ ቀርቼ ቢሆን አሁን የሚኖረኝን ሁኔታ ማሰብ አንገሸገሸኝ::

የተወለድኩት ደቡብ ጎንደር ጋሳይ ከምትባል የገጠር ከተማ ውስጥ ነው:: የስምንት ልጅ ጌታ ለሆኑት ወላጆቼ ሦስተኛ ነኝ:: የበታቾቼም ሆነ የበላዮቼ የችሎት የችሎታቸውን ያህል ተምረዋል:: የትምህርት ቤት ነፃነት ቀርቶ የግቢዬ ፀሃ እየናፈቀኝ ያደኩት እኔ ብቻ ነኝ:: መራመድ ያልቻልኩት በእኔ ስንፍና ወይም በፍላጎት ገዝቸው አልነበረም::

እነሱ ግን መነሳት፣ መራመድ አቅቶኝ ምድር ላይ ስጥመለመል እንደልዩ ፍጡር አዩኝ:: ስወለድ እንደማገኛውም ልጅ ጤነኛ እንደነበርኩ የምትናገረው እናቴ እንኳን አፈረችብኝ:: የእኔ መውጣትና መኖሬን ማሳወቅ የእሷንም የጤነኛ ልጆቿንም ክብር እንደሚነካ አሰበች:: እናም እኔ ከቤት ውስጥ ከቤትም ጓዳ! እንድቀመጥ ተፈረደብኝ:: ስለመኖሬ እንኳ የሚያውቁት ጓዳ ድረስ ዘው ማለት የሚችሉ የቅርብ ሰዎች ብቻ ናቸው። ለዛውም ተቀምጬ በእህቶቼና አስታዋሽ በሌለው በራሴ ጸጉር የተለማመድኩትን የጸጉር ስራ አገልግሎት ሲፈልጉ። ሁኔታው ቢያናድደኝም ያቺን ደቂቃም ሰው ማግኘት ብርቄ ስለሆነ እታዘዛለሁ:: ያውም በሚስጢር ገብተው አለመኖሬን እያወጁ እንደሚሰሩ እያወኩ::

ወላጆቼ የውጭ ሰው እኔ መስራቴንም ሆነ መኖሬን አውቆ እንዲመጣ አይፈለጉም:: ስለዚህ እኔ ከእነ አለሁበት ሁኔታ መጣወቅ የወዳጆቻቸውን ክብር እንደሚነካ ስለተረዱ ለመጠበቅ ሚስጥሩን ያከብሩታል:: አዎ የእኔ ነገር ውሾን ያነሻ ውሾ ነበር::

በዚህ ሁኔታ ተቀምጬ እያለ ነው የቤታችን የመጨረሻዋ ልጅ የአስራ ሁለተኛ ክፍልን ማትሪክ የወሰደችው:: ምክንያቱን ባላውቀውም የእሷ ፈተና ባለውለታዬ እንደሆነ ይሰማኛል:: እግሬ እንጅ ጭንቅላቴ ስላልታመመ ስለመጨረሻዬ ዘውትር እጨነቅ ነበር:: ለመሞት ያደረኳቸው ጥረቶች ታውቆም ሆነ ሳይታወቅ ተሰናክለውብኛል:: በዚህም መኖር እየጠላሁ የኖርኩባቸው አመታት ቀላል አልነበሩም:: ሞት እንኳን እንዲህ በቀላል ላገኘው የማልችለው ብርቅ ነገር ሆነብኝ:: አንዳንዴ በራሴ አቅም ማጣት ሳይሳካ ይቀራል:: በተለይ አንድ ቀን ራሴን ለማነቅ ያደረጉት ሙከራ ከንቱ የቀረው አቅም በማጣቴ እንጅ ሰው ደርሶብኝ አልነበረም:: አንገቴን በቢለዋ አርጀ ለመግደል የሞከርኩበት ጊዜም ነበር:: ብቻ ለጉዳት የሚጥል ደም ከመፍሰሱ በፊት እናቴ ደርሳ አዳነችኝ። ለምንም እንደማልጠቅም፣ እንደውም ለእነሱ ውርደት እንደተፈጠርኩ እያሰቡ ስለምን ተከታትለው እንደሚያድኑኝ ሳስብ ይገርመኛል:: እንዲህ እየሆንኩ እያዩ እንኳን ተጎልታ ከምትውልበት ሰይጣን ቀረባት እንጅ አንድም ቀን ህይወት አሳስቧት ብለው አያውቁም:: በቃ የማስብም ከንቱ መቀመጤ የሚቆጨኝም አይመስላቸውም:: ያን ቀን ግን በአመጽ ራሴን ይፋ አወጣሁ::

“ወይ ግደሉኝ! ካልያም ልኑርበት አትከልክሉኝ! እኔ ለእናንተ ስል መስዋዕት መሆን አለብኝ?” በመጀመሪያ ከእናቴ ላይ ነበር እንደብራቅ የጮህኩት::

“ኧረ ኧረ ኧረበጉዴ ወጣሁ እናንተ! ኧረገኝ! ኧረ ምን ውሃው በላኝ ሰዎች! ምን ሆነሻል:: እንደልማዷ አመማት ብላ እዛው ጸበል ልታረሰርሰኝ እንደሆነ ሲገባኝ “አዎ እኔ የእናንተ እብድ! ቆይ! እግሬ እንጅ ጭንቅላቴ የታመመ መሰላችሁ እንዴ? እንዳትነኪኝ ነግሬሻለሁ እኔ ምንም አልነካኝም ልታሳብዱኝ የምትጥሩት እናንተ ናችሁ:: እጄን እያወናጨፍኩ ተከላከልኩ::

“ውሃው በልቶኝ ዛሬ ኧረ እባካችሁ ድረሱልኝ!” ጠበሉን እንደያዘች እጀን ለመያዝ ሞከረች::

“ክፉ ነሽ እሽ ክፉ ነሽ ደግሞ እናቴ አይደለሽም አሁን እንዳላመመኝ ጠፍቶሽ ነው በህመም እያመካኘሽ እዚሁ ለማፈን ነው እንጅ! አዎ ልጆችሽ እንዳይዋረዱ እኔ ጓዳ ታፍኜ እሞታለሁ ልቀቂኝ ልቀቂኝ!” ጎረቤት እስኪሰማ ጮህኩ::

ኧረ በጉዴ ወጣሁ ዛሬ እናንተ ሆዬ! እኛ ደግሞ ምን አደረግንሽ ልጄ!? እሽ ወተሽስ ምን ትሆኚ? አሁን የሰው መፈራረጃ ልታደርጊን እንጅ በምንሽ ልትሄጅው ነዋ? እንደ አህያ ትንከባለይ ነገር!” ሁኔታየ አስደንግጧት ይሁን አሳዝኛት ባላውቅም እያለቀሰች ነበር የመለሰችልኝ:: እሷን እምባ ሳይ እንደገና ደነገጥኩ:: ቢሆንም ወደኋላ ማፈግፈግ አልፈለኩም::

“በቃ ማንም ይወቀኝ እወጣለሁ! ጸጉርም ከአሁን በኋላ ያለ ሳንቲም አልሰራም:: ይሄው ጸጉር ቤት የሚሰሩት እንኳን እንደሷ አይሆንም እየተባለ እየሰማሁ! ሁኔታውን ሳስበው ነው መሰለኝ እንደገና ቁጣየን አናረው::



“እንደው ምናለ ብትተይኝ ልጄ:: አሁን የሰው መፈራረጃ ልታደርጊን እንጅ እውነት አንች ሰርተሽ ሕይወትሽን ልትለውጭ ነው? በምንሽ ተንቀሳቅሰሽ? እንደው ይልቅ የሰጠሽን ብትቀበይውና እንዳመጣብኝ እስካለሁ ብጦርሽ ምነው? ‘አርሶ ያልጠገቡ ራስ ሰርቶ’ አሉ የእኔው ሃጢያት ነው እንጅ! ቢያድለኝማ መች እንዲህ... አቋርጣ ለቅሶዋን ጀመረች:: ብታሳዝነኝም መለሳለስ አልፈለኩም:: በተለይ ‘..ብጦርሽ...’ የምትለዋ ቃል ስለት ሆና ከላይ እስከታች ስትቀደኝ ራሴን መቆጣጠር ተሳነኝ:: እየተጎተትኩ ወጥቼ የሰፈር ልጆች በመሰብሰብ ሹርባ ለመስራት ታገልኩ:: ዓላማዬ እንደምሰራ ማሳየት ነው:: አንዳንዶቹ ግን ምን ጉድ ናት ብለው ፈሩኝ መሰል እምቢ አሉ::

ከፍ ከፍ ያሉትና ምን አልባትም ስለ እኔ በሹክሹክታ የሰሙት ግን እየቀረቡ መሰራት ጀመሩ:: ነገሩ ግን ከየዋሉበት የመጡትን ቤተሰቦቼን ሁሉ አስቆጣ:: ተማርን ያሉት እህትና ወንድሞቼ ሳይቀሩ ተናደደቡብኝ:: ለማስቆም ግን መግደል የሚጠይቅ ነበርና ሳይሞክሩት ቀሩ:: እኔም በየቀኑ እንደ እባብ እየተሳብኩ እየወጣሁ ወንበሬ ላይ በመቀመጥ የሃገሩን ቁንዳላ ሁሉ ስቆነድል መዋልን ተያዝኩት::

ስጀምር ፀጉር ቤቶች ያስከፍላሉ ከተባለው ዝቅ ብዬ ነበር:: በኋላ ግን እንደውም የእኔ ጨመረ:: እውነትም ለዚህ የተሰራሁ ሳልሆን አልቀረሁም:: የትኛውም ፀጉር ቤት የእኔን ያህል ማሳመር ባለመቻሉ ሴቱ ሁሉ እኔን መርጦ መሰብሰብ ጀመረ::

ይህን ዝና ሰምታ ክረምቱን በሚያምር ሹርባ ለማሳለፍ የመጣች አንዲት አዲስ ደንበኛ ነበረች አዲስ ህይወት የከፈተችልኝ:: ገና ከመጀመሯ በፊት ነው የተለያዩ ነገሮችን ስትጠይቀኝ የነበረችው:: የልብስ ነጋዴ ናት:: ለሱቋ የሚሆን የተለያ ልብስ ለማምጣት ብዙ ከተሞች እንደምትሄድ ትናገራለች:: ይህን የፀጉር ሥራ ሞያዬን በተመቻቸ ሁኔታ መስራትና እኔም ዊልቼር ገዝቼ እንደፈለኩ መንቀሳቀስ እንዳለብኝ የመከረችኝም ፍጹም ተቆርቋሪ በሆነ ስሜት ነበር:: እንዳለችው ከተመቻቸ ቦታ ሰፋ ባለ መልኩ መስራትን ባልጠላም፣ ቀድሞ ልቤን ያንጠለጠለው ግን ዊልቸሩ ነበር::

“በፈጠረዎ ከቻሉስ የሚረዱኝ ይሄኛውን ነው:: የተለያየ ቦታ ማየት እንደናፈቀኝ መሞት አ...አ..” ድሮም አስተዛዝኘ ለመንግር አቅጀ ነበር:: በየምክንያቴ መቅደም የለመደው እምባዬ ግን አንደበቴን ጭምር ተቆጣጠረብኝ:: እሷን ግን ከማሳዘን ይልቅ አበሳጫት መሰለኝ::

“በይ በይ በይ! አድናቆቴን እንዳታጠፊው! የምን ማልቀስ ነው? በማልቀስ የሚፈታ ችግር የለም:: ጭንቅላቱን እስካላሰራ ድረስ ሁሉም አካል ጉዳተኛ ነው:: ጭንቅላትሽን ከተጠቀምሽበትና አደርገዋለሁ ብለሽ እስከተነሳሽ ደግሞ አንችም ምንም የሚጎድልሽ ነገር የለም:: ታይኛለሽ አይደል እኔን? ለሰው ስታይ ሙሉ ጤነኛ ነኝ:: ግን እስካሁን ድረስ ወገን ዘመድ ያሰለቸሁ ትልቅ ጡረተኛ ነበርኩ:: ... ስትል የቁጣ ናዳ ካወረደችብኝ በኋላ፤ ውጤት አልመጣልኝም ብላ አሮጊት እናቷ ጋር በመቀመጥ እንዴት ድህነትን ስታራባ እንደኖረች፤ አሁን ብድር ወስዳ ንግድ በመጀመሯ እናቷንም እሷንም የለወጠችበትን ሁኔታ በማንሳት፤ ጭንቅላቱን አሰርቶ በህይወቱ ለውጥ እስካላመጣ ድረስ ሁሉም አካል ጉዳተኛ እንደሆነ እየተበሳጨች ነገረችኝ:: ብዙዎቹን ማነሳሻዎቿንም በጣም ወደድኩላት::

ከዚህች ግቢ ታጥሬ በተራ ነገር እንዳልቀርና ትልቅ ራዕይ መቋጠርና ለዚያ መጣር እንዳለብኝ ደጋግማ መከረችኝ። ማውራት ብቻ ሳይሆን ቁም ነገረኛ ሴትም ናት። ከምኑ ገብታ የት አግኝታ እንዳመጣቻቸው እንጃ ዊልቼሩን አንድ ድርጅት በራሱ መኪና ሰጥቶኛና አበረታቶኝ ሄደ:: አዎ ያች ሴት ህይወቴን በጣም ረጅም እርምጃ እንዲራመድ ትልቁን ምርኩዝ አቀብላኛለች::

እውነትም ዊልቸሬ ወደ ፈለኩት ቦታ ሁሉ መራኝ:: መጀመሪያ የሄድኩት ወደ ቀበሌ ነበር:: መስሪያ ቦታ ስጡኝ አልኳቸው:: ወላጆቼ የእኔን ገንዘብ ማጥፋት እንደሃጢያት ይቆጥሩት ስለነበር መጠነኛ ገንዘብ አጠራቅሜ ነበር። እናም ብድር መግባት አልፈለኩም:: ከዚህ ይልቅ ቦታ በመፍቀድ ሊታበረታቱኝ ይገባል ስል ወተወትኳቸው።



እነሱ ሲሰጡኝም በቂ የሚባል ዕቃ ያሟላች ጸጉር ቤት ከፈትኩ። ገቢው ግን ከድሮው የሚሻል አልሆነም:: ከተማችን ትንሽ በመሆኗ ሰው ወደ ሹሩባው ያደላል:: እኔ ደግሞ ከፍ ያለ ገቢና ለውጥ ማየት እፈልጋለሁ፡ ስለዚህ የተወሰነ ጊዜ ከሰራሁ በኋላ ያገኋትን ቦታ ለባለቤቶቹ አስረክቤ እቃዎቼን ጭኜ ባህር ዳር ገባሁ::

ለካ ጀመሪያ ቤትም ሱቅም መከራየት ነበረብኝ:: ደግነቱ ብቻዋን ወድቃ ትሞታለች ብላ የፈራችው እናቴ ውጤቷ ተበላሽቶባት ከቤት የዋለችውን ታናሽ እህቴን አያይዛ ልካኝ ነበር። አሁን በእኔ ማፈር ቀርቷል። እንደውም የቀበሌውም የድርጅቱም ሰዎች ያሳዩኝን ክብር ማየት በራሳቸው እንዲያፍሩ ያደረጋቸው ይመስለኛል። እውነትም እያገዘችኝ ተሯሩጠን ቤት ተከራየን:: ስራችንም በአዲስ መንፈስ አጧጧፍነው:: የገባነው ሰኔ አጋማሽ ነበር ባህር ዳር በእኔ አዲስ ዲዛይን ሹርባ ተሞላች:: ፀጉር ቤታችን የተለያየ መዋቢያዎችንና ዊጎችን ማቅረብ ጀመረች:: ድሮም ሁለት ሰዎችን ቀጥረን ነበር የጀመርነው። እረፍት ማጣታችን ግን ሌላ ሁለት ሰራተኞች አስፈለገን:: በዚህ ላይ የእህቴ ለስራው ፍላጎት ማጣት ሌላ አማራጭ እንድፈልግ አስገደደኝ:: እምቡሽ እምቡሽ እየተባለች ስላደገች. የሰውን ጸጉር ማገላበጥን እንደ ትልቅ ውርደት ቆጠረችው:: እኔ ደግሞ በችግሬ የተከተለችኝን እህቴን እንዲሁ ልሸኛት አልፈለኩም:: እናም ሌላ ሱቅ ተከራይቼ የመዋቢያ እቃዎች ቤት ከፈትኩ:: የማሰራት ግን እንደሁሉም በደመወዝ ነበር:: አላማዬ ማደግ በመሆኑ ያለምክንያት የሚባክን ነገር የለኝም:: በዚህ ጉዳይ ድሮም ጠንቃቃ ብሆንም የክልሉ ነጋዴ ሴቶች ማህበር የሚሰጠን ሞያዊ ድጋፍ ይበልጥ አጎብዞኛል:: ከዚህ መሃል እንዳለሁ ይህን ችሎታሽን ለሰው ማካፈል ይገባሻል የሚሉ አስተያየቶች ይመጡልኝ ጀመር:: ይህም አንድ ሃሳብ ፈጠረልኝ:: የጸጉር ስራ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት መክፈት:: ቦታና ብድር ለማግኜት ወደ ቀበሌ አመራሁ:: ጥሩ አጋጣሚ ላይ ነበር:: የተለያዩ ወጣቶችን እያደራጁ ቦታና ብድር የሚሰጡበት ወቅት፤ እኔንም ብዙ ሳያንገላቱ ተባበሩኝ:: ሁሉም ስኬታማ ነበር። አመታትን ተቀምጬ አሳልፌአለሁና ለማካካስ ያለ እንቅልፍ ታተርኩ:: በተለይ ትምህርት ቤቱ ካሰብኩት በላይ ትርፋማ ሆነ:: ፀጉር ቤቱና መዋቢያ ሱቁም ቢሆን ቀላል የማይባል ትርፍን ያስገቡልኝ ጀመር:: በርካታ ሰራተኞችንም ቀጠርኩ:: አግዙኝ አግዛችኋለሁ ብሎየለም? ጥረቴን ያየው አምላክ ባለሶስት መኝታ ቤት ኮንደሚንየም እጣ ቀድሞ መዘዘልኝ:: በቃ ሃብትና ክብር አቅጣጫቸውን ወደኔ አዞሩ::

እንዲህ ገቢዬን ከየቦታው ማካበት በጀመርኩበት ወቅት ነበር ወንድሜ እንጎዳይን ለምርመራ ወደ አዲስ አበባ ይዞ የሄደው:: ወንድሜ ደብረታቦር የሚኖርና በማስተማር ስራ የሚተዳደር ነው:: ወደ አዲስ አበባ ሲሄድም አንዳንድ ነገሮችን ላግዘው ጥርት አድርጌ ነበር:: እሱ ግን ከእኔ ምንም መውሰድ አልፈለገም:: እኔም ብሆን ያላቸውን ስሜት ስለማውቅና መረዳት እንጅ መርዳት የማይገባኝ ሰው እንደሆንኩ ማሰባቸው ስለሚያስጠላኝ ትልቅ ጉዳይ ካልተፈጠረ በቀር አልቀላቀላቸውም:: ያኔም ካልፈለገ ይተወው ስል በግዴለሽነት ሸኘሁት::

ሲመለስ ግን በነበረው አልተመለሰም:: ምክንያቱም እንጉዳይ ውጭ ሄዳ ካልተከመች በቅርቡ ልትሞት እንደምትችል ተነግሯታል:: ከህጻንነቷ ጀምሮ ስቃይ ያየባት ለተንኮሏ ደግሞ እውነትም እንጉዳይ የሆነች የምታሳሳ ህጻን:: እንኳን ወላጅ ማንም ቢሆን እንዲህ አይነቱን ጉድ የሚችል አቅም አይኖረውም:: ወንድሜም ቢሆን ይህን ተሸክሞ ስለክብር ለማሰብ ጊዜ አልነበረውም። የሚሰጠው ካገኘ እንኳን ከእኔ ከመንገደኛም ይቀበላል::

አስተማሪ ደመወዙ ከእለት ሆድ አልፎ ለእንዲህ አይነት ትልቅ ጉዳይ የሚጠበቅ አልነበረም:: ሚስቱ የቤት እመቤት ናት:: በደህና ጊዜ የገዛው ከደብረታቦር ከታማ ወጣ ብሎ የሚገኘው መኖሪያ ቤቱም አወጣ ተብሎ ሃምሳሽ ሽህ ብር ብቻ ሆነ:: ሃምሻ ሺ ይዞ አሜሪካ ልብ ለማሳከም መሞከር፤ የማይታሰብ ነበር:: አሉኝ ካላቸው ሁሉ ተሯሩጦ መቶ ሽህ እንኳን መሙላት አልቻለም። ሁሉንም ካጠናሁ በኋላ ነው ከአካውንቴ ስምንት መቶ ሽህ ብር አውጥቼ የሸኘሁት:: ለነገሩ እስከሚመጣ የላኩትም ከዛው የሚዳረስ ነው:: የልጅቷ መዳን ትልቁ ዓላማዬ ቢሆንም ዋናው ሃሳቤ ግን እኔ የታፈረብኝ እንዴት መከታ ልሆናቸው እንደቻልኩ ማሳየት ነበር:: ሁኔታው ንግዴን የሚያነጋ፣ ትልዕ እዳ ውስጥ የሚከተኝ ቢሆንም ማነነቴን እስካሳየልኝ ድረስ ግድ አልነበረኝም:: ከሁሉም በላይ ትልቁ ድል እንዳረባ ሰው በጣሉኝ ቤተሰቦቼ መሃል ይህን ያህል ክብር ማግኘት ነው::

# የሰው ልጅ አውሬነትና የሰው ልጅ ቅዱስነት በሊቢያ!

ኤልያስ

- ለክርስቲያን ወገኖቹ ሲል የተሰዋው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም
- አራት ኤርትራውያን "ሙስሊም ነን" ብለው ከISIS አመለጡ
- በሊቢያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መንግስት አላነጋገረንም አሉ

ባለፈው እሁድ ነበር በአረመኔው የአሸባሪ ቡድን (ISIS) 30 ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መቀላታቸውን የሰማነው:: ከእነዚህ ውስጥ ሦስቱ ጥገኝነት ተከልክለው ከእስራኤል የመጡ ኤርትራውያን ነበሩ ተብሏል:: አንደኛው ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነው:: ጀማል ራህማን ይባላል:: *ሶማሌላንድፕሬስ* ድረገጽ እንደዘገበው፤አሸባሪው ቡድን ጀማል ሙስሊም በመሆኑ ለጊዜው አልፈለገውም ነበር:: ሆኖም ቡድኑ የጀማልን ጓደኛ ጨምሮ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን መርጦ ሲወስድ አላስቻለውም:: በፈቃደኝነት ተቀላቅሏቸው ሄደ:: በኢትዮጵያውያኑ ላይ ግድያ እንዳይፈጽም የቻለውን ያህል ቢያደርግም አልተሳካለትም:: በመጨረሻም ሃይማኖታቸውን እንዲቀይሩ ተጠይቀው "አይሞከርም!"ካሉት ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጎን በISIS አሸባሪ ቡድን ተቀልቷል:: *ሶማሌላንድፕሬስ* የሐረር ተወላጁን ጀማል ራህማንን የገለጸው፤ "ኢትዮጵያዊው ሙስሊም ሰማዕት!" በማለት ነው:: (ከዚህ በላይ ቅድስና ከየት ይመጣል!?) በአንድ ቦታ ነው የሰው ልጅ አውሬነት እና የሰው ልጅ ቅድስና የተገለጠው። በአንድ በኩል አረመኔው ISIS፤ በሌላ በኩል ለክርስቲያን ወገኖቹ ሲል የተሰዋው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም!

አሁንም ግን በሊቢያ የኢትዮጵውያን ስደተኞች መከራ አላበቃም:: አሁንም አሸባሪው ቡድን በርካታ ኢትዮጵያውያንን መያዙ ተሰምቷል:: በትሪፖሊ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ወደ አገራቸው መመለስ ቢፈልጉም ማን እንደሚወስዳቸውና የት እንደሚመዘገቡ እንደማያውቁ ጠቁመው እስካሁን ከመንግስት ወገን ያነጋገራቸው እንደሌለ ሰሞኑን



ከISIS ያመለጡ 4 ኤርትራውያን

ለቪኦኤ ገልጸዋል:: በግብጽ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሙሃሙድ ድሪል ስልክ ላይ ደጋግመው ቢደውሉም እንደማይነሳ በምሬት ተናግረዋል- ስደተኞቹ:: አንድ በጣም ተስፋ የቆረጠ ኢትዮጵያዊ፤"የኢትዮጵያ መንግስት የሚረዳን አይመስለኝም" ብሏል - ለቪኦኤ:: ዜጎች እንዲህ በባዕድ አገር፤ "ከአሁን አሁን እያዝ ይሆን?" እያሉ ከሞት ጋር በተፋጠጡበት የጭንቀት ሰዓት መንግስት "አለሁላችሁ" ሊላቸው ይገባል:: (ዜጎችን ከሞት ከመታደግ የላቀ ልማት የለም!)

በነገራችሁ ላይ በሊቢያ በከፍተኛ ስጋት ውስጥ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ብቻ አይደሉም:: የተለያዩ የአፍሪካ አገራት ስደተኞች በጀልባ ወደ አውሮፓ ለመሻገር እየተጠባበቁ ሲሆን በአሸባሪው ቡድን ተይዘው አሰቃቂ የሞት እርምጃ እንዳይወሰድባቸው በመፍራት በርካታ ስደተኞች በአንድ ጀልባ ላይ እየተሳፈሩ የባህር ሲሳይ በመሆን ላይ ናቸው:: ባለፈው ቅዳሜ በሜዲትራኒያን ባህር በሰጠመችው ጀልባ ከ800 በላይ ስደተኞች ለሞት የተዳረጉ ሲሆን ከሟቾቹ መካከል ኤርትራውያን፣ ሶማሊያውያንና ኢትዮጵያውያን-ይገኙበታል ተብሏል:: በቁጥር የሚበዙት ግን ኤርትራውያን እንደሆኑ ዘገባዎች ይጠቁማሉ:: (ለእነሱም ዜጎቼ የት ገቡ የሚል መሪ ይስጣቸው!)

***ወንድማማቾቹ ከ ISIS አመለጡ***

የ19 ዓመቱ ሃቤን እና የ14 ዓመት ታዳጊ ወንድሙ ሳሙኤል፤ከኤርትራ ተሰደው ሊቢያ የገቡት የአውሮፓ አገራትን አልመው ነበር:: እንዳለመታደል ሆኖ ግን በአይምሬው አሸባሪ ISIS እጅ ውስጥ ገቡ:: ታጣቂዎቹ ሃይማኖታቸውን ሲጠይቋቸው፣ሙስሊም መሆናቸውን ተናገሩ:: ክርስቲያን ነን ቢሉ የሚጠብቃቸውን ያውቃሉዋ::

"ክርስትያኖች ነን፤ ነገር ግን እምነታችንን መካድ ነበረብን:: ያለበለዚያ ታጣቂዎቹ ይገድሉናል:: ወይ በጥይት ይመቱናል አሊያም ይቀሉናል" በማለት ሃቤን ለሜይልኦንላይን ድረገፅ አስረድቷል:: ሃቤን እንደሚለው፤ጓደኞቹ ክርስቲያን በመሆናቸው በISIS ግድያ ተፈጽሞባቸዋል::

"ጓደኞች ነበሩኝ - ኤርትራዊና ግብፃዊ - ክርስትያን መሆናቸውን በመናገራቸው ተገድለዋል"

እነ ሃቤን የጓደኞቻቸው መገደል ጥልቅ ሃዘን ውስጥ እንደሚከታቸው ሳይታለም የተፈታ ነው:: ነገር ግን እነሱም እንደማይቀርላቸው ያውቃሉ::

"ክላሺንኮቭ የታጠቁ ሰዎች ይመጡና እምነትህን ይጠይቁሃል:: ክርስትያን ከሆንክ ወስደው


የሰው ልጅ ወደ ገፅ 20 ዞሯል

## የፖለቲካ ጥግ

# በመንግሥት በጀት ትዳራቸውን የሚያስተዳድሩ ፕሬዚዳንቶች

## በየዓመቱ አንድ ድንግል የሚያገባው መሪ





1. **ምስዋቲ**

የስዋዚላንዱ ንጉስ ምስዋቲ አስገራሚ ባህላዊ መሪ ናቸው - እንግሊዝ የተማሩ! በጐሳቸው ባህል መሰረት ብዙ ሚስቶችን ማግባት ይችላሉ (እችላለሁ ስላሉ ነው!) ለዚህም ነው 14 ሚስቶች አግብተው 24 ልጆችን ያፈሩት:: ይሄ ብቻ ግን አይደለም:: (ቢሆንማ በማን እድላችን!) በየዓመቱ በሚካሄደው የደናግል ኮረዶች ዳንስ፣ ንጉሡ አንድ ድንግል መርጠው ያገባሉ:: ሚስቶቻቸው በ14 የተንደላቀቁ ቤተመንግስቶች ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን እነሱን ለማስተዳደርም ከድሃዋ አገራቸው ዓመታዊ በጀት ላይ 31.7 ሚ. ፓውንድ ይወስዳሉ (ትዳር በመንግስት በጀት ይመቻል!)

ሁሉም ሚስቶቻቸው ደስተኛ ናቸው ለማለት ያዳግታል:: (የንጉስ ወህኒ ቤት እኮ ነው!) ለምሳሌ ሦስቱ ሚስቶቻቸው (ለስሙ ንግስቶች ናቸው!) አካላዊና ስነልቦናዊ ጥቃት ደርሶብናል በማለት የንጉሱን ቤተመንግስት ጥለው ወጥተዋል:: ለንጉስ ምስዋቲ በዓመት አንዴ የሚካሄደው የኮረዶች ባህላዊ የዳንስ ትርኢት ሁሌም በጉጉት የሚጠበቅ ነው:: እ.ኤ.አ በ2012 ዓ.ም 80ሺ. ደናግል ኮረዶች (እርቃነ-ጡታቸውን) ሆነው ለስዋዚላንዱ ንጉስ የዳንስ ትርኢት አሳይተዋል - በስቴዲየም። በዚህ ትርኢት ንጉሱ ይዝናናሉ:: አንድ ድንግል መርጠውም ያገባሉ:: አንዳንዶቹን ልጃገረዶች ደግሞ አልፎ አልፎ ለመቅበጥ ይፈልጓቸዋል::

በንጉሡ ተመርጣ ሚስት የሆነች ኮረዳ ወዲያውኑ አንድ ቤተመንግስትና BMW አውቶሞቢል ይበረከትላታል:: ለአንዲት ምስኪን የገጠር ኮረዳ ይሄ ምን ማለት እንደሆነ አስቡት! (ግን ድንግልናዋን ብቻ ሳይሆን ነፃነቷንም ተነጥቃ ነው!) ያለንጉሱ ፈቃድ የትም ንቅንቅ አትልም:: (እስር በሉት!) በዓመት አንዴ ግን ሁሉም ሚስቶቹ አሜሪካ ሄደው እቃ እንዲሸምቱ ንጉሱ ገንዘብ ይሰጧቸዋል:: በነገራችን ላይ አባታቸው ንጉስ ሶብሁዛ (ሁለተኛው) 70 ሚስቶች ነበሯቸው፤ 400



ልጆችም ወልደዋል:: (የዘር ነዋ!)

ንጉስ ምስዋቲ የመጨረሻ ሚስታቸውን ያገቧት በ19 ዓመቷ ሲሆን በዳንስ ትርኢቱ ላይ ነው የመረጧት:: ንጉሱ የሚያስተዳድሯት ስዋዚላንድ በጣም ትንሽ አገር ስትሆን የህዝቧ ቁር 2 ሚሊዮን እንኳን አይሞላም:: 70 በመቶ ህዝቧ ግን ከድህነት ወለል በታች ነው የሚኖረው:: የአፍሪካ የመጨረሻው ንጉስ ናቸው የሚባሉት ምስዋቲ ደግሞ የጠገቡ ሃብታም ናቸው - የ200 ሚ. ዶላር ጌታ! በአፍሪካ ቀዳሚ "ሴት አውል" ፕሬዚዳንት በሚል በአንደኝነት ተመርጠዋል::

2. **ጃኮብ ዙማ**

ጃኮብ ዙማ የደቡብ አፍሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ካገለገሉ በኋላና የአገሪቱም ሆነ የአፍሪካ ናሽናል ኮንግረስ ፓርቲ ፕሬዚዳንት ከመሆናቸው በፊት በአስገድዶ መድፈር ተከሰው ነበር:: ዙማ ዘመናዊ መሪ (ድንቄም ዘመናዊ!) ቢመስሉም አራት ሚስቶች አሏቸው:: ፕሬዚዳንት ጃኮብ እ.ኤ.አ በ2014 ዓ.ም "ውሃ አጣጪ" አምስተኛ ሚስታቸውን (ለእርጅና ዘመኔ ብለዋል!) ለማግባት ዝግጁ መሆናቸውን ጠቁመው ነበር:: የ72 ዓመቱ ዙማ፤ (በደቡብ አፍሪካ በስንት ዓመት ነው አረጀሁ የሚባለው?) "ሚስቶች አሉኝ፤ ነገር ግን የመጨረሻይቱን በቅርቡ አገባለሁ" ብለዋል:: (ለምን የመጨረሻ እንዳሉ አልገባኝም!!)

ለፕሬዚዳንቱ ቅርብ የሆኑ ሰዎች እንደመሰከሩት፤ ሰውየው ከሴት ሌላ ወሬ የላቸውም:: 20 ገደማ ልጆች ያሏቸው ዙማ፤ ስድስት ጊዜ ያገቡ ሲሆን በእርግጥ አሁን በመንግስት በጀት የሚያስተዳድሯቸው አራት ሚስቶች ብቻ ናቸው ያሏቸው:: (ሰውየው መደበኛ ትምህርት አልዘለቃቸውም ይባላል!) ጃኮብ አንድ ጊዜ በአስገድዶ መድፈርና በትዳር ላይ በመማገጥ ተከሰው ነበር - "አፍሪካ ክራድል" እንደዘገበው::

3. **ጋዳፊ**

ሊቢያን ከ30 ዓመታት በላይ አንቀጥቅጠው የገዟት ኮሎኔል ሙአመር ጋዳፊ (መሬት ይቅለላቸውና!) ሁለት ሚስቶች ነበሯቸው - ሳፍያ ፋርካሽ እና ፋቲሃ አል-ኑሪ:: ለብዙዎች የጋዳፊ ሞት

በጀት ወደ ገፅ 23 ዞሯል

# ሳይንስ፤ “ውሃ በጣም አስታዋሽ እና ታሪክ ዘጋቢ ነው” ይላል

## ውሃ ፍቅርና ጥላቻንም ይሰያል



ተፈሪ መኮንን

ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነኝን፤ ‹‹የሕፃናት ቍርባን የሥነ ምግብ ባለሙያዎችን አከራከረ›› በሚል የቀረበው ዜና ነው፡፡ በአንድ በኩል፤‹‹ሥጋ ወደሙን ከምግብ መቁጠር ሃይማኖታዊ ነጻነትን እና ሥርዓትን የሚፃረር ነው›› በሚል የቀረበ ሐሳብ አለ፡፡ በሌላ በኩል፤ የሥነ ምግብ ባለሙያዎች ‹‹እንደ ተጨማሪ ምግብ ነው የምናየው›› ያሉ መሰለኝ፡፡ እንግዲህ ይህ ፅሑፍ፤ ይህን ክርክር ዳራ አድርጎ የተፃፈ መሆኑ ነው፡፡ እዚህ የማጫውታችሁ፤ ሳይንስ በውሃ ባህርይ መቸገሩን ነው፡፡ ሳይንስ፤ ‹‹ውሃ ያስታውሳል›› ይላል፡፡

### ውሃ ቅርብ – ውሃ ሩቅ

ውሃ በየትም ቦታ ይገኛል፡፡ ለምሣሌ፤ ድንች 80 በመቶ ውሃ ነው፡፡ አንዲት ላም፤ 74 በመቶ ውሃ ነች፡፡ ባክቴሪያም 75 በመቶ ውሃ ሲሆን፤ የቲማቲምን ነገር ተውት፡፡ ቲማቲም 95 በመቶ ውሃ ነው፡፡ ቲማቲም ሙሉ በሙሉ ውሃ ከመባል የተረፈው ለጥቂት ነው፡፡ የሰው ልጅ ራሱ 70 በመቶ ውሃ ነው፡፡ ከጠጣርነቱ ይልቅ ውሃነቱ ያመዝናል፡፡ የሰውን ልጅ ‹‹የውሃ - ጠጣር›› ምጣኔ ሲታይ፤ አንድ እጅ ጠጣር፣ ለሁለት እጅ ውሃ ነው፡፡ ውሃ በጣም እንግዳ ነገር ነው፡፡ ቅርፅ የለውም፣ ሽታ የለውም፣ ‹‹ትራንስፓረንት›› ነው፡፡

የሰው ልጅ፤ ከአጠገቡ እንዲጠፋበት የማይፈልገው ነገር ውሃ ነው፡፡ ውሃ በዙሪያው ከሌለ ድራሹ ይጠፋል፡፡ ውሃ ጣዕም የለውም፡፡ ግን የውሃን ጣዕም አብዝተን እንፈልገዋለን፡፡ ውሃ ሽታ የለውም፡፡ ግን የውሃን ሽታ አብዝተን እንወደዋለን፡፡ ውሃ በጣም የሚፈለግ፤ ነገር ግን እጅግ አደገኛ ነገር ነው፡፡ ውሃ በየዓመቱ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት የሚቀጥፍ ነው፡፡ ሰሞኑን እንኳን በሜድትራኒያን ባህር ያለቀው ስደተኛ ቁጥር ዘጠኝ መቶ የደረሰ መሰለኝ፡፡ ውሃ ይገድለናል፡፡ ግን ከእርሱ ጉያ መራቅ አንፈልግም፡፡ ውሃን ዘወትር ስለምናየው፤ አስገራሚ ነገር መሆኑን እንዘነጋለን፡፡ ውሃ የተለየ ነገር ነው፡፡ ስለ ውሃ በማወቅ ስለሌሎች ፈሳሾች ለማወቅ አንችልም፡፡ ስለ ሌሎች ፈሳሾች ያለን ዕውቀት፤ ፈሳሽ የሆነውን ውሃን ለማወቅ ምንም አይጠቅመንም፡፡ ምክንያቱም ውሃ ልዩ ንጥረ ነገር ነው፡፡ ስለ ውሃ ስናውቅ፤ ከውሃ ጋር ዝምድና ስላላቸው ኬሚካሎች ማለትም ስለ <<hydrogen Selenide or hydrogen Sulphide>> ዕውቀት ቢኖረን፤ ውሃ 135 ድግሪፋናይት ሊፈላ የሚችል ወይም በ Room temperature ወደ ጋዝነት ሊቀየር የሚችል ነገር አድርገን ልናስበው እንችላለን፡፡

በሌላ በኩል፤ አብዛኞቹ ፈሳሾች ሲቀዘቅዙ በ10 በመቶ ይኮማተራሉ፡፡ ውሃም በረዶ ከመሆን ደረጃ ሳይደርስ በሚኖረው ቅዝቃዜ ለዓመል ያክል ትንሽ የመኮማተር አዝማሚያ ያሳያል፡፡ ግን ወደ ነጥበ-በረድ (freezing Point) ሲቃረብ በአስገራሚ ሁኔታ መንሰራፋት ይይዛል፡፡ ጠጣር ከመሆን ደረጃ ሲደርስ፤ ምግደቱ (volume) በ10 በመቶ ጨምሮ ይንሰራፋል፡፡ ስለዚህ በረዶ በውሃ ላይ ይንሳፈፋል፡፡ በረዶ እንዲህ ዓይነት ባህርይ ባይኖረው ኖሮ፤ በውሃ ገፅ ላይ መንሳፈፉ ቀርቶ ይሰጥም ነበር፡፡ በረዶው እየሰረገ እና እታች ወርዶ እየተቀለለ፤ ውቂያኖሶች ወይም ሐይቆች ከስር ጀምረው በረዶ እየሆኑ ሲመጡ እናይ ነበር፡፡ ሆኖም ነገሩ እንደዚያ አይደለም፡፡ በባህር ገፅ ላይ እንደ ቂጣ ተጠፍጥፎ የሚንሳፈፈው በረዶ፤ እንደ ጋቢ ባህሩን ጀቡኖ፤ ሙቀት ከባህሩ እንዳይወጣ አምቆ በመያዝ፤ የባህሩ ውሃ ወደ በረዶነት እንዳይቀየር ያደርጋል፡፡ በዚህ ዓይነት የባህሩን ሙቀት በማቀብ፤ ውሃው ወደ በረዶነት እንዳይቀየር እገዛ ያደርጋል፡፡ በረዶው ባይንሳፈፍ ኖሮ፤ ሙቀት እያፈተለከ፤ የባህሩ ውሃ በቶሎ ነጥበ - በረድ (freezing Point) ላይ ደርሶ፤ ያ የባህር ውሃ ለረጅም ጊዜ ምናልባትም ለዘላለም በረዶ ሆኖ በቀረ ነበር፡፡ ይህም ለህይወት መቀጠል የማያመች ሁኔታን ያስከትል ነበር፡፡

ውሃ፤ የኬሚስትሪን ደንብ እና የፊዚክስን ህግ የሚያውቅ አይመስልም፡፡ ሁሉም ሰው እንደሚያውቀው፤ የውሃ ኬሚካላዊ ቀመር $H_2O$ ነው፡፡ ይህ ማለት አንድ ትልቅ የኦክስጅን አተም እና ሁለት አነስ-አነስ ያሉ የሐይድሮጅን አተሞችን የያዘ ውህድ ነው፡፡ እነዚህ የሃይድሮጅን አተሞች ከኦክስጅን አተም ጋር በጥብቅ ተያይዘዋል፡፡ ግን ውሃ ጠላቂ ዘሎ ሲገባ ለመከልከል በሚያስችል ኃይል እርስ በእርስ የተጣበቁ አይደሉም፡፡ ሆኖም ውሃ ቱቦ ሆኖ ሽቅብ ሊረጭ የሚችለው ወይም በመኪና መስተዋት ላይ የተንጠባጠበው የዝናብ ውሃ ከሌላ የውሃ እንክብል ጋር እንደ ዛጎል ሲጣመር የምናየው የመተሳሰር ባህርይ ስላለው ነው፡፡ በውሃ ገፅ ላይ ያለው ከፍተኛ የመሳሳብ ዝንባሌ (Surface tension) የተፈጠረው በዚሁ የትስስር ተፈጥሮ የተነሳ ነው፡፡ በውሃ ገፅ ላይ የሚገኙ ሞለኪሎች፤ ከበላያቸው ካሉ የአየር ሞለኪሎች ይልቅ፤ ከእነሱ በታች እና ከጎናቸው ካሉ ሌሎች የውሃ ሞለኪሎች ጋር በከፍተኛ ሁኔታ የመሳሳብ ባሕርይ አላቸው፡፡ ይህም አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮችን ለማንሳፈፍ የሚያስችል የኃይል ድርን ይፈጥራል፡፡

ታዲያ የሃይድሮጅን አተሞች ከኦክስጅን አተም ጋር በጥብቅ ቢያያዙም፤ አንዳንዴ ከሌሎች የውሃ ሞለኪሎች ጋር ይተሳሰራሉ፡፡ የውሃ ሞለኪሎች በባህርያቸው ዳንስ የሚወዱ ይመስላሉ፡፡ ለአንድ አፍታ ከአንዱ ጋር ይጣመሩና መልሰው ያን ለቅቀው ከሌላው ጋር ይጣመራሉ፡፡ ሁል ጊዜ የዳንስ ጓደኞቻቸውን ይቀይራሉ፡፡ በብርጭቆ የተሞላ ውሃ ሲታይ እንዲህ ያለ ዓመል ያለው አይመስልም፡፡ ሆኖም በውሃ ውስጥ ያሉ ሞለኪሎች በሰከንድ ውስጥ በቢሊየን ለሚቆጠር ጊዜ የዳንስ አጣማጃቸውን ይቀያይራሉ፡፡ በዚህ መንገድ የውሃ ሞለኪሎች፤ ባህር እና ውቂያኖሶችን ይፈጥራሉ፡፡ ይሁንና ከውሃ ሞለኪሎች በአንድ ጊዜ ተያይዘው የሚገኙት 15 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው፡፡

### ውሃ ያስታውሳል

ከሰሞኑ የተመለከትኩት አንድ ዶኩመንታሪ ‹‹ውሃ በዙሪያችን ያለ ነገር ነው፡፡ ግን ስለዚህ አስደናቂ የተፈጥሮ ክስተት ምስጢር በውል እናውቃለን?›› በማለት ይጀምራል፡፡ አያይዞም፤ ‹‹ውሃ ከየት መጣ? ለዚህ ፕላኔታችን ይህን ልዩ የተፈጥሮ ሐብት ያደላት ማን ይሆን?” ሲል ይጤቃል፡፡

‹‹በዚህ በእኛ ዩኒቨርስ ውስጥ ውሃ ያላት ፕላኔት የእኛይቱ መሬት ብቻ ነች፡፡ ግን ይህን ሐብት ማን ሰጣት? ለምን ሰጣት?›› የሚለው የዶኩመንታሪው ተራኪ፤‹‹ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ሊሰጠን የሚችለው ራሱ ውሃ ብቻ ነው›› ይላል፡፡

ዛሬ በምድር ላይ ያለው ውሃ፤ ገና ከፍጥረት ማለዳ የነበረው ውሃ ነው፡፡ የውሃ ስርዓት ዝግ በመሆኑ፤ የውሃው መጠን አይጨምርም አይቀንስም፡፡ በመሬት ላይ 320 ሚሊየን ኪዩቢክ ማይል ውሃ አለ፡፡ ዝንተ ዓለም መጠኑ ይኸው ነው፡፡ የሚጨመር የሚቀነስ ነገር የለም፡፡ ዛሬ በብርጭቆ ሞልተን ብድግ አድርገን የምንጠጣው ውሃ፤ ‹‹የተሰጠውን ሥራ›› እየሰራ፤ ከጥንት እስከ ዛሬ የኖረ ነው፡፡ የነበረ እና ወደፊትም የሚኖር ነው፡፡ ሳይንቲስቶች እንደሚሉት፤ ከ3.8 ቢሊየን ዓመታት ጀምሮ ውቂያኖሶች ከሞላ ጎደል ዛሬ ያላቸውን የውሃ መጠን አግኝተዋል፡፡ ባለሙያዎች፤ ነገረ-ውሃን ‹‹ሃይድሮስፌር›› (Hydrosphere) ይሉታል፡፡

የነገረ-ውሃ ጥናት ውቂያኖስ ነው፡፡ 97 በመቶ የሚሆነው የምድራችን ውሃ የሚገኘው በውቂያኖሶች ሲሆን፤ ከውቂያኖሶችም ግማሽ የሚሆነው ውሃ የሚገኘው (51.6 በመቶው) በሰላማዊ ውቂያኖስ (Pacific Ocean) ነው፡፡ የሰላማዊ ውቂያኖስ ስፋት ከዓለማችን የየብስ ስፋት ይበልጣል፡፡ አትላንቲክ ውቂያኖስ 23.6 በመቶ፣ ህንድ ውቂያኖስ 21.2 በመቶ፣ ሌሎች የዓለማችን ባህሮች በአንድነት 3.6 በመቶውን የምድር ውሃ ይዘዋል፡፡

ለመጠጥ ሊውል የሚችለው የዓለማች የውሃ መጠን፤ ከዓለማችን የውሃ ሐብት 3 በመቶው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የሚበዛው የበረዶ ቂጣ ሆኖ የሚገኝ ሲሆን፤ ይህ የበረዶ ቂጣ 90 በመቶው የሚገኘው በአንታርቲካ ነው፡፡ ቀሪው ደግሞ በግሪንላንድ፡፡ ከ3 በመቶው ውስጥ እጅግ በጣም ትንሽ መጠን የሚሸፍነው (0.036 በመቶ) በሐይቅ፣ በወንዞች፣ በግድቦች ሲገኝ፤ 0.001 ተን ሆኖ በደመና ውስጥ ይገኛል፡፡

ሩስተም ሮይ (Rustum Roy) በአሜሪካ፤ ‹‹ስቴት ዩኒቨርስቲ ኦቭ ፔንሲልቫኒያ›› ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ የዓለምአቀፍ የሳይንስ አካዳሚ አባል የሆኑት ሩስተም ሮይ፤ ‹‹እኛ ሁልጊዜም ጠበብ ያለ የጥናት መስክ መርጠን፤ ትኩረታችንን ወስነን፤ በጣም ጥንቃቄ አድርገን ነው ጥናት የምናካሂደው፡፡ እናም አሁን ውሃን በመውሰድ ለማጥናት ወስነን ምርምር ስናካሂድ፤ የውሃን ነገር ከብዙ አቅጣጫዎች እናየዋለን›› ይላሉ፡፡

ኪሪል (Kirill) የተባሉ በሩሲያ የስሞለንስኪ እና የካሊንግራድስኪ (Smolensky and Kaliningradsky) ሐገረ-ስብከት ሊቀ ጳጳስ ውሃ ስለ ውሃ ሲናገሩ፤ ‹‹በብዙ ሐይማኖታዊ መፃህፍት፤ ውሃ ከተራ ግዑዝ ነገር ላቅ ያለ ተደርጎ ይቀርባል፡፡ ውሃ ተራ ግዑዝ ነገር ሳይሆን ላቅ ያለ ፅንሰ-ሐሳብ ሆኖ ሲቀርብ እናስተውላለን፡፡ ይህም ፅንሰ-ሐሳብ ለየት ባለ መንገድ ከህይወት ጋር ትስስር ያለው ነገር ሆኖ ሲገለጥ እናስተውላለን›› ይላሉ፡፡

ከምድር የተፈጥሮ ክስተቶች ውስጥ እንደ ውሃ ለስላሳ እና ገራም ነገር የለም፡፡ ሆኖም፤ ይህ ገራም እና ለስላሳ ነገር፤ እንደ ዓለት ፅኑ እና ጠንካራ የሆነን ነገር ያፍረከርከዋል፡፡ አልሞ ይበላዋል፡፡ ውሃን ማንም ሊቆጣጠረው ይችል ይሆናል፡፡ ግን ውሃን የሚያሸንፍ ነገር በምድር ላይ አይገኝም፡፡ በጣም ገራም እና ለስላሳ የሆነው ውሃ፤ በጣም ፅኑ እና ጠንካራ የሆነውን ነገር ሁሉ ያሸንፋል፡፡ ገራሙ ጠንካራውን፤ ለስላሳው ፅኑዕ እና ድርድር የሆነውን ነገር ያንበረክከዋል፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ ይህን እውነት ሁሉም ሰው ያውቀዋል፡፡ ግን ከዚህ እውነት የሚገኘውን ትምህርት መመሪያው አድርጎ ህይወቱን ለመምራት የሞከረ ሰው ብዙ አይገኝም፡፡ ይህን እውነት የሕይወት መመሪያ ሊያደርግ የሞከረ ላኦትዙ የተሰኘ የቻይና ሊቅ ነው፡፡ ‹‹በድካም ኃይል ይገኛል›› የሚል ሐሳብ ያለው ላኦትዙ፤ ከሁለት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በፊት ስለ ውሃ ፅፏል፡፡ ላኦትዙ ነገረ-ውሃ ገብቶታል፡፡

የኖቤል ተሸላሚ የሆኑት ዶ/ር ከርት ውትሪች (Kurt Wuthrich)፤ ‹‹ውሃ በእጅጉ ጥናት የተደረገበት ነገር ነው፡፡ ሆኖም ውሃ ሁሌም እንግዳ ነው፡፡ ከሌሎች ፈሳሽ ንጥረ ነገሮች ጋር ሲተያይ ከተለመደው ነገር ወጣ ያለ ፊዚካላዊ እና ኬሚካላዊ ጠባይ የሚያሳይ ንጥረ ነገር ነው›› ይላሉ፡፡

አሎይስ ግሩበር (Allois Gruber) የተባሉ የኦስትሪያ ተመራማሪ በበኩላቸው፤ ‹‹ውሃ ከነጥበ-በረድ (freezing point) ሳይደርስ በፊት፤ እፍጋቱ (Density) ለምን እንደሚጨምር፤ በተቃራኒው ከነጥበ-በረድ አለፍ ሲል ለምን እንደሚቀንስ እስከ ዛሬ ድረስ ለማወቅ የቻለ ሳይንቲስት አልተገኘም›› ይላሉ፡፡

ቅዝቃዜው ከነጥበ-በረድ በታች ሲሆን እፍጋቱ ለምን እንደሚጨምር፤ በተቃራኒው ከነጥበ-በረድ በላይ ሲሆን እፍጋቱ ለምን እንደሚቀንስ ምክንያቱን አውቆ ሊያብራራልን የሞከረ ጠቢብ አላገኘንም፡፡ ማንኛውም ንጥረ ቁስ (substance) ሲቀዘቅዝ ይኮማተራል ወይም contract ያደርጋል፡፡ ሆኖም ውሃ በጣም ሲቀዘቅዝ በጣም ይንሰራፋል ወይም expand ያደርጋል፡፡

### ሰው እና ውሃ

ሰው ያለ ውሃ ሊኖር አይችልም የሚል ነገር መናገር ከንቱ ነው፡፡ የሰው ልጅ ውሃ ካጣ፤ ሰውነቱ በፍጥነት ይፈራርሳል፡፡ በቀናት ውስጥ ከንፈራችን በቢላ ቆርጠው እንዳነሱት እልም ብሎ ይጠፋል፡፡ ድዳችን እንደ ከሰል ይጠቁራል፡፡ አፍንጫችን እንደ ቅጠል ክሽልል ብሎ የተፎነነ ይመስላል፡፡ ቁመቱ በግማሽ ይቀንሳል፡፡ በዓይናች ዙሪያ ያለው ቆዳ ተሸብሽቦ ዓይናችንን ለማርገብገብ ያዳግተናል፡፡

ታዲያ በምድር ላይ ካለው ውሃ ለጤና ተስማሚ ሆኖ ጥማችንን ሊቆርጥልን የሚችለው እጅግ በጣም ጥቂቱ ነው፡፡ የሚበዛው ገዳይ ነው፡፡ ወይም ጨዋማ ነው፡፡ የሰው ልጅ በህይወት ለመኖር ጨው ያስፈልገዋል፡፡ ግን፤ ሰውነታችን የሚፈልገው በመጠኑ በጣም ትንሽ ጨው ብቻ ነው፡፡ በባህር ውሃ ውስጥ የሚገኘው ጨው ግን በጣም ብዙ ነው፡፡

የባህር ውሃ ከሰውነታችን እንደሚወጣው ላብ እና እንባችን ያለ ይዘት ያለው ነው፡፡ በአንድ ሊትር የባህር ውሃ ውስጥ በሻይ ማንኪያ፤ ሁለት ከግማሽ የሚሆን ጨው ይገኛል፡፡ ከሚገባው በላይ ጨው ብንወስድ፤ ወዲያው የምግብ ልመት ስርዓታችን ይቃወሳል፡፡ የውሃ ሞለኪሎች፤ እንደ እሳት አደጋ ሰራተኛ በፍጥነት አደጋውን ለመከላከል ይራወጣሉ፡፡ በድንገት ወደ ሰውነታችን የገባውን ውሃ ‹‹ዳልዩት›› ለማድረግ እና ከሰውነታችን ለማስወጣት ይረባረባሉ፡፡ በዚህ የተነሳ፤ ሰውነታችን ተገቢውን ሥራ ለመስራት የሚያስፈልገው ውሃ በእጅግ ይቀንስበታል፡፡ ሰውነታችን በውሃ እጥረት ይቸገራል፡፡ ወይም Dehydrated ይሆናል፡፡ በጣም የከፋ ‹‹ዲሐይድሬሽን›› ሲከሰት፤ ራስን የመሳት ችግር ይፈጠራል፡፡ አዕምሮ ለጉዳት ይዳረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ አደጋውን ለመከላከል የተራወጡት እና በከባድ ሥራ የዛሉት የደም ሴሎች፤ ጨውን ወደ ኩላሊት ያጓጉዛሉ፡፡ ኩላሊት ፋታ የማይሰጥ ሥራ ይሸከማል፡፡ የሚመጣው ጨው ከአቅሙ በላይ ሲሆን በሩን ይዘጋል፡፡ ኩላሊት ሥራ ሲያቆም ያ ሰው ይሞታል፡፡ ለዚህ ነው የባህር ውሃ የማንጠጣው፡፡

እንደተጠቀሰው የውሃ ባህርይ ልዩ ነው፡፡ ምነው ቢሉ፤ በፊዚክስ ውስጥ ተቀባይነት ካላቸው አጠቃላይ ህግጋት ጋር የሚጣጣም ባህርይ አያሳይም፡፡ ግን ይህ የውሃ ልዩ ባህርይ፤ ህይወት በምድር ላይ እንዲኖር ለማድረግ ያስቻለ ነው ይላሉ፡፡ ከቁሳዊ ነገሮች ውስጥ በሦስት ኩነት (ጠጣር፣ ፈሳሽ እና ጋዝ) ሊገኝ የሚችል ውሃ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ሳይንስ፤ ይህ ለምን እና እንዴት እንደሆነ ገና አላወቀም፡፡ ከፈሳሽ ነገሮች ውስጥ ውሃ ለምን ከፍተኛ ‹‹ሰርፌስ ቴንሽ›› ያለው ፈሳሽ ሆነ ለሚለው ጥያቄም ምላሽ አላገኘም፡፡ ውሃ በምድራችን ላይ ከፍተኛ የአሟሚነት ባህርይ ሊይዝ የቻለው እንዴት ነው? ለሚለው ጥያቄም መልስ የለውም፡፡ ውሃ፤ በአስር ሺዎች የሚለካ ‹‹አትሞስፌሪክ ግፊት›› ያለበትን ሁኔታ ተቋቁሞ፤ በትላልቅ ዛፎች ግንድ ውስጥ በሚገኙ ‹‹ቀጫጭን ቱቦዎች›› (thin tubes) ውስጥ ሽቅብ መውጣት የቻለው እንዴት ነው? ለሚለው ጥያቄም ሳይንስ ገና መልስ አላገኘም፡፡ ስለዚህ፤ በሩሲያ ‹‹የሞስኮ ስቴት ዩኒቨርስቲ›› የባዮሎጂ ፋካልቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶ/ር ቭላድሚር ቮይኮቭ (Vladimir Voeikov) ስለ ውሃ ብዙ የምናውቀው ነገር የለንም ይላሉ፡፡

### የውሃ ትንግርት

በደቡብ ምሥራቅ እስያ በ1956 ዓ.ም የተከሰተ አንድ አስደናቂ ነገር አለ፡፡ ቦታው፤ ዚግት (?) እየተባለ የሚጠራ ወታደራዊ ላቦራቶሪ ነው፡፡ በዚህ ላቦራቶሪ አውዳሚ የጦር መሣሪያ ለመፍጠር እና ለመፈብረክ ለዓመታት ጥናት እየተደረገ ቆይቷል፡፡ አውዳሚ የጦር መሣሪያ ለመፍጠር በውሃ ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡ እኒያ የሳይንስ ጠቢባን በአንድ ክፍል ውስጥ ለረጅም ሰዓታት በምስጢር ውይይት ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ፤ ውይይቱ ድንገት ተቋረጠ፡፡ በስብሰባው የነበሩት ሳይንቲስቶች በሙሉ በድንገት ታመሙና ወደ ሆስፒታል ተወሰዱ፡፡ በሁሉም ላይ የምግብ መበከል ከሚያስከትለው የጤና መታወክ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ችግር ይታይባቸው ነበር፡፡ ወዲያው የችግሩን መንስዔ ለመረዳት ጥረት አደረጉ፡፡ ሆኖም ሳይቲስቶቹ ከውሃ በስተቀር ሌላ የወሰዱት ምግብ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ውሃው ተመረመረ፡፡ በጠጡት ውሃ ውስጥ ምንም ዓይነት መርዛማ ነገር አልተገኘም፡፡ የጠጡት ውሃ ኬሚካላዊ ይዘት፤ ያው የታወቀውና የተለመደው $H_2O$ ነበር፡፡ ምርመራ ከተካሄደ በኋላ የተጠናቀረው ሪፖርት ያመለከተው፤ ሰዎቹ የቀመሱት መርዝ አለመኖሩን ነበር፡፡ ሰዎቹ የተመረዙት በጠጡት ውሃ ነበር፡፡

ይህ ችግር ከተከሰተ ከ20 ዓመታት በኋላ አንድ አስደናቂ መላምት ቀረበ፡፡ ይህ መላምት የውሃን ተገማች ያልሆነ ባህርይ ፍንትው አድርጎ የሚገልጥ ነበር፡፡ አጥኚዎቹ፤ ያቀረቡት መላምት፤ ‹‹ውሃ እንደ ሰው አዕምሮ ሁኔታን የመመዝገብ ባህርይ አለው›› የሚል ነበር፡፡ ስለዚህ ሰውን አጥፊ የሆነ ነገር ለመስራት ለሚያስቡት ሳይቲስቶች ውሃ መርዝ ሆነባቸው፡፡

በዓለም ዙሪያ በተደረጉ በርካታ ጥናቶች እንደተረጋገጠው፤ ውሃ በዙሪያው የሚከናወኑ ነገሮችን ሁሉ መዝግቦ ይይዛል፡፡ በውሃ ዙሪያ የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ፤ በውሃ ላይ ተፅዕኖ ያሳድሩበታል፡፡ እርሱም፤ በዙሪያው ባሉ ቦታዎች የሚከናወኑ ነገሮችን መዝግቦ ይይዛል፡፡ ውሃ ሁሉንም ነገሮች ያስታውሳል፡፡ ከውሃ ጋር የተገናኘ ማንኛውም ነገር (ለምሣሌ፤ መርከብ በላዩ ላይ ቢሄድ ወይም ዳክዬ ብትዋኝበት) ውሃው የእነዚህን ክስተቶች አሻራ መዝግቦ ያኖራል፡፡

በነገራችን ላይ፤ ተራ ውሃን በነሐስ ውሃ ማቅረቢያ ውስጥ በማኖር፤ ፈዋሽ ይዘት እንዲኖረው የማድረግ ጥበብ አለ፡፡ ታዲያ ከዚህ ጋር በተያያዘ ፕሮፌሰር ሩስተም ሮይ የሚሉት ነገር አለ፡፡ ‹‹የአሜሪካ ጦር ለቁስል ማከሚያ የሚጠቀምበት፤ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች በእጃቸው የሚገኝን ጀርም (Infectious bugs) ለማጥፋት በማሰብ

ሳይንስ ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# 10 ምርጥ የአፍሪካ አዳዲስ ቴክኖሎጂ አፍላቂ ኩባንያዎች

መንግሥቱ አበበ

አፍሪካ የራሷ ብቻ በሆኑ ችግሮች የተተበተበች አህጉር ናት፡፡ በተለይ የገጠር አፍሪካዊ ሕይወት በተለያዩ ችግሮች የተወሳሰበ ነው፡፡ የተለያዩ ኩባንያዎች ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ይሆናል ባሉት የፈጠራ ውጤት የገጠር ነዋሪውን ሕይወት ቀላልና ምቹ ለማድረግ እየጣሩ ነው፡፡ ቀጥሎ 10ሩን ምርጥ ችግር ፈቺ የተባሉ የፈጠራ ውጤቶች እንቃኛለን፡፡

1. **አይ ሃብ (I Hab):-** የአፍሪካን ማኅበረሰቦች በቴክኖሎጂ ለማገናኘትና ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ የሚሰራ ለትርፍ ያልተቋቋመ ግብረ ሰናይ ኩባንያ ነው፡፡
   ኤሪክ ሄርስማን አይ ሃብ (I Hab) ለኬንያ ማኅበረሰብ በጣም ጠቃሚ የቴክኖሎጂ ምንጭ ሆኗል፡፡ ይህ ሁለት ነገሮችን በማዋሃድ የሚሰራው ግብረሰናይ ድርጅት፤ ከዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ሲሆን በሶስት ዓመት ብቻ ከ10 ሺህ በላይ አባላት አፍርቷል፡፡ ድርጅቱ 150 ኩባንያዎች እንዲቋቋሙ ያደረገ ሲሆን አብዛኞቹ ድርጅቶች በተለይ የአፍሪካ ብቻ በሆኑ ችግሮች ላይ በማነጣጠር የቴክኖሎጂ መፍትሔ በመፍጠር ያተኮሩ ናቸው፡፡
2. **ሰነርጂ (Sanergy):-** ከሰሐራ በታች ላሉ የአፍሪካ አገሮች ቋሚ የጤና ሽፋን ለማምጣት የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡
   የሰነርጂ ቋሚ ሞዴል ምስጋና ይግባውና ሽንት ቤት በሌላቸው፣ ቆሻሻና ብዙ ሰዎች በሚኖሩባቸው የኬንያ ሰፈሮች ከ12ሺህ በላይ ነዋሪዎች በየቀኑ የመፀዳጃ ቤት ወረቀትና ደቃቅ ሰጋቱራ፣ ሳሙናና ውሃ እንዲሁም ተንቀሳቃሽ መፀዳጃ ቤት እያገኙ ነው፡፡
   የአካባቢው ነዋሪዎች በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በመደራጀት፣ ተንቀሳቃሹን መፀዳጃ ቤትና መገልገያዎቹን ገዝተው ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ሰገራው በየቀኑ እየተሰበሰበ መንግሥት ባወጣው የጥራት ደረጃ የተለያዩ ኬሚካሎች ተጨምሮበት ወደ ሚጣራበት ማዕከል ይወሰድና ማዳበሪያ ይሆናል፡፡ ማዳበሪያውን ከፍተኛ ዋጋ ከፍለው በፋብሪካ የተመረተውን ማዳበሪያ መግዛት የማይችሉ የምስራቅ አፍሪካ ገበሬዎች ገዝተው ይጠቀሙበታል፡፡
3. **ዋን ኤከር ፈንድ (One Acre Fund):** - የአዲሱን ትውልድ የአፍሪካ ገበሬዎች ለመደገፍ የተቋቋመ ነው፡፡ ይህ ዘዴ፣ ሞዴሉ ቀላል፣ ጥቅሙ ግን ግዙፍ ነው፡፡ በጥቂት ዓመት ብቻ የአፍሪካ አነስተኛ ገበሬዎች ትልቁ ኔትዎርክ ከግማሽ ሄክታር በታች እንደሚሆን ዋን ኤከር ፈንድ ገምቷል፡፡
   ኩባንያው ለገበሬዎቹ ዘርና ማዳበሪያ በዱቤ ይሰጣል፡፡ ምርታቸውን የሚሰበስቡበት መሳሪያዎችና የሚጭኑበት መኪና ያቀርባል፣ በመሳሪያዎች እንዴት እንደሚጠቀሙ ያሰለጥናል፤ እንዲሁም ምርታቸውን ለመሸጥ ይረዳቸዋል፡፡ ዋን ኤከር ፈንድ ከ10 ዓመት በፊት በ2006 በኬንያ ከተመሰረተ ወዲህ ወደ አጎራባች አገሮች ዩጋንዳ፣ ታንዛንያና ብሩንዲ በመዛመት 180ሺህ አባል ገበሬዎች ሲኖሩት ይህን ቁጥር በ2014 ዓ.ም መጨረሻ 200ሺህ ለማድረስ አቅዷል፡፡
4. **ሮኬት ኢንተርኔት (Rocket Internet):** - ዓላማው የአሜሪካ ዓይነት ንግድ በአፍሪካ ማቋቋም ነው፡፡ በአሜሪካ፣ አውሮፓ፣ በእስያ... የተለመዱ ዘመናዊ የኢንተርኔት ግብይቶችን በአፍሪካ ማስተዋወቅ ነው፡፡ በአፍሪካ ሥራ ከጀመረ ከ2007 ወዲህ ከ100 በላይ ኩባንያዎች አቋቁሟል፡፡ በፉድ ፓንዳ በኢንተርኔት ምግብ ማቅረብ፣ በላማንዲ (Lamundi) ሪል ኢስቴት፣ በጃርጎ (Jarogo) ሆቴል መያዝ፣ እንዲሁም በጁሚያ (Jumia) በመጠቀም በአህጉሩ ተወዳጅና ተዋቂ ከሆነው የኢንተርኔት መረብ ከአማዞን ሊንክ ጋር ግንኙነት በመፍጠር መገበያየት የሮኬት ኢንተርኔት ያስገኘው ውጤት ነው፡፡
   ኩባንያው ጀርመን - በርሊን ከሚገኘው ዋና መ/ቤቱ የሚመራው ቢዝነስ አብዛኛው ተመሳሳይ ነው፡፡ በአፍሪካ አዲስ የቢዝነስ አሰራርና አመራር ለማምጣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ለአህጉሩ ዕድገት ወሳኝ ነው፡፡
5. **ኮንጋ (Konga):-** የኢንተርኔት ሽመታን ደህንነት የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ የሚሠራ ነው፡፡ ኩባንያው በቅርቡ ባስተዋወቀው የገበያ ስፍራ፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ ‹አልባሳት፣ የቤት ዕቃዎች፣ ... በአጠቃላይ ከ200 ሺህ በላይ ምርቶች ያለ ስጋት በኢንተርኔት መግዛት ያስችላል፡፡ የዕቃዎቹ ሻጮች ደግሞ ከናይጀሪያ ትናንሽ የመንደር ነጋዴዎች አንስቶ ትላልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን ያጠቃልላል፡፡
   የገዢዎችንና የሻጮችን ደህንነት በተመለከተ፣ ናይጄሪያውያን ብሮድባንድ ኢንተርኔት መጠቀማቸውን እስቀጠሉ ድረስ በኢንተርኔት መገበያየት እንደሚጀምሩ ኮንጋ እምነቱ መሆኑን ገልጿል፡፡
6. **ስቴሪዮ ዶት ሚ (Sterio.me):-** መሰረተ ልማትን ከትምህርት ውስጥ ማውጣት ወይም መንገድ፣ ትራንስፖርት፣ የትምህርት ተቋም፡ ... ሳይኖር በኢንተርኔት ማስተማር ነው ዓላማው፡፡
   ይህ በጅምር ላይ ያለ ተቋም ለሙከራ፣ በሞባይል ኢንተርኔት ለማስተማር (ኢ-ለርንግ) በናይጄሪያ 75 ት/ቤቶች ተመዝግበው እየተማሩ ያሉ ልጆችን ከት/ቤት አስወጥቶ ትምህርቱን የሚሰጠው በኤስኤምኤስ (SMS) መልዕክት ነው፡፡ ከክፍል ውጭ ሆነው ለመማር ለተመዘገቡት የትምህርት መጻህፍትና ደጋፊ ጽሑፎችን በሞባይል እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
   ትምህርቶቹ ቀደም ብለው በአስተማሪዎቹ የተቀረፁ ስለሆነ ተማሪው እንደ ነፃ ድምፅ ጥሪ (Free Voice Call) በልዩ የኤስኤምኤስ መልዕክት ይልካል፡፡ አስተማሪዎቹ ወዲያውኑ የትኛው ተማሪ ትምህርቱን ጨርሶ እንደላከና እንዴት እንዳዘጋጁት ይረዳሉ፡፡ ይህም ለማረሚያና ቀጣዩን ትምህርት ለማዘጋጀት ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡
7. **አፕ ኢነርጂ (UP energy):-** በገጠሪቷ አፍሪካ ያለሥጋት ምግብ ለማዘጋጀት ይረዳል፡፡
   በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ በገጠሪቷ ዩጋንዳ የሚኖሩ ሰዎች እስካሁንም ድረስ በሶስት ጉልቻና ናፍጣ ብቃት በሌለውና ለጤና አደገኛ በሆነ ዘዴ ምግብ እያዘጋጁ ነው፡፡ አፕ ኢነርጂ ሰዎቹንም ሆነ አካባቢውን የማይጎዳ ዘዴ አዘጋጅቷል፡፡
   ድርጅቱ ለትላልቅ ቢዝነሶች የካርቦን ዱቤ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፡ - ለአካባቢው ቸርቻሪዎች ደግሞ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አረንጓዴና ብቃቱ የበለጠ የተረጋገጠ የማብሰያ ምድጃ፣ የውሃ ማጣሪያ ቴክኖሎጂና የፀሐይ ብርሃን በማቅረብ በቀጥታ እንዲገዙ ድጋፍ ያደርጋል፣ ስለአጠቃቀሙ መመሪያም ይሰጣል፡፡
8. **ዳፕቲዮ (Daptio):-** አዲሱን ትምህርት የመቀበል ዘዴ ተመራጭ ማድረግ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የኢንተርኔት ቀጥታ ትምህርት የበለጠ እየተለመደ ስለሆነ ቀጣዩ እርምጃ፣ የተለመደውን የሌክቸር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ተመራጭና ተቀባይነት ባለው የማስተማር ዘዴ (Adaptive Learning) መተካት ነው፡፡
   የዚህ ትምህርት ዘዴ ግብ፣ ተማሪዎች፣ የሚማሩትን ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የሚረዱበትንና የተሻለ ውጤት የሚያገኙበትን ትክክለኛ የትምህርት ማውጫና ትክክለኛ ጊዜ የሚያገኙበትን ሞዴል መቅረፅ ነው፡፡
   አፍሪካ ወደፊት የኢንተርኔት ሞባይል ትምህርት የሚስፋፋባት አህጉር ናት፡፡ ስለዚህ በቀጣይ 5 ዓመታት በአፍሪካ የሞባይል ትምህርት 39 በመቶ ሲያድግ ከኢንተርኔት የሞባይል ትምህርት የሚገኘው ገቢም በ2017 ወደ 530 ሚሊዮን ዶላር ያድጋል፡፡ የዳፕቲዮ አስፈላጊነት ይህን እውነታ ማረጋገጥ ነው፡፡
9. **ፕሪፕ ክላስ (Prep):-** ቀጣዩን ትውልድ ለማጀት ፕሪፕ ክላስ፣ የናይጄሪያ ተማሪዎች ደረጃውን ለጠበቀ ፈተና የሚያዘጋጅ ተንቀሳቃሽ የኢንተርኔት ድርጅት ነው፡ ተማሪዎቹ ለኢንተርኔት ወይም ለወረቀት ፈተና ለመዘጋጃ ልምምድ ይከፍሉና ለፈተናው ቀን ማሻሻል ያለባቸው ነገር ይነገራቸዋል፡፡ ይህን የኢንተርኔት ትምህርት በቀላሉ ማግኘት እንዲቻል ፕሪፕ ክላስ በናይጄሪ ከ1000 በላይ ከሆኑ ሳይበር ካፌዎች ጋር እየሰራ ነው፡፡
10. **አውዛ (Aweza):-** የተበታተነ ኅብረተሰብ ለማገናኘት በደቡብ አፍሪካ ከ11 በላይ ቋንቋዎች አሉ፡፡ አውዛ በእነዚህ የተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ያለውን የቋንቋ ክፍተት ለማጥበብና የቋንቋ ልዩነቶችን ለመቀነስ የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡ የአጠቃቀም መመሪያው ተጠቃሚዎች በትናንሽ ፓኬጆች ያሉ ቃላት ወይም ሐረጎችን ወደሌላ ቋንቋ መተርጎም የሚያስችሉ ናቸው፡፡

# አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ የዜድቲኢ አምባሳደር ሆነ



አለማየሁ አንበሴ

ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ የዜድቲኢ (ZTE) ኩባንያ የስማርት ሞባይል ስልኮች አምባሳደር ሆነ፡፡ አትሌቱ ባለፈው ረቡዕ በሸራተን አዲስ በተከናወነ ስነስርአት ዜድቲኢ ለኢትዮጵያ ገበያ ሊያቀርባቸው ላቀዳቸው የስማርት ሞባይል ስልኮች አምባሳደር መሆኑ በይፋ ታውቋል፡፡ በስነ ስርዓቱ ላይ የተገኘው አትሌቱ፤ ከዜድቲኢ ጋር በፈፀመው ውል ምን ያህል እንደተከፈለው ባይገልፅም በዚህ መልኩ መስራቱ እንዳስደሰተው ተናግሯል፡፡


የቻይናው ዜድቲኢ ኩባንያ የዘመኑን የ4G ቴክኖሎጂ የታጠቁ ስማርት ስልኮችን በቅርቡ ለሃገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ እንደሚጀምር በሸራተን በተካሄደው ምርቶቹን የማስተዋወቅ ስራ ላይ የተገለፀ ሲሆን ኩባንያው በቅርቡ በኢትዮጵያ የሞባይል መገጣጠሚያ ፋብሪካ እንደሚያቋቁም የኩባንያው ኃላፊዎች ተናግረዋል፡


ለብዙ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል ይፈጥራል የተባለው የሞባይል መገጣጠሚያ ፋብሪካው፤ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተገንብቶ ወደ ስራ እንደሚገባ የኩባንያው የአፍሪካ ቢዝነስ ተርሚናል ምክትል ፕሬዚዳንት ሚስተር ዲንግ ሃዎ ለጋዜጠኞች ተናግረዋል፡፡ ኩባንያው በመላው ዓለም በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የምርቱ ተጠቃሚ ደንበኞች እንዳሉት የጠቆሙት የኩባንያው ኃላፊዎች፤ ኩባንያው የስማርት ስልክ ምርቶቹን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ኢትዮ ቴሌኮም የ4G አገልግሎት በተጀመረበት ወቅት በመሆኑ ትክክለኛ ጊዜ ነው ብለዋል፡፡

የስማርት ስልኮቹ ለኢትዮጵያ ገበያ በተመጣጣኝ ዋጋ ቀርበዋል ያሉት የኩባንያው የምስራቅ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ሚስተር ጂያ ቼን፤ ስልኮቹ የአውሮፓ እና የአሜሪካ ስታንዳርድ ያላቸው ናቸው ብለዋል፡፡ የዜድቲኢ ምርቶችን ለማከፋፈልም ህዳሴ ቴሌኮም ከኩባንያው ጋር ስምምነት እንደፈፀመ ታውቋል፡፡

ዜድቲኢ በ2014 እ.ኤ.አ በአለማቀፍ ደረጃ ከ37 የ4G ቴክኖሎጂ አቅራቢ ኩባንያዎች አንዱ የነበረ ሲሆን የገቢ ድርሻውም 24.8 በመቶ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ የፈረንጆች ዓመት 100 ሚሊዮን የሚባይል ቀፎዎችን ለገበያ ያቀረበ ሲሆን 48 ሚሊዮን የሚሆኑት የስማርት ቀፎዎች ናቸው ተብሏል፡፡ በ2015 እ.ኤ.አ 60 ሚሊዮን የስማርት ቀፎዎችን ለዓለም ገበያ እንደሚያቀርብም የኩባንያው አመራሮች ተናግረዋል፡፡

# “ልብ ብዬ ሳየው የሚያስቀኝ መፅሐፍ አለኝ”




ዓለማየሁ ገላጋይ

“ትክ ብዬ ሳያት የምታስቀኝ ሚስት አገባሁ” ያለ አንድ የአገሬ ሰው አለ፡፡ ይሄ ግለሰባዊ መትከንከን ምሳሌያዊ አነጋገር የሆነው ለብዙ ሰዎች በቀጥታ አለያም በተዘዋዋሪ ተተርጓሚነት ስላለው ነው፡፡ ይሄኔ ምሳሌያዊ አነጋገሩ በተወለደበት ዘመን “...አለ፣ አያ እከሌ” እየተባለ ይነገር የነበረ ይሆናል። ከጊዜ ብዛት፣ ከበባታ መስፋት “አያ እከሌ” ተዘንግቶ፣ ምሳሌው እርቃኑን ቀርቶ ይሆናል፡፡ (እንዲያም አለ እንዲህ) ምሳሌው እኔ ጋ ደርሶ ዛሬ መግቢያ አድርጌዋለሁ፡፡ መግቢያ ብቻ ሳይሆን እንግዳ ስሜቴን ቅልብጭ አድርጎ የሚያሳይ ዘዴ ሆኖ አገልግሎኛል፡፡ እንዲህ፡-

“ልብ ብዬ ሳያቸው የሚያስቁኝ መፅሐፍት ገዛሁ” እንዴ? ያሰኛል፡፡ መልሱ እንዲህ ነው፡-

አንዳንድ መፅሐፍት አሉ፤ የአንባቢን ድክመት መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ፡፡ እነዚህ መፃህፍት በተለይ ከሰው በስጦታ መልክ ከቀረቡ እንደ ስድብም የሚቆጠሩ አይነት ናቸው፡፡ ለምሳሌ እኔ’ጋ ካሉትና ልብ ብዬ ሳያቸው ከሚያስቁኝ መፅሐፍት አንዱን ልጥቀስ - “The Complete IDIOT’s Guide” (የተሟላ የደደቦች መመሪያ) የሚል ርእስ አለው፡፡ ይሄን መፅሐፍ አንድ የቅርብ ሰው በስጦታ መልክ ካቀረበልዎ አንድም እርስዎ፣ አለበለዚያም እርሱ (ከሁለት አንዳችሁ) ደደቦች ናችሁ፡፡ ‘እንዴት?‘ ያሰኛል፡፡ ‘እንዲህ‘ ነው፡፡

ሰውየው ይሄን መፅሐፍ የሰጥዎ ሆን ብሎ ከሆነ ድድብናዎን ወይም ጅልነትዎን አለያም ፉዞነትዎን አይቶ ያዘነልዎ፣ ወይም ቀርቦ የተማረረብዎ፣ ካልሆነም ተመራምሮ የደረሰብዎ ሰው ነው ማለት ነው፡፡ ፍቺ በሌለው መንገድ፣ ያለምክንያት፣ በእንዝህላልነት ይሄን መፅሐፍ ገዝቶ ከሰጥዎ ደግሞ ሰውየው እራሱ ደደብ፣ ወይም ጅል አለበለዚያም ፉዞ ነው ማለት ነው፡፡

ይሄ መፅሐፍ የተበረከተበት አግባብ እንዴት ነው? ብሎ ማጤን ደግሞ ደግ ነው፡፡ መፅሐፉ እቤትዎ ድረስ ወይም ብቻዎን ሳሉ ተሸፋፍኖ ከተሰጥዎ “ምክር” ነው፡፡ በአደባባይ ተገላልጦ ከተበረከተልዎ ደግሞ “ስድብ” ነው፡፡ እንዴት? ቢሉ ይሄንን ነባር ምሳሌ ያጤናሉ፡፡ “ለብቻዬ የሰደበኝ - መከረኝ፤ በሰው መካከል የመከረኝ - ሰደበኝ”

“The Complete IDIOT’s Guide” ሦስተኛው እትም (2003 ዓ.ም) እኔ’ጋ አለ፡፡ ይሄ መፅሐፍ ከያዛቸው ርእሰ ጉዳዮች መካከል እኔ “ደደብ” የሆንኩበትን የቤት አያያዝ መርጬ በማስቀደም አነበብኩ፡፡ አከፋፋይ ቦታ ላይ ቆሞ በመምከር ይጀምራል፡፡ ቤትዎ ጭንቅላትዎ ውስጥ እንዳለው ህልምዎ አድርገው ማደራጀትና መሰደር ከቻሉ፣ ከዚህ ምስቅልቅል አለም የሚሸሹበትን ብቸኛ ቦታ በድል አድራጊነት መመሥረት ችለዋል ይላል፡፡ ጐጆ’ኮ “ከራስ በላይ ኮርኒስ” ተብሎ የሚጠቃለል ጉዳይ አይደለም፡፡ (Your home doesn’t have to mean just a roof over your head) ይልና ስለቤት አያያዝ ወሳኝነት ይመከራል። ምክሩን አንብቤ እንዲህ እደመድማለሁ፡፡

ያልተደራጀና የተመሰቃቀለ ቤት እንቅፋት እንደበዛበት የባህር ቀዘፋ እንግልት የሞላበት መንፈስ ፈጥሮ ይደክማል፡፡ ሰው በጠዋቱ ከቤቱ ሲወጣ ከደከመው ፉክክር በበዛበት ዓለም ውስጥ ምኑን ተወዳደረው? በአግባቡ የተያዘ መኖሪያ ግን ለልዩ ተልእኮ ማዕከል እንደሚያደርጉት ወታደራዊ ቤዝ ነው...

....ወደ እኔ እውነታ ስመጣ ግን እንደዚያ አይደለም፡፡ ቤቴ በሰዎች “ሥርዓት” ሲይዝ ይዞርብኛል፡፡ ከምስቅልቅሎቹ ጋር ተግባቦት አለኝ። ስላልተሰደረ ደክሞኝ ከቤቴ አልወጣም፣ ቤቴን አልጠላም፣ የፈለኩትን ከቤቴ አላጣም፣ መንፈሴ በቤቴ ላይ አይጐሽም... ለመሆኑ “ከ’Idiot’ እነቴ” ጋር ተስማምቼ ኖርኩ? ወይስ Idiot አይደለሁም? ደግሞስ ምስቅልቅሎቹ ካልተሰማኝና ካልረበሸኝ መፅሐፉ ለምን አስፈለገኝ? እንዴትስ አብሮኝ ለአመታት ቆየ?... እያልኩ ልብ ብዬ ሳየው ከሚያስቀኝ መፅሐፍ ጋር አለሁ፡፡

እኔ ጋ ካሉትና ልብ ብዬ ሳያቸው ከሚያስቁኝ መፅሐፍት ሌላኛው “Bathroom Reader” (ለመታጠቢያ ቤት አንባቢ) የሚል ጠቅላይ ርእስ ያለው ነው፡፡ በ“Bathroom Reader” ኢንስቲትዩት እየተዘጋጀ የሚቀርብ ተከታታይነት ያለው መፅሐፍ ነው፡፡ ለትህትና መታጠቢያ ቤት ይባል እንጂ አላማው መፀዳጃ ቤት ነው፡፡ ሽፋኑ ላይ የመፀዳጃ ቤት ወረቀት፣ የመፀዳጃ ቤት ውሃ መልቀቂያ ይታያል፡፡ ከመፀዳጃ ቤት ወረቀቱ ጋር መፅሐፉ ቦታ ተጋርቷል፡፡ የመፅሐፉ አላማ በመፀዳጃ ቤት ቆይታ ወቅት የተመጠነ እውቀት ማስተላለፍ እንደሆነ ከርዕሱ እና ከሽፋን ምስሉ እንረዳለን፡፡ የፅሁፎቹ መጠን እንደ መፀዳጃ ቤት ቆይታችን እንድንመርጣቸው ሆነው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ አጭር (Short)፣ መካከለኛ (Medium)፣ ረጅም (Long) እና ሰፋ ያለ (Extended) በሚል ተከፋፍለዋል፡፡ ይሄን መፅሐፍ ልብ ብዬ ባየሁ ቁጥር አንድ ቀልድ ትዝ ይለኛል፡፡

መፀዳጃ ቤቱ የጋራ የሆነበት መንደር ውስጥ ነው፡፡ ልጁ ገብቶ ብዙ የቆየባቸው ተጠቃሚዎች እየተነጫነጩ ነው፡፡ ከመካከላቸው አንዱ አዛውንት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ልጁን ያናግሩታል፤

“ሰማህ አንተ ልጅ”

“አቤት”

“ሽንት ቤቱን ብቻህን ያዝከው’ኮ፡፡ እኛም መጠቀም እንፈልጋለን፣ ለምን አትወጣም?”

ልጁ ውስጥ እንዳለ ይመልሳል፡-

“ቢወጣስ የት ይኬዳል?”

እኛ ከምናውቀው የጋራ መፀዳጃ ሽታ በላይ የከረፋ የሥራ አጥነት አለም ልጁን ይጠብቀዋልና ተደበቀበት፡፡ ቀልድ ይመስላል እንጂ መራር እውነት ነው፡፡

...እና (በእኛ ዓይን) የቀበጡቱ ፈረንጆች መፀዳጃ ቤት ተቀምጦ የሚባክን ጊዜን ሥራ ላይ ለማዋል “Bathroom Reader” አቀዱና ተገበሩ። መፅሐፉ ግን “መፅሐፍ” ነው፡፡ ታሪክ፣ አስቂኝ ገጠመኝ፣ ፖለቲካ፣ ሥነ-ፅሁፍ፣ ጥያቄና መልስ፣ ሥነ-ልቦና... ያልያዘው ነገር የለም፡፡ ያለ መፅሐፉ አላማ መኖሪያ ቤት ውስጥ እያነበብኩት ነው፡፡ እንኳን መፀዳጃችን ከተማችን እንደ ጋራ ሽንት ቤት በከረፋችበት አግባብ ሌላ ምን አማራጭ አለ?

ሦስተኛው ሳየው የሚያስቀኝ መፅሐፍ “100 MISTAKES THAT CHANGED HISTORY” (ታሪክ የቀየሩ መቶ ስህተቶች) የሚል ርእስ አለው። መግቢያው እንኳን “History Making Mistake” (ታሪክ ሰሪው ስህተት) የሚል ንዑስ ርዕስ ተሰጥቶታል፡፡ ታዲያ እኛ ምን ሆነን ነው “ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ ነው” እያልን የከረምነው? ከዚህ መፅሐፍ አንፃር “ቆራጡ” (ምናምን) የሚባል መሪ የለም፡፡ ወይም ይቺ አለም እዚህ የደረሰችው በታቀደላት ቀጥተኛ መንገድ ተጉዛ ሳይሆን መሪዎችና ሌሎች ተሳስተው በፈጠሩት ክስተት ነው፡፡ ስለዚህ “Your Kingdom, or your life is a mistake” ይላል መፅሐፉ፡፡ ይሄንንም ለማስረገጥ መቶ ስህተቶች እንዴት የዓለምን ታሪክና ገፅታ እንደቀየሩት ያስነብባል፡፡

2500 ዓመታት ወደኋላ ተጉዞ የአይኦኒያን ከተማ ከሆነችው ከሚሊተስ (Miletus) መሪ አሪስታጐራስ (Aristagoras) ስህተት ይጀምራል። የአሪስታጐራስ ስህተት ምዕራብ አውሮፓ አሁን ባለችበት ሁኔታ እንድትገኝ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ አሪስታጐራስ የፐርሺያውን ንጉስ ቀዳማዊ ዳሪየስ አስደስቶ ለመሾም ለመሸለም ሲል ያመፀችውን የናክሶስ ከተማ ለመውረር ተነሳ፡፡ ድል ሳይቀናው ቀርቶ ተሸነፈ፡፡ ለመሸነፉ ከባቢሎን ንጉስ የሚደርስበትን ቅጣት ያውቃልና የአካባቢውን ከተሞች በባህል ስም ለአመፅ አስተባበረ፡፡ “ቋንቋችንና ባህላችን ለግሪክ እንጂ ለፔርሺያ ባእድ ነው፡፡ ስለዚህ ባቢሎናውያንን አንቀበልም” አለ። የአቴንስንና የመላው ግሪኮችን ድጋፍ አግኝቶ ቢዋጋም ከፔርሺያዎች ሽንፈት አላመለጠም፡፡ በዚህ ስህተት አውሮፓ ከግሪክ ግለሰብን ማዕከል ካደረገ ባህል ባሻገር ጠንካራ ማዕከላዊነት ያለውን የፔርሺያ ባህል ለማካተት ተገደደች፡፡ በዚህም አሁን ያለችውን ሆነች፡፡

ይሄ የመፅሐፉ ጅማሬ እስከ 2008 ዓ.ም የአውሮፓ የኢኮኖሚ ድቀት ድረስ ይጓዛል፡፡ እና ብዙ የፖለቲካ፣ የሳይንስ፣ የማህበራዊ ህይወት ስህተቶች የቀየሩትን ታሪክ ያሳየናል፡፡ እንዲህ ያለው ምርምር ከታሪክ ጋር በባላንጣነት ከመኖርና እሱኑ ከማመንዠግ አይገላግልም ትላላችሁ፡፡

አራተኛውን ልብ ብዬ ሳየው የሚያስቀኝን ያገኘሁት ከወደ ሩሲያ ነው፡፡ ሊያኪሚንኮ (LYAKIMENKO) የተሰኘ የሥነ ፅሁፍ ተመራማሪ፣ ሾሎሆቭ (Sholokhov) የተሰኘ ደራሲ ሥራዎች ላይ ጥናት ያካሄደበት መፅሐፍ ነው፡፡ ርእሱ “Sholokhov፡ A Critical Appreciation” (ሾሎሆቭ፡ የማድነቅ ሂስ) ይሰኛል፡፡ ማድነቅ ብቻ ከሆነ ምኑን ሂስ ሆነ? ስህተት ፈልጐ ማጣት አንድ ነገር ነው፤ ስህተትን ወዲያ ብሎ ማድነቅን ብቻ በማነፍነፍ እንዴት ሂስ ይሰራል? እያልኩ መፅሐፉን ሳየው ያስቀኛል፡፡

ሌላኛው መፅሐፍ የማርክ ክሪክ ነው፡፡ “The Household Tips of the Great Writers” ይሰኛል፡፡ መፅሐፉ በቤት አያያዝና በአትክልት ቦታ እንክብካቤ ውስጥ አጣማጅ አድርጐ ያላነሳቸው ደራሲዎች የሉም፡፡ ፍራንዝ ካፍካ፣ ጄን ሀውስቲን፣ ማርሲል ፕሩስት፣ ኤርነስት ሔሚንግዌይ፣ ቬርጂንያ ዎልፍ፣ ቶማስማን፣ ሆሜር፣ ቻርልስ ዲከንስ፣ ሐሮልድ ፒንተር፣ ጆን ስቴንቤክ፣ ሚለን ኩንዴራ፣ ኤሚል ዞላ፣ ዤን ፖውል ሳርት፣ ኤድጋር አለን ፖ... የሚገርመው ግን አንዱም የሉም፡፡ ደራሲው በፀሐፊዎቹ ስታይልና የሥነ ፅሁፍ አይነት የቤት አያያዙን፣ የመታጠቢያ ቤት እንክብካቤውንና የአትክልት ስፍራ አያያዙን ፅፎ አቅርቧል፡፡ አሁን ይሄ ማታለል ነው ወይስ...?

እንዲህ ያሉ “ግራ” ሥራዎችን ወደፊት እየመላለስን እንዳመቻችን እንመለከታለን፡፡

## የፍቅር ጥግ

### (ስለውበት)

- ውበት ሌላ ሳይሆን እውነታ በፍቅር አይን ሲታይ ነው፡፡

*ራቢንድራናዝ ታጎር*

- ውበት፤ ዘላለማዊነት ራሱን በመስተዋት ሲመለከት ነው፡፡

*ካሊል ጂብራን*

- ውበት ከወይን ጠጅ ይብሳል፤ ባለቤቱንም ተመልካቹንም ያሰክራል፡፡

*አልዶስ ሁክስሌይ*

- ውበት፤ ጥሩ የትውውቅ ደብዳቤ ነው፡፡

*የጀርመናውያን ምሳሌያዊ አባባል*

- ውበት በዕለት ሥራ ውስጥም ይገኛል፡፡

*ማሚ ሲፐርት በርንስ*

- ውበት፤ የእግዚአብሔር የእጅ ፅሁፍ ነው፡፡

*ቻርለስ ኪንግስሌይ*

- ሰዎች ውበት ውስጣዊ ነው ይላሉ፡፡ እኔ ግን ከቆንጆ ኩላሊት ይልቅ ቆንጆ ፊትን እመርጣለሁ፡፡

*ያልታወቀ ምንጭ*

- ውበት የአፍቃሪ ስጦታ ነው፡፡

*ዊሊያም ኮንግሪቭ*

- ውበት የሚጠወልግ አበባ ነው፡፡

*ምሳሌያዊ አባባል*

- አካላዊ ውበት እንደተመልካቹ ሊሆን ይችላል፤ ውስጣዊ ውበት ግን ከውስጥ የሚያበራ በመሆኑ ማንም ሊከደው አይችልም፡፡

*ኒቫን ፓንዋር*

- የሴት እውነተኛ ውበት ያለው ቆዳዋ፣ ፀጉሯ ወይም ተክለ ሰውነቷ ላይ አይደለም ... ልቧ፣ ነፍሷ፣ መንፈሷ ላይ እንጂ፡፡

*አሌክሳ ዶልም*

- ለውስጣዊ ውበታችሁ ስትል የምትወዳችሁ ብቸኛዋ ሴት እናታችሁ ናት፡፡

*ያልታወቀ ምንጭ*

- በዙሪያችሁ ውበትን በፈጠራችሁ ጊዜ ሁሉ ነፍሳችሁን እያደሳችሁ ነው፡፡

*አሊስ ዎከር*

- ሴቶች ሆይ፤ ውበት የሚተረጎመው በጂንስ ሱሪያችሁ ልክ አይደለም፡፡

*ሮበርት እስካሌት*

### ሳይንስ ከገፅ 12 የዞረ

የሚታጠቡበት ወይም እጅግ ምርጥ ‹አንቲባዮቲክ› ሆኖ የሚያገለግለው ውሃ መሆኑን ታውቃላችሁ›› ይላሉ፤ ፕሮፌሰር ሮይ፡፡ ‹‹ታዲያ ይህ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው?›› ሲሉ ይጠይቃሉ ፕሮፌሰሩ፤ ጠርሙሱን በእጃቸው ይዘው እያገላበጡ፡፡ ‹‹ታዲያ ይህን ነገር እንዴት ውሃ ልንለው እንችላለን›› በማለት ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት፤ የውሃው ኬሚካላዊ ባህርይ አይቀየርም፡፡ ያው የተለመደው H2O ነው፡፡ ‹‹የውሃ ሞሎኪላዊ መዋቅር (Molecular Structure) በእጅጉ ይቀያየራል፡፡ በዚህ ጉዳይ እጅግ ወሳኙ ነገር፤ የውሃው ኬሚካላዊ ባህርይ ሳይሆን የውሃው ሞሎኪላዊ መዋቅር (Molecular Structure) ነው›› የሚሉት እኚሁ ፕሮፌሰር፤ የውሃ ሞሎኪላዊ መዋቅር (Molecular Structure) ስንል፤ ሞሎኪሎቹ እርስ በእርስ ሲያያዙ የሚፈጥሩት መዋቅራዊ ቅርፅ (ስርዓት) ነው፡፡ ይህ ሞሎኪላዊ መዋቅር ቅርፅ የሚፈጠረውም፤ የተወሰኑ የውሃ ሞሎኪዩል ቡድን ወይም ክለስተር በሚፈጥሩት ቅርፅ ነው፡፡ ቅርፁን በአጉሊ መነፅር ስንመለከተው፤ ልዩ ልዩ ውብ ወይም አስቀያሚ ምስል እንመለከታለን፡፡

ስለዚህ፤ ውሃ በአካባቢው ያለውን ሁኔታ እየተከተለ፤ የውሃ ክለስተሮች የሚሰሩት ቅርፅ የተለያየ ይሆናል፡፡ በዚህ መንገድ፤ ውሃ ልክ እንደ ‹‹ማግኔቲክ ቴፕ›› በዙሪያው ያለውን ነገር ይመዘግባል። ለምሣሌ፤ መብራት ሲበራ ወይም ሲጠፋ የውሃው ሞሎኪላዊ መዋቅር (Molecular Structure) ይቀየራል፡፡ ከኬሚካላዊ ይዘት አንፃር፤ ውሃ - ውሃነቱ አይቀየርም፡፡ ሆኖም ሞሎኪላዊ መዋቅሩ (Molecular Structure)፤ ከውጭ (በአካባቢው) እንዳለው ነገር ሁኔታ ይቀያየራል፡፡ እንደ አንድ ሰው የነርቭ ስርዓት፤ ከውጭ ለሚያጋጥመው ነገር ምላሽ ይሰጣል ወይም react ያደርጋል፡፡

በእያንዳንዱ የውሃ ‹‹አስታዋሽ ሴል›› ውስጥ (memory cells) 440 ሺህ የመረጃ ቧንቧዎች አሉ፡፡ እያንዳንዱ ባንቧም የየራሱን የመረጃ ዓይነት የመመዝገብ ሚና ይጫወታል፡፡ እናም በዚህ

ሳይንስ ወደ ገፅ 22 ዞሯል

# ሁለት ፅንፎች

መሐመድ ነስሩ

አጭር ልብወለድ




አያት፡፡ አየችው፡፡

ከአዲሱ ገበያ ወደ ቄራ በምትሄደው 6 ቁጥር አውቶብስ ውስጥ ናቸው፡፡ መጀመሪያ እሱ ነው ያያት፡፡ የቀይ ዳማ ናት፡፡ ውብ የሆኑ ትልልቅ ዓይኖች ታድላለች፡፡ ረዘም ያለ ፀጉር አላት፡፡ ጸጉርዋ የተፈጥሮ ይመስላል፡፡ ግን አርቴፊሻል ነው፡፡ ሂውማን ሄይር! ... ቢሆንም አስውቧታል፡፡ ቅንድብዋና ሽፋሽፍትዋ “እኔ ነኝ ጥቁር ... እኔ ነኝ ጥቁር” እያሉ ከፀጉርዋ ጋር ይፎካከራሉ፡፡ አንገትዋ ረዘም ያለ ነው፡፡ ብርሌ አንገት! እሱ የሚወደው ዓይነት!... አንገቷ ላይ ያንጠለጠለችው የአንገት ሐብል የብር መስቀል ነው። በጡቶችዋ መሀል ይጫወታሉ፡፡

ከአንድ ቦታ ነው የተሳፈሩት፡፡ ካያት በኋላ ቲኬት ለሁለቱም ቆረጠ፡፡ ቲኬቱን እንቺ አላት፡፡

“ምንድን ነው?”

“ቲኬት!”

“የምን ቲኬት?” አለች ግራ ገብቷት፡፡

“የአውቶብስ መጓጓዣ ቲኬት ነው ... ያዢው!”

ተቀበለችው፡፡ እና በሙሉ ዓይንዋ አየችው። ጠይም ነው፡፡ እሷ ደግሞ ጥሎባት ጠይም ወንድ ትወዳለች፡፡ እንደ ዘንግ ቀጥ ያለ አፍንጫ አለው። ፀጉሩን አሳድጎታል፡፡ አሳድጎ ፈርዞታል፡፡ ያምርበታል፡፡ ያምራልም፡፡ አጠገብ ለአጠገብ ነው የቆሙት፡፡

መካከለኛ ኑሮ የሚኖር ቤተሰብ ልጅ ነች፡፡ ስልክ ይዛለች፡፡ ሳምሰንግ፣ ጋላክሲ፡፡ ኤርፎን ጆሮዋ ላይ ሰክታ ሙዚቃ እየሰማች ነው፡፡ እሱም ስልኩን ላውድ ላይ አድርጎ ሙዚቃ እያዳመጠ ነው፡፡

“ይቅርታ ረበሽኩሽ?” አላት

“በምኑ?”

“በሙዚቃው”

“ኧረ ችግር የለውም”

“ምንድነው የምታዳምጪው?” አለ የኤርፎንዋን ገመድ በእጁ ነካ እያደረገ፡፡

“ሙዚቃ ...”

“የምን ሙዚቃ ... ማለቴ ... አማርኛ ነው እንግሊዝኛ?”

“እንግሊዝኛ”

“የኔ እህት፤ እኔ እንኳን እንግሊዝኛ አማርኛ እራሱ እንደፓንት ነው ያጠረኝ”

“ምን አልከኝ?”

“አይ...ጥሩ ነው፡፡ ደስ ይላል!”

“ሙዚቃ አትወድም?”

“እወዳለሁ ... በተለይ ደሀ የሚል ቃል ያለበት ዘፈን በጣም እወዳለሁ!”

“ለምን?”

“ደሀ ስለሆንኩ”

ፈገግ አለች፡፡

“አሁን ለምሳሌ ነዋይ ደበበ የኔ ደሀ ሲል እኔን የሚጠራኝ እየመሰለኝ ብዙ ጊዜ ‹አቤት!› እላለሁ”

“እኔ ግን የሰው ደሀ አለ ብዬ አላስብም!”

“እንዴት?”

“ሙሉ አካልና ሙሉ ጤና ያለው ሰው ቀርቶ የሌለው እንኳን አዕምሮ በመታደሉ ብቻ ሀብታም ነው ብዬ አምናለሁ!”

“እኔ ደግሞ ድህነቴን አምኜና ተቀብዬ የምኖር ሰው ነኝ! አይገርምሽም?”

“እስኪ ስለድህነት ንገረኝ” አለችው ፈገግ እንዳለች፡፡

“ከሚታየው ልጀምርልሽ?”

“እሺ”

“አሁን ለምሳሌ ይሄን ስልክ የገዛሁት ከሰፈር ልጆች ጋ ከመኪና ዕቃ ስናወርድ የማገኘውን ገንዘብ አጠራቅሜ ነው፡፡ ወላጆቼ ደሀ ናቸው፡፡ ያደግሁት በድህነት ውስጥ ነው፡፡ ወጪ ለመቀነስ በቀን ሁለቴ የሚበሉትን ሰዎች በዕውቀቱ ስዩም ቁምሳ ነው የሚበሉት ይላል፡፡ አምስት ሰዓት ላይ ቁርስ፤ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ምሳ፡፡ እኛ ቤት ግን እንኳን ምሳ ወይም እራት ብቻ ሊዘለል ይቅርና ቀኑን ሙሉ እህል ሳንቀምስ ውለን የምናድርባቸው ብዙ ቀናት ነበሩ፡፡”

አዘነች፡፡ እውነቱን ሳይደብቅ ስለነገራት ደስ አላት፡፡ አደነቀችው፡፡ በራስ መተመኑና ምንም ሳይሸማቀቅ ይህን መናገሩ ብስለቱን ያሳያል አለች። ብዙ ወንዶች እንደዚህ አይደሉም፡፡ እንደውም ይዋሻሉ፡፡ ያላቸው መስለው ለመታየት ይጥራሉ፡፡ እሷ ደግሞ ከምንም ነገር በላይ የምትጠላው፤ ውሸት ነው፡፡ በተለይ ወንድ ሲዋሻት ቅጥል ትላለች፡፡ ደግሞ ታሪክም አላት፡፡ በዚህ ዙሪያ የሚሽከረከር ታሪክ፡፡

የቀድሞ ጓደኛዋ ብዙዓለም ይባላል፡፡

መንገድ ላይ ነው የተገናኙት፡፡ ከመሳለሚያ ወደ አውቶብስ ተራ እየተጓዘች ነበር፡፡ ዝናብ እያካፋ ነው፡፡ ጃንጥላ መያዝዋን ያስተዋለ ወጣት ተጠጋት፡፡

“ይቅርታ ጃንጥላው ለሁለት ይበቃናል?” አላት በጥላዋ እየተጠለለ፡፡

ዝም አለችው፡፡

ዝምታዋን እንደ እሺታ ወሰደው፡፡ ማውራት ጀመሩ፡፡

“መኪናዬን እኮ አሁን ጋራዥ አስገብቼ መምጣቴ ነው ... ለዚህ ነው የተቸገርኩት፤ ተቸግሬ ያስቸገርኩሻ” አለ ብዙዓለም፡፡

“ኧረ ችግር የለውም” አለችው፡፡

“ቦሌ አካባቢ አንድ የቢዝነስ ቀጠሮ አለኝ... ለዚያ እየቸኮልኩ ነው ... ታክሲ የሚባል ደግሞ የለም፡፡

“አውቶብስ ተራ ጋር ታገኝ ይሆናል”

“አዎ! እኔም እሱን ነው ተስፋ ያደረኩት”

ስታየው ጠይም ነው፡፡ ቆንጆ አይደለም፡፡ ግን እንደከዋክብት የሚያበሩ ዓይኖች አሉት፡፡ ጠይም ነው፡፡ ጠይምነቱ ልቧ ላይ ጠብ፣ ነፍሷ ላይ ጥብቅ ብሏል፡፡ ሲያወራም ደስ ይላል፡፡

አድራሻ ተለዋወጡ፡፡ እና ተለያዩ፡፡

በቀጠሮዋቸው ዕለት ሲገናኙ ለመዘነጥ ሞክሮ ነበር የመጣው፡፡

እንደተገናኙ “ህሊናዬ!” ብሎ ተጠመጠመባት፡፡

“እንዴት ነህ ብዙዓለም?”

ተቀመጡ፡፡

በጫወታ መሀል፤ “ስራህ ግን ምንድን ነው?” ብላ ጠየቀችው፡፡

“ፋርማሲስት ነኝ ... ቦሌ አካባቢ ትልቅ ፋርማሲ አለኝ .. ገብቶሻል አይደል አባባሌ ... መድኀኒት መደብር አለኝ”

“ራስህን ችለኃላ?”

“እግዚአብሔር ይመስገን ለቤተሰቦቼ ተርፌያለሁ”

“ቤተሰቦችህ ችግረኞች ነበሩ?”

“ኧረ በጭራሽ ... አባቴ የአየር መንገድ ሜካኒክ ነው፤ እናቴ ነርስ ናት .. አንቀባረው ነው ያሳደጉን!”

“ደስ ይላል” አለችው፡፡

ብዙዓለምና ህሊና ተላመዱ፡፡ ተዋደዱ፡፡ ፍቅር ተጀመረ፡፡ ለወራት ያህል አብረው እንደቆዩ ህሊና ሌላ ታሪክ ሰማች፡፡ እውነቱን ማወቁዋ ደስ አላት፡፡ የነገራት ሁሉ ውሸት መሆኑን መረዳትዋ አቃጠላት፡፡ ብዙዓለም ደሀ ነው፡፡

ብዙዓለም የደሀ ልጅ ነው፡፡

ደሀ በመሆኑ ሳይሆን ውሸታም በመሆኑ ጠላችው፡፡ አውቶብስ ተራ አካባቢ በሚገኝ አንድ ካፌ ውስጥ አስተናጋጅ ነው፡፡ ስራው ሳይሆን ማንነቱ (የውሸት ማንነቱ) እንድትጠላው አደረጋት። እንደሞኝ ስላታለላትና እንደተራ ዕቃ በገንዘብ ሊሸውዳትና ሊገዛት የሚሞክር መሆኑን ስታውቅ በዓይኔም አልየው አለች፡፡

ቤተሰቦቹ በጨረቃ ቤት የሚኖሩ ደሀ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ስታውቅ ይህን ሁሉ ውሸት ምን አመጣው በሚል ተንገሸገሸች፡፡ ቀጠረችው፡፡ የሆድ የሆድዋን አውርታ ልክ ልኩን ነግራው (እሷ እንደምትለው) ተለየችው፡፡

ይኸው እዚህ ደግሞ ድህነቱን በነፃ ሳይሸማቀቅ የሚያወራ፣ በራስ መተማመን ያለው ወንድ ገጠማት። ወንድ ሁሉ በውሸት ‘ራሱን የሚክብ፣ በሴት ለመወደድ አለሁ አለሁ የሚል ይመስላት ነበር፡፡ አሁን እዚህ ግን የድህነቱን ጥልቀት በተባ አንደበት የሚያብራራላት ወንድ ገጠማት፡፡ ታሪክዋና እውነቱ ተላተሙ፡፡ ከብዙዓለም በኋላ ወንድ አላምንም ብላ ነበር፤ ወንዶች ሴትን እንደዕቃ ነው የሚያዩዋት፤ በብር ኃይል ሊገዟት የሚችሉ፤ በገንዘብ ተኀትታ የምትመጣ ጠቦት ናት ብለው የሚያምኑ ይመስላት ነበር አልሆነም፡፡

እነሆ እዚህ አሁን የተለየ ወንድ ተገኘ፡፡

“አሁን ለምሳሌ እዚህ ስልክ ላይ ያስጫንኩትን ዘፈን ለምን እንደዚህ ከፍቼ የማዳምጥ ይመስልሻል?”

“ለምንድነው?”

“ሄድፎን መግዣ የሌለኝ ደሀ ስለሆንኩ ነው፤ እንጂ እንዳንቺ ሰው ሳልረብሽ ለ‘ራሴ ብቻ ማድመጥ የማልፈልግ ይመስልሻል?”

“ለየት ያልክ ሰው ነህ!” አለችው

“እንዴት?”

“እኔ‘ጃ ... እንዲሁ”

ድንገት ተጠራች፡፡ እዛ ማዶ ከተቀመጡ እናት አጠገብ አንድ ሰው ሊወርድ ሲነሳ “ህሉ ነይ እዚህ” ብለው ተጣሩ፤ እናትየው፡፡ “እናቴ ናት” ብላው ወደዚያው አመራች፡፡ የሚሄዱበት ደርሰው ሲወርዱ፣ ያለመውረጃ ቦታው ተከትሏቸው ወረደ፡፡

ከኋላ ኋላ እየሄደ ስልኩን ወረቀት ላይ ፅፎ አንድ ህፃን አስይዞ ወደ እሷ ላከው፤ ዞር ብላ አየችው፡፡ ተጠቃቀሱ፡፡

የዚያኑ ቀን ደወለችለት፡፡

ስልኩን አንስቶ “ማን ልበል?” አለ፡፡

“ቅድም የተዋወቅኩህ ልጅ ነኝ፤ አውቶብስ ውስጥ ...”

“እእ... እንዴት ነሽ?”

“ደህና ነኝ.... ስም እንኳን ሳንለዋወጥ አይደል?” አለችው እንደማፈር እያለች፡፡

“ዮናታን እባላለሁ!” አላት፡፡

“ህሊና እባላለሁ!” አለችው፡፡

“ስለደወልሽልኝ በጣም ደስ ብሎኛል ... ይኼ ስልክ ያንቺ ነው?”

“አዎ ሴቭ አድርገው!”

መገናኘት ጀመሩ፡፡ ተግባቡ፡፡ ተዋደዱ፡፡ ተጣመሩ፡፡

ውሸት እንደምትጠላው አውቆ ነው መሰል፤ አድብቶ ይከታተላታል፡፡ የዮናታንም ታሪው ውሸት

ጽንፎች ወደ ገፅ 20 ዞሯል

## ኪነጥበባዊ ዜና

ናፍቆት ዮሴፍ

### “ደሳሳው ጎጆ” መፅሐፍ ይመረቃል




“The Shack” የተሰኘው የደራሲ ዊሊያም ፒ ያንግ ልብ አንጠልጣይ ልብወለድ መፅሀፍ በተርጓሚ ኃይል ከበደ “ደሳሳው ጎጆ” በሚል ወደ አማርኛ ተመልሶ ሰሞኑን ለንባብ በቃ፡፡ መጽሃፉ በመጪው ሚያዚያ 23 ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ፊት ለፊት ከሼል ማደያው ጀርባ በሚገኘው ኤስአይኤም ዋና ፅ/ቤት አዳራሽ እንደሚመረቅም ለማወቅ ተችሏል። “ደሳሳው ጎጆ” በ194 ገፆች የተቀነበበ ሲሆን ለአገር ውስጥ በ44 ብር ከ90፣ ለውጭ አገር በ14.99 ዶላር ለገበያ ቀርቧል፡፡

ተርጓሚና ደራሲው ከዚህ ቀደም “የፓንዶራ ሙዳይ”፣ “የፍጥረቴ ሩጫ”፣ “ጉርሻና ፌሽታ” እና “ምስካይ” የተሰኙ የጥበብ ስራዎችን ማሳተሙ ይታወሳል፡፡


### 3ኛው አገር አቀፍ የቴአትር ፌስቲቫል ይካሄዳል

*ቴአትሮች ተወዳድረው ይሸለማሉ*

በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ከ10 ዓመት በላይ የሰራው ተስፋ ኢንተርቴይንመንት፣ ከህይወት ፕሮሞሽንና ኮሚዩኒኬሽን ጋር በመተባበር 3ኛውን አገር አቀፍ የቴአትር ፌስቲቫል በአዳማ ከተማ ኦሊያድ ሲኒማ ያካሂዳል፡፡ በፌስቲቫሉ ለእይታ ቀርበው በዳኞች የሚወዳደሩ ስምንት ቴአትሮች የተመረጡ ሲሆን ከብሔራዊ ቴአትር “ባቢሎን በሳሎን” እና “ቅጥልጥል ኮከቦች”፣ ከሀገር ፍቅር “የበዓል እንግዶች”፣ “ትዳር ሲታጠን” እና “የጉድ ቀን” እንዲሁም ከግል የቴአትር ኢንተርፕራይዞች “የፍቅር ካቴና”፣ “ብር አምባር” እና “ወንድ አይገባም” የተሰኙት ቴአትሮች መመረጣቸውን የተስፋ ኢንተርቴይንመንት ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ አቶ ተፈራ ወርቁ ገልፀዋል፡፡ ፌስቲቫሉ ከሚያዚያ 24 እስከ ግንቦት 1 ሊካሄድ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በሊቢያ በኢትዮጵያዊያን ወገኖች ላይ በተፈፀመው ግድያ ሃዘን ምክንያት ፌስቲቫሉ ለአንድ ሳምንት መራዘሙንና ከግንቦት 1-9 እንደሚካሄድም ለማወቅ ተችሏል፡፡ ብዙ ተዋንያን ያላቸው እንደነ “የቴዎድሮስ ራዕይ”፣ “ቶፓዝ” እና “ግይድ” የመሳሰሉ ቴአትሮች በበጀት እጥረት ሳቢያ አዳማ ሄደው መታየት ባይችሉም እዚሁ አዲስ አበባ በዳኞች ታይተው እንደሚወዳደሩ ተገልጿል፡፡

አንደኛውና ሁለተኛው አገር አቀፍ የቴአትር ፌስቲቫል በአዲስ አበባ መካሄዱን ያስታወሱት አቶ ተፈራ፣ የአሁኑ አዳማ የሚካሄደው ፕሮግራሙን ለየት ለማድረግና ለአዳማ ህዝብ ቴአትሮቹን ለማሳየት ታስቦ ነው ብለዋል፡፡ ወደፊት በሌሎች ክልሎችም ፌስቲቫሉ እንደሚካሄድ አክለው ገልጸዋል፡፡ ቴአትሮቹ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተውጣጡ የቴአትር ምሁራን የሚዳኙ ሲሆን አሸናፊ ቴአትሮች፣ ተዋንያንና ደራሲና አዘጋጆች በየዘርፉ ይሸለማሉ ተብሏል፡፡

### “የምስጢር መንትዮች” መፅሀፍ ተመረቀ




በተዘራ አስናቀ የተደረሰውና በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተው “የምስጢር መንትዮች” ታሪካዊ ልብወለድ መፅሐፍ በትላንትናው ዕለት በሩሲያ የሳይንስና የባህል ማዕከል ተመርቋል፡፡ መፅሃፉ የማህበረሰባችንን እውነተኛ ገፅታ፣ ድህነት፣ ዕውቀት፣ አስተሳሰብና የባህል ተፅዕኖዎች እያደረሱ ያሉትን ውጣ ውረድ አጉልቶ ያሳያል ተብሏል፡፡ በምረቃ ስነስርአቱ ላይ የተለያዩ የጥበብ ባለሙያዎች ግጥም፣ ወግና መነባንብ ያቀረቡ ሲሆን ኮሜዲያኖችም ታዳሚውን አዝናንተዋል፡፡ በ242 ገፆች የተመጠነው መፅሐፉ፣ በ38 ብር እየተሸጠ ነው፡፡

# ‹‹ዞዝ!›› ወ ጥበብ

## “የብሔራዊ ትያትሩ አንበሳ ፊቱን ስምን አዞረ?”

ተሊኒዮስ አትናቴዎስ

እናት፤ ቀኑን ሙሉ ተጎልቶ ፊልም በማየት ከቤት አልወጣ ያለ ልጃቸውን እርሱ ባለበት በቤት ስልክ ለሚያዋሯቸው ወዳጃቸው ሲገልፁ ምን ቢሉ ጥሩ ነው... ‹‹የእሱን ነገር አታንሺብኝ፤በቃ ‹ዞዝ› ሆኖብኛል!››

*ዞዝ*
*የማትንቀሳቀሰው የማትሄደው፣*
*ትናንትም ዛሬም እዛው፣*
*ልበ ደንዳናው ግኡዝ፣*
*አንድ ወጡ ዞዝ፣*
*ሰሜን ወገራን ተጓዝኩ፣*
*በለሳን ጋይንትን አለፍኩ፣*
*ዘወር ብዬ ባስተውልህ፣*
*ዞዝ! ዛሬም እዛው ነህ?! ...*

ዞዝ ምንድን ነው? እነሆ ይኼን ጥያቄ ባጭሩ ብቻ እመልሰው ዘንድ ወደድኩ፡፡ በኔና በውድ አንባቢያን መካከል እንዳንተያይ የሚጋርደን አንዳችም ነገር (ዞዝ) እንዲኖር አልፈቅድምና፡፡ ዞዝ የተራራ ስም ነው፡፡ ምን አይነት ተራራ? የት የሚገኝ? እና አሁን እንዴት እዚህ ሊነሳ ቻለ? ያውም የጥበብ አምድ ላይ? ዝርዝሩን በጽሑፌ ውስጥ ከተለያዩ ሀሳቦች ጋር እያሰናሰልኩ መመለስ መረጥኩ እንበል፤ በቃ ይኼም በራሱ አንድ ዞዝ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የግልፅነት፣ ምላሽ የማንቀራፈፍ፣ የንፉግነት...ወዘተ ዞዝ!

ክቡራትና ክቡራን አንባቢያን፤ ‹‹ዞዝ›› በራሱ ስልጣን (የስልጣንም ዞዝ አለ) የአንድን ከደርግ አፈ ሙዝ (ዞዝ) በተአምር የተረፈን ኢትዮጵያዊ ታጋይ ውብ የእድሜ ዘመን አንክቶ ከበላ የግጥም መድበል መካከል እደግመዋለሁ፤በራሱ የጥበብ ኃይል ተመዝዞ ወጥቶ ከተፃፈ ከ35 አመታት በኋላ ለዚህ ዘመንም የተስማማና በተለይም ሰሞኑን በከተማችን ውስጥ ተምሳሌታዊ፣ ሀሳብ ወካይ የመግባቢያ ቋንቋ Metaphor እስከመሆን የደረሰ ብርቅዬና ድንቅዬ፣ እንግዳና ቤተሰባዊ የግጥም ውበትና ጉልበት መገለጫ ‹‹ቃል›› ነው፡፡ ለምሳሌ ጓደኛዋ አብራው እንድትቆይ የጠየቃት ኮረዳ፤ አባቷ ወይም ታላቅ ወንድሟ ከፊልድ መመለሱን ነግራው ‹‹እኔም እፈልግ ነበር ፍቅሬ፤ ግን በኋላ ደሞ ቤት ስገባ ‹እስካሁን የት ነው ያመሸሽው?!› ብሎ አይኑን እያጉረጠረጠ ዞዝ ይሆንብኛል!›› ትላለች፡፡ ቀለል ማድረግም ይቻላል... ወዳጆች ሰብሰብ ብለው ሲጨዋወቱ ወይም በስራ ውጥረት ላይ ሆነው ድንገት መብራት ድርግም ቢል ‹‹ኤጭ! አሁንስ ይኼ መብራት ዞዝ ሆነብን'ኮ!›› ይባላል፡፡ ታክሲ ጠፍቶ ከቀጠሮ ብናረፍድ ለቀጠረን ሰው ‹‹ይቅርታ ትራንስፖርቱ ዞዝ ሆኖብኝ ነው›› እንደማለት፡፡ ተግባብተናል ብዬ ላስብና ልቀጥል... /ባለመግባባት ግብቡነትም እንግባባለን!/

ዞዝ - የቃሉ መገኛ ከሁለት ወራት በፊት ለንባብ የበቃው የታጋይ /አምባሳደር ህላዌ ዮሴፍ ‹‹ታሪክና ጥበብ›› የግጥም መድበል ነው፡፡ ህላዌ በመድበሉ ውስጥ በትግል ዘመኑ የከተባቸው 61 ያህል ግጥሞችን ያካተተ ሲሆን፤ ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነኝ ግን አንዱ ግጥሙ ብቻ ነው፡፡

በመግቢያ ገፆቹ በደራሲ ጌታቸው በለጠ ‹‹በትንታግ እሳት መሀል የተፃፉ ትንታግ ግጥሞች›› በሚል አርዕስት በቀረበው ቅኝት መካከል /ገፅ 30 ላይ/ ‹‹እያንዳንዱ ግጥም በምን ሁኔታና ጊዜ እንደ ተፃፈም በማብራሪያ ተደግፏል›› የሚል አረፍተ ነገር ሰፍሯል፡፡

በእርግጥም ይህ መሆኑ ገጣሚው ካስተዋለውና በስንኝ ከሰደረው Observations and Expressions ባሻገር ምናቡን በቅርብ እንጋራ ዘንድ ማገዙ ሀቅ ነው፡፡ ምናልባትም ሳይለው የቀረው ጉዳይም ቢኖር ስሜቱን ለመታከክ ይረዳል፡፡የግጥም ነገር በወረቀት ከቀረበውም በላይ ያልፋልና፡፡ ስታንሌይ ኩኒትዝ እንዲል...*"The poem on the page is only a shadow of the poem in the mind. And the poem in the mind is only a shadow of the poetry and the mystery of the things of this world."*

*ዞዝ ዛሬም እዛው ነህ?!*
*የት ሆኜ ነው የማላይህ?!*
*ከፊት ከጀርባዬ የማጣህ?!*
*‹‹ወንዞች ተሻገር! ድንበር ስበር፣*
*አገር አቋርጥ፣ ሂድ ብረር፣››*
*ነው የምትለኝ፣*
*ወይስ አትራቀኝ፣*
*ዞዝ!*
*አንተ ግዑዝ! ...*

ህላዌ ለዚሁ ዝነኛ ለሆነው ዞዝ የተሰኘ ግጥሙ የፃፈውን የግርጌ ማስታወሻ እንይ...

‹‹ዞዝ - በሰሜን ጎንደር ዞን በምዕራብ በለሳ ወረዳ (በቀድሞው ሊቦ አውራጃ በለሳ ወረዳ በዘሀዬ ምክትል ወረዳ) የሚገኝ፣ በአካባቢው ካሉት ተራራዎች ሁሉ ለየት ያለና የጠረጴዛ ቅርፅ ያለው፣ከሩቅና ከሁሉም አቅጣጫ የሚታይ ተራራ ነው፡፡ ከተራራው ግርጌ፣ላሊበላና ሰቆጣ አካባቢ የሚገኙ አይነት፣ከውቅር ድንጋይ የታነፀው ዞዝ አምባ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል፡፡

ዞዝ በኢሕአሠ የአመራር ብቃት መጓደል ምክንያት ካለበት አካባቢ ወጣ ብሎ መስፋፋት ያልቻለው የሪጅን ሦስት ሠራዊት አባላት እዛው በለሳ ውስጥ ስንንከላወስ ጧት ማታ የምንመለከተውና ከአይናችን የማይሰወር ተራራ ነበር፡፡ ግጥሙ እንደ ዞዝ ተራራ የተገተረውንና መነቃነቅ የተሳነውን የኢሕአሠ አመራር በሾርኒ የወረፍኩበትና የታጋዩንም ብሶት ለማንፀባረቅ የሞከርኩበት ግጥም ነው፡፡

መጀመሪያ ረቂቁን‹‹አብሩክ››ላይ ሆነን፣ተራራውን እያስተዋልኩ፣ ከተቃጠለ ዛፍ በተፈረካከሰ ጥቁር ከሰልና በቢክ እስክሪብቶ፣ በነጭ አቡጀዲ የአንገት ልብሴ ላይ ሞነጫጭሬ፣ ‹‹አዲ›› ውስጥ ባረፍን ጊዜ በወረቀት ላይ አስፋፍቼ አሰፈርኩት፡፡ ግጥሙ በለሳ ውስጥ የኢሕአፓ/ሠን አመራር የሚቃወመው ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄውን ማቀጣጠል በጀመረበት ወቅት፣ በተለይ በ1972 ዓ.ም፣ በሠራዊቱ ስብሰባዎች ላይ በተደጋጋሚ ተነቧል፡፡›› /ገፅ-48-49/

በመድበሉ ውስጥ ጋሽ ጌታቸው በለጠ፤‹‹ከሺህ ቃላት አንድ ስዕል የበለጠ ይናገራል›› ይላሉ›› ብሎ ያወደሳቸውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ጥበብ ረዳት ፕሮፌሰር ሰአሊና ገጣሚ በቀለ መኮንን ‹‹እሳትን ለመስራት እሳትን መብላት›› በሚለው የቅድመ ህትመት የመግቢያ ፅሑፉ ውስጥ‹‹በሰአሊዎቹ ነፃ ፈቃድ የተፈጠሩት ስልተ-ብዙ ስዕሎችና ከጋመ የሕይወት ውጣ ውረድ የተጨመቁት ስነ ግጥሞች የጣምራ ጉዞ ራሳቸውን በቻሉ የጣምራ ሰልፎች ሰምሯል ለማለት ይቻላል፡፡› ብሎ አድናቆቱን የቸራቸው ፤የበርካታ ሰዓሊያን፤ በግጥሞቹ ላይ ተመርኩዘው የሰሯቸው የስዕል ቅቦችም መካተታቸው የመድበሉን አቀራረብ አዲስ የሚያሰኘው ነው፡፡ የሚገርመው ታዲያ ዞዝ ግጥም በሰአሊያኑ መካከልም ልዩ ትኩረት ያገኘ ነበር፡፡ ገጣሚው በግጥሙ ዞዝን ከተራራነት ባለፈ በ‹ሾርኒ. የቀሸረበትን ሀሳብ ከእውነታዊነት Realistic በዘለለ የModern Art አሳሳል ለማማጥ፡፡ በመጨረሻም ግጥሙ የደረሰው ሰአሊ ዮናስ ደገፉ /ገፅ 46/ በሚገርም መንገድ አስቀምጦታል፡፡ በድጋሚም ሰአሊ ሰለሞን ኃይሉ፤ ‹‹ጓዶቻችን›› ለሚለው ግጥም ባበረከተው /ገፅ 156/ ስራው ዞዝንም በስእል ድርሰቱ ውስጥ አካትቶት ይገኛል፡፡

ይህ መነጋገሪያ ግጥም ግን በመፅሀፉ ምረቃ ዕለት (መጋቢት 27 ቀን 2007 ዓ.ም) የመነበብ እድል ካላገኙት መሀል ነበር አሉ፡፡ እኔ አልተገኘሁም፡፡ መረጃ የማግኘት ዞዝ ገጥሞኝ፡፡ እናም አልተጠራንም ወይም እንዳንሳተፍ ተገልለናል የሚሉ አኩራፊ የጥበብ ቤተሰቡ አባላት መኖራቸውንና ከእነርሱም አንዳንዶቹ በፊልም ሙያ እንደ የቲኬት ቀረጥና የአዳራሽ ኪራይ ዞዝ አናውዞናል ባዮች መሆናቸውን ሰምቻለሁ፡፡

በጣም ከባድ ይቅርታ፤ አርቲስቶች ግን መቼ ነው በጋራ የምትቆሙትና ህብረት የነሳችሁን ዞዝ ሰንኮፉን ላንዴው ነቅላችሁ የምትጥሉት? ስማ! እንትና ሲደማ፣ አብረህ ከምታማ፣ አንተም አብረህ ድማ! እንደ ታጋዩ ገጣሚ፤ ‹‹ደማቁ ደምህ ነው ህይወት የዘራብኝ፤አንተ ደሜ! የጓዴ ደም!›› ተባባሉ እስቲ? (SOLIDARITY!) በምረቃው ላይ ባለመገኘቴ እኔን የቆጨኝ ነገር ቢኖር ግን ሌላኛው ታጋይ በረከት ስምኦን በጣም የሚወደድለትን የትግል ዘመን ግጥሙን ‹‹መቸስ ምን እንላለን››ን ለወዳጁ መፅሀፍ ምረቃ በብሔራዊ ቴአትር መድረክ ላይ ቆሞ ማንበቡን ስሰማ ነው፡፡ *Poetry becomes alive when it is read aloud!*

ስለ ሰአሊያን ካነሳን አይቀር አንድ ነገር ማለት ይገባናል፡፡ ሙያውንና ሰአሊያኑን የሚያበረታታውን የማኩሽ ጋለሪ ባለቤትን አቶ ተስፋዬ ህይወትን ማመስገን፡፡ ማመስገንም ይልመድብን። እናም ከእኒህ አይነት ቅን ሰዎች ጋር በመተባበርም አንዳንድ የሰአሊያኑን ችግር ለመፍታት ቢሞከር? አንድ ሰአሊ ወዳጄ እንደነገረኝ፤ የባለሙያዎቹ የጥበብ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ያደገ ቢሆንም ቅሉ ሀሳባቸውን እንደ ልብ ለመሳል ለምሳሌ የተወጠረ ሸራ በፈለጉት ጊዜ ለማግኘት በከተማው ውስጥ የአቅርቦት እጥረት (ዞዝ) አለ፡፡

ከዚያው ከብሔራዊ ቴአትር ሳንወጣ አንድ ሰሞንኛ ወሬ (ዞዝ) ብንጨምርስ ምን ይለናል... የወሬኝነት አባዜ (ዞዝ) በሉት ከፈለጋችሁ፡፡ እና ባለፈው አርብ እለት በአዲሱ የቴአትር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ፣ አንድን ተዋናይ ‹‹በአስቸኳይ›› በሌላ ተዋናይ ስለመለወጥ የተላለፈ ውሳኔ ቅዳሜ ምሽት በኢትዮፒካሊንክ ቀርቦ ነበር፡፡ እኔን ዞዝ የሆነብኝ ነገር ምን መሰላችሁ? ተዋናዩ በተደጋጋሚ መቅረቱ ቢገለፅም ከ15 ቀናት በፊት በቴአትር ቤቱ በተመረቀው ‹‹የፍቅር ማዕበል›› ፕሮግራም ላይ የተሰራጨው ህትመት ፤ ይኸው ተዋናይ ትርኢት እንዳይቋረጥ ሲል እናቱንም ሳይቀብር መድረክ ላይ መቆሙን፤ እንዲሁም ሀዘኑንም ደስታውንም ከዚያው መድረክ ሳይለይ፣ የቀለበት ስነ ስርአቱንም ቴአትር ሰርቶ ሲጨርስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር መድረክ ላይ በቴአትሩ ታዳሚያን ፊት ማከናወኑ መገለፁ ነው፡፡

በነዚህ ሁለት ‹‹እውነታዎች›› መሀል ያለው ክፍተት (ዞዝ) ምን ይሆን? እናላችሁ ስመጥሮቹ መራሔ ተውኔቶች ቴአትር ቤቱን ለ5 አመት ገደማ ያስተዳደረው ማንያዘዋል እንደሻውና የቴአትር ክፍሉን ለ6 አመታት ያህል የመራው ተስፋ ገብረማሪያም ‹‹ተዋናዩ በፍፁም በድንገት አልቀረም፤ ከቀናት በፊት ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር እንደገጠመው ነግሮን ፈቃድ ጠይቆን፣ እኛም ይህንኑ ለሚመለከተው ክፍል በፅሑፍ አሳውቀናል፡፡›› በማለት የአዲሱን ስራ አስኪያጅ በተቋሙ ከቶም ያልተለመደና ተወዳጁን ተዋናይ በሌላ የመተካት ቀጭን ትዕዛዝ እንደማይቀበሉ አመልክተዋል፡፡ ቀድሞ በትወና ክህሎቱ ከሌሎች ሁሉ መርጠን ለምን በክብር ጋበዝነውና!

ውሳኔው የተላለፈበት ‹‹እድል ላላገኙ ወጣቶች እድል ለመስጠት ቦታችንን መልቀቅ ይገባናል እና ‹ከአቅም በላይ የሆነ ችግር› ካልገጠመን በቀር ትርኢት አይቋረጥም "The Show Must go on" በሚል ፅኑ አቋሙ የሚታወቀው ለ8 ሰአት ቴአትር 4 ሰአት መድረክ ጀርባ ቀድሞ በመገኘት ዲስፒሊኑ የሚደነቀው አርቲስት ፈለቀ የማርውሃ አበበ ግን የእገዳ ውሳኔውን ሰምቶም እንኳ ‹‹ችግር የለም በቃ፣ ባለመግባባት የተፈጠረ የሆነ ቀላል ነገር (ዞዝ) ነው ብለን እንለፈው›› ብሎ /ልቡ እየደማም ቢሆን/ የቴአትር ተመልካቹን በማክበር ቅዳሜም እሁድም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር መድረክ ጀርባ እንደተለመደው ቀድሞ ተገኝቷል፡፡ በስንብት ጊዜም በተደጋጋሚ የላቀ ችሎታ ሽልማት ባስገኘለትና በበርካታ አንጋፋ ከያኒያን በልዩ ልዩ መድረኮች በተመሰከረለት በአስገራሚ የትወና ተሰጥዖው፣ ዘወትር በጋለ ጭብጨባ በሚቀበለው በሚወደውና በሚያደንቀው ተመልካች ፊት ተንበርክኮ፣ የሚያከብረውንና ያስከበረውን መድረክ በእርካታ ስሟል፡፡ የክብር ስንብት ...?

አዲሱ ስራ አሥኪያጅ ሙያውን የተማሩና ለኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የሚጨነቁ ናቸው ይባላል፡፡ ታዲያ እንዲህ አይነት ውሳኔ ለማስተላለፍ የበቁት ምን ያለ ዞዝ ገጥሟቸው ይሆን? ለምን መሰላችሁ እንዲህ የምለው---ቴአትር ቤቱን ማስተዳደር ቀላል እንዳልሆነ ብዙ ጊዜ ሲወራ ምን እንደሚባል ስለማውቅ ነው፡፡ እሺ. ምንድነው በሉኛ..."የአንበሳው ሀውልትም ፊቱን ያዞረው እንዲህ አይነቶቹን ለዘመናት ያልተፈቱ ግሳንግሶች (ዞዞች) መስማት ታክቶት ነው!" ሀሪፍ አይደለች? ወደ ታጋይ ህላዌ ዞዝ የመጨረሻ ህያው መስመሮች ላንዴው እንመለስ...

*አንተም እንደ ጓደኞችህ፣*
*...እንደተንበረከኩልህ እንደተጀነንክባቸው፣*
*ከበታች እንዳደረግኻቸው፣*
*እንደ እነርሱ ሰልለህ፣*
*ግርማ ሞገስህን ተገፈህ፣*
*አውላላህን ቀርተህ፣*
*አተር ሸምብራ በቅሎብህ፣*
*መቼ ይሆን የማይህ?*
*አለያ የዋርድያ ሰአት ይተከልብህ*
*ወይ ዋርድያው ራሱ ይኳለትብህ*
*በኔ እድሜስ አይሆንም፣*
*ዛሬን ነገን አይቻልም፣*
*ወይስ እንደ ዞዝነትህ ድንጋነትህን ይዘህ፣*
*መቆየትህን ትመርጣለህ?*
*በልማ ተንፍስልኝ ፍሬ ያለው መልስ ካለህ፣*
*ዞዝ!*
*አንተ ግዑዝ፣*
*አንተ ግዑዝ!*

/ጥር፣ 1972፤ በለሳ፣ ጎንደር/

በተለይ ‹‹አተር ሸምብራ በቅሎብህ››የሚለውን ሀረግ እዩት እስቲ? በየ‹‹ዞዞቻችን›› ላይ ልምላሜ እንዲያብብ እንመኝ ዘንድ አይነሽጥም? ከላይኛው አንጓ ውስጥ ያለውስ ‹‹ወንዞች ተሻገር! ድንበር ስበር፣ አገር አቋርጥ፣ ሂድ ብረር፣›› ነው የምትለኝ››የሚለው ስንኝ፤ ዘርፈ ብዙ ‹‹ዞዞቻችንን›› ሸሽት ሀገር ለቅቀን ከመሰደድ እንድን ዘንድ ተስፋ የማድረግን ሰላማዊና ሀገራዊ ራዕይ አያቆጠቁጥም?... በየሀገሩ በስደት ላይ ሆነው የመከራ አለንጋ (ዞዝ) የሚጠብሳቸውን ምስኪን ወገኖቻችንን አንድዬ በምህረቱ ይጎብኝልን። የጥበብ ሁሉ ባለቤት፤ ለታመኑት ከፈተና የሚታደግ፣የሰማዕትነትን አክሊል የሚያቀዳጅ አምላክ፤ ሀገራችንን በምህረቱ ይጎብኝልን፡፡ አሜን!!

## የሰዓሊያን ጥግ

- በብሩሼ እሰብካለሁ፡፡

*ሔነሪ ኦሳዋ ታነር*

- ስዕል ሃሳቦቼን የማያይዝበት ምስማር ነው፡፡

*ጆርጅስ ብራኪው*

- እኔ ነገሮችን አልስልም፤ የምስለው በነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት ብቻ ነው፡፡

*ሔነሪ ማቲሴ*

- ስዕሎች በጣም መማረክ የለባቸውም፡፡

*ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን*

- ስዕል ማለቂያ የሌለው የሚመስል ጀብዱ ነው፡፡

*ጃሶን*

- ስዕሎች ብዙ ጊዜ ግድግዳን ከማሳመር ይልቅ ያበላሻሉ፡፡

*ዊሊያም ዎርድስ ዎርዝ*

- ሰዓሊ ሃሳቦቹን ከቆሻሻ ጋር እንዳይጥላቸው መጠንቀቅ አለበት፡፡

*ቴሪ ጉይሌሜትስ*

- ለምንድን ነው የሞቱ ዓሳዎች፣ ሽንኩርቶችና የቢራ ብርጭቆዎች የምስለው? ልጃገረዶች እኮ እጅግ ውብ ናቸው፡፡

*ሜሪ ሎውሬንሲን*

- ዓይኖቼ የተፈጠሩት የሚያስጠላውን ሁሉ ለመሰረዝ ነው፡፡

*ራኦል ዱፊ*

- ማስታወቂያዎች የ20ኛው ክ/ዘመን የዋሻ ስዕሎች ናቸው፡፡

*ማርሻል ማክሉሃን*

- ስዕል ቃላት አልባ ግጥም ነው፡፡

*ሆራስ*

- ሰዓሊ፤ ሰዎች እንዲኖራቸው የማይፈልጉትን ነገር የሚፈጥር ነው፡፡

*አንዲ ዋርሆል*

- ፎቶግራፍን ልዩ ፈጠራ የሚያደርገው የመጀመሪያ ጥሬ እቃዎቹ ብርሃንና ጊዜ መሆናቸው ነው፡፡

*ጆን በርገር*

- ስዕል በተፈጥሮ አንፀባራቂ ቋንቋ ነው፡፡

*ሮበርት ዴላዩናይ*

- ፀሐፊ በዓይኖቹ መፃፍ፣ ሰዓሊ በጆሮዎቹ መሳል አለበት፡፡

*ጌርትሩድ ስቴይን*

- የሰው ልጅ ሁሉ ሰዓሊ ነው፡፡ የህይወትህ ህልም ውብ ስዕል መስራት ነው፡፡

*ሚጌል ኤንጅል ሩይዝ*

- ስዕሎች የተንጠለጠሉበት ክፍል ሃሳቦች የተንጠለጠሉበት ክፍል ነው፡፡

*ጆሹዋ ሬይኖልድስ*





- ፓወር ሚል ሰፊ የደረጃ መረገጫዎች እና ምቹ መወጣጫ::

- **ፓወር ሚል** የደረጃ እንቅስቃሴ መሳሪያ፣ በላቀ ምቾት የተለያየ እድሜ እና አቅም ላላቸው ተጠቃሚዎች::

- **ፍሌክስ ስትራይድር** ፣ ወጥ ተፈጥሯዊ የሩጫ እንቅስቃሴ እና የሶምሶማ እንቅስቃሴ፣ ለመሬት ቅርብ የሆነ መረገጫ ያለው፣ በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ የእርምጃውን ስፋት መቀያየር የሚያስችል ነው::



- ፍሌክስ ስትራይድር ለመሬት ቅርብ የሆነ መረገጫ::

LifeFitness

**የመሸጫ ሱቃችን በዘፍመሽ የገበያ ማዕከል ላይ ይገኛል::**

አድራሻ:- መገናኛ አደባባይ፣ ቀነኒሳ መንገድ፣ አዲስ አበባ ዘፍመሽ የገበያ ማዕከል፣ 1ኛ ፎቅ ሀገዛ ቁጥር FB110
ኢ- ሜይል:-info@bekdesgroup.com , lifefitness@bekdesgroup.com
ስልክ:- 011-6-29-99-51/ 52/ 53 ሞባይል:- 0911-80-43-29

# የአይሲስ የግድያ ቪዲዮዎች የቡድኑ "የስነ-ልቦና ጦርነት" አካል ናቸው ተባለ

## የግድያ ቪዲዮዎቹ አለማቀፍ ስነ-ልቦናዊ ተጽዕኖ እየፈጠሩ ነው

አይሲስ የተባለው አሸባሪ ቡድን እያሰራጫቸው የሚገኙና በተለያዩ አገራት ዜጎች ላይ የፈጸማቸውን አሰቃቂ ግድያዎች የሚያሳዩ የቪዲዮ ምስሎች፣ ቡድኑ በአለማቀፍ ደረጃ የከፈተው የስነልቦና ጦርነት አካል ናቸው መባሉን አሶሼትድ ፕሬስ ዘገበ፡፡

የጀርመን የአገር ውስጥ የስለላ ተቋም ሃላፊ ሃንስ ጆርጅ ማሰን እንዳሉት፣ አገራት እነዚህ አሰቃቂ የግድያ ቪዲዮዎች በወጣት ዜጎቻቸው ላይ የሚያሳድሩትን የስነልቦና ተጽዕኖ ለመቅረፍ የራሳቸውን እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል፡፡

የቪዲዮ ምስሎቹ የአሸባሪውን ቡድን የጥፋት ፕሮፓጋንዳ በወጣቱ ትውልድ ልቦና ውስጥ የሚያሰርጹ ናቸው ያሉት ጆርጅ ማሰን፤ ምስሎቹ ለእይታ ሲበቁ የቡድኑን የጥፋት ተልዕኮ አሰቃቂነት የሚያሳዩ መልዕክቶችን አብሮ ማቅረብ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቡድኑ በቅርቡ በጀርመን ለሚገኙ ደጋፊዎቹ ባሰራጨው የቪዲዮ መልዕክት፣ ባለፈው ጥር ወር በፈረንሳይ የተፈጸመውን ዓይነት ጥቃት እንዲፈጽሙ ጥሪ አቅርቧል ያለው ዘገባው፣ የጀርመን የደህንነት ባለስልጣናትም መልዕክቱን ያስተላለፈው ትውልደ ጀርመናዊው አለማቀፍ አሸባሪ ዴኒስ ኩስፐርት መሆኑን ማረጋገጣቸውን አስታውሷል፡፡

ሲኤንኤን በበኩሉ፤አይሲስ እያሰራጫቸው ያሉት የግድያ ቪዲዮዎች በአለማቀፍ ደረጃ ፍርሃትን እያነገሰ እንደሚገኝና የቡድኑ ቪዲዮዎች ሌሎችም ለመሰል ጥፋቶች እንዲነሳሱ ተጽዕኖ እንደሚያደርግ ዘግቧል፡፡

በሜሪላንድ ዩኒቨርሲቲ የስነልቦና መምህር ፕሮፌሰር አሪ ክሩግላንስኪ እንዳሉት፤ የአይሲስ የአሰቃቂ ግድያ ቪዲዮዎች፣ ግለሰቦች በግጭት ወቅት ተመሳሳይ ጥቃቶችን እንዲፈጽሙ የሚያነሳሳ ስነልቦናዊ ጫና የመፍጠር ሃይል አላቸው፡፡

የጀሃዲስቶች አሰቃቂ ግድያዎች በቪዲዮ ምስሎች በስፋት መሰራጨታቸው፣ ግለሰቦች ከዚህ ቀደም የማያስቡትን አንገት ቀልቶ መግደል የሚል የጭካኔ ሃሳብ ትኩረት ሰጥተው ማሰብ እንዲጀምሩ በማድረግ ረገድ በአለማቀፍ ደረጃ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ነው ብለዋል ፕሮፌሰሩ፡፡



# አውሮፓ በሊቢያ ህገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ላይ ወታደራዊ ዘመቻ ልትፈጽም እየተዘጋጀች ነው

## በዚህ ወር ብቻ ከ1 ሺህ በላይ ስደተኞች በሜዲትራኒያን ባህር ሞተዋል

## በእሁዱ የጀልባ አደጋ የተጠረጠሩ ፍርድ ቤት ቀርበዋል





የሜዲትራኒያን ባህርን አቋርጠው ወደ አውሮፓ አገራት ለመግባት ሲሞክሩ ለህልፈተ ህይወት በሚዳረጉ ስደተኞች ዙሪያ ለመምከር ከትናንት በስቲያ በብራስልስ አስቸኳይ ስብሰባ የጠሩት የአውሮፓ አገራት መሪዎች፣ ሊቢያውያን ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን ለማጥቃትና አካባቢውን ለማረጋጋት የሚያስችል ወታደራዊ ዘመቻ ለማካሄድ ዝግጅት እያደረጉ እንደሆነ አልጀዚራ ዘገበ፡፡

በዚህ አመት ብቻ 36 ሺህ ያህል የተለያዩ አገራት ዜጎች ባህር አቋርጠው በስደት ወደ ጣሊያን፣ ማልታ እና ግሪክ እንደገቡ የጠቆመው ዘገባው፣ የአውሮፓ መሪዎች ስደተኞችን በህገወጥ መንገድ የሚያጓጉዙ ጀልባዎችን ተከታትሎ በመለየት በቁጥጥር ስር የሚያውልና በሊቢያውያን ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ላይ እርምጃ የሚወስድ የአውሮፓ ጥምር ወታደራዊ ዘመቻ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መክረዋል ብሏል፡፡

ባለፈው እሁድ ከሊቢያ በመነሳት ሜዲትራኒያን ባህርን አቋርጣ ወደ ጣሊያን ስትቃረብ በሰመጠችው ጀልባ ከ800 በላይ የተለያዩ አገራት ዜጎች ለህልፈተ ህይወት መዳረጋቸውን ተከትሎ አስቸኳይ ስብሰባ ያደረጉት መሪዎቹ፣ በሜዲትራኒያን ባህር ስደተኞችን ለማዳን ለሚከናወኑ ተግባራት የሚሰጡትን የገንዘብ ድጋፍ በሶስት እጥፍ ለማሳደግ የተስማሙ ሲሆን በወር በድምሩ 9.7 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል ገብተዋል፡፡

የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሩን ስደተኞችን ለመታደግ የሚሰሩ ስራዎችን ለማገዝ የሚውሉ ሶስት ሄሊኮፕተሮችንና ሁለት መርከቦችን ለመስጠት ቃል ሲገቡ፣ ጀርመንና ፈረንሳይም እያንዳንዳቸው ሁለት መርከቦችን ለመስጠት ቃል መግባታቸውን ዘገባው ገልጧል፡፡

የውሮፓ አገራት መሪዎች በህገወጥ ስደት ለህልፈተ ህይወት የሚዳረጉ ዜጎችን ጥፋት ለመቀነስና ዜጎቻቸው ከሚሰደዱባቸው አገራትና የስደተኞች መተላለፊያ ከሆኑ አገራት ጋር በትብብር መስራትን ጨምሮ፣ ለስደት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን የመቅረፍ ስራ በስፋት ለመስራት ተስማምተዋል፡፡

የአውሮፓ ህብረት በበኩሉ ባለፈው ሰኞ በሜዲትራንያን ባህር የሚከሰተውን የስደተኞች ሞት ለመቀነስና ቀጣይ ጥፋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ባለ 10 ነጥብ የድርጊት መርሃ ግብር ቢያወጣም፣ መርሃግብሩ ጥፋትን ከመቀነስ ይልቅ የሚያባብስና ተጨማሪ ስደተኞችን ለስደት የሚያበረታታ ነው በሚል እየተተቸ እንደሚገኝ ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

በዘንድሮው አመት ብቻ ሜዲትራኒያን ባህርን አቋርጠው ወደ አውሮፓ አገራት ለመግባት ሲሞክሩ ለህልፈተ ህይወት የተዳረጉ ስደተኞች ቁጥር ከ1 ሺህ 700 በላይ መድረሱን የዘገበው ቴሌግራፍ በበኩሉ፣ ይህ የሞት መጠን ባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ከተመዘገበው ጋር ሲነጻጸር በ30 እጥፍ እንደሚበልጥም ገልጧል፡፡

አሶሼትድ ፕሬስ በበኩሉ የተመድ የስደተኞች ድርጅትን ጠቅሶ ከትናንት በስቲያ ባወጣው ዘገባ፣ ባለፈው አመት ብቻ 219 ሺህ ያህል ስደተኞች ሜዲትራኒያን ባህርን አቋርጠው በህገወጥ መንገድ ወደ አውሮፓ አገራት መግባታቸውንና ከ3 ሺህ 500 በላይ የሚሆኑም በጉዞ ላይ ሳሉ ለሞት መዳረጋቸውን አስነብቧል፡፡ ከእነዚህ መካከልም ከ1ሺህ በላይ የሚሆኑት በዚህ ወር ብቻ መሞታቸውንም አስታውቋል፡፡

ጣሊያን ባህር አቋርጠው የሚመጡ ስደተኞችን ከአደጋ ለመታደግ በሊቢያ ድንበር አቅራቢያ ታደርግ የነበረውን እንቅስቃሴ በጥቅምት ወር 2014 ማቋረጧ፣ ለሟቾች ቁጥር ማሻቀብ ምክንያት ሆኗል ብለው የሚተቹ አስተያየት ሰጪዎች መኖራቸውንም ዘገባው አክሎ ገልጧል፡፡

ባለፈው እሁድ ከደረሰውና በአካባቢው ከደረሱ መሰል አደጋዎች ሁሉ የከፋ ጥፋት የደረሰበት ነው በተባለው አደጋ ከ800 በላይ ሰዎች መሞታቸውንና ስደተኞቹ ኤርትራ፣ ሶማሊያና ሶሪያን ጨምሮ የ20 የተለያዩ አገራት ዜጎች እንደሆኑም ሲ ኤን ኤን ዘግቧል፡፡

ከእሁዱ የስደተኞች ጀልባ አደጋ ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው ሲሲሊ ውስጥ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉት የጀልባዋ ካፒቴንና አንድ የህገወጥ የሰዎች ዝውውሩ ተሳታፊ ትናንት ፍርድ ቤት ቀርበው ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

# የቀድሞው የግብጽ ፕሬዚዳንት የ20 አመት እስር ተፈረደባቸው

## *22 የሙስሊም ብራዘርሁድ ደጋፊዎችም በሞት ተቀጥተዋል*



የቀድሞው የግብጽ ፕሬዚዳንት ሞሃመድ ሙርሲ፣ በስልጣን ዘመናቸው ዜጎች ያለአግባብ እንዲገደሉ፣ እንዲታሰሩና እንዲሰቃዩ መመሪያ አስተላልፈዋል በሚል ተከስሰው የ20 አመት እስር እንደተፈረደባቸው ቢቢሲ ዘገበ፡፡

ከሁለት አመታት በፊት በግብጽ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ ከስልጣናቸው የወረዱት የሙስሊም ብራዘርሁድ መሪ ሞሃመድ ሙርሲ፣ በታህሳስ ወር 2012 በቤተመንግስታቸው አቅራቢያ ለተቃውሞ የወጡ ከአስር በላይ ግብጻውያን እንዲገደሉ፣ ብዙዎችም እንዲታሰሩና ለስቃይ እንዲዳረጉ ትዕዛዝ መስጠታቸውን አረጋግጫለሁ በማለት ነው ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን የጣለባቸው ተብሏል፡፡

ባለፈው ማክሰኞ በካይሮ የዋለው ችሎት ከሙርሲ በተጨማሪ በሌሎች 12 የሙስሊም ብራዘርሁድ ባለስልጣናት ላይ ተመሳሳይ የእስራት ቅጣት እንደጣለ ዘገባው ጠቁሟል፡፡

ሙርሲ በተቃዋሚዎች ላይ ግድያ መፈጸምን

እስር ወደ ገፅ 19 ዞሯል

## አቶ ሳሙኤል ቦጋለ ሚያዝያ 2 ቀን 2007 አረፉ



### ሳሚ ምንጊዜም አንረሳህም እንወድሀለን

### ጌታ ነፍስህን በገነት ያኑርልን ከቤተሰቦቹ

"የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን"
የሐዋርያት ስራ 21 ፥14

በጀት ከገፅ 11 የዞረ

የእሳቸው ዘመን ማብቃቱን ያረጋግጥላቸዋል። ለ5 ዓመት አስገድዶ ደፍሮኛል ለምትለው ሳፍያ ግን የኮሎኔሉ መንፈስ እድሜልኳን ሲያስበረግጋት ይኖራል፡፡ የፕሬዚዳንቱን በድን ምስል ባየችበት ወቅት የተደበላለቁ ስሜቶች እንደተሰማት ተናግራለች - ከደስታ እስከ ንዴት፡፡

እሷ ብቻ ግን አይደለችም የተደፈረችው፡፡ ጋዳፊ ሴት ጠባቂዎቻቸውንም (Body guards) አስገድደው ይደፍሩ ነበር፡፡ ይሄ ብቻ አይደለም። ይደበድቧቸውና በመድሃኒትም ያደነዝዟቸዋል፡፡ ከእኒሁ ሴት ጠባቂዎቻቸው ጋር በፕሬዚዳንታዊ መኖርያ ቤታቸው ውስጥ የቡድን ወሲብ ይፈፅሙ እንደነበርም "አፍሪካ ክራድል" ዘግቧል፡፡

ዘገባዎች እንደሚጠቁሙት፤ ሌሎች ልጃገረዶችም የኮሎኔሉን "አፈንጋጭ የወሲብ ፍላጐቶች" ለማርካት የቦዲጋርዶቻቸውን ያህል ተሰቃይተዋል፡፡ የአፍሪካና የአውሮፓ በተለይ የጣልያንና ቤልጂየም ልዕለ ሞዴሎች ዘወትር እየተመለመሉ የፕሬዚዳንቱን ፍላጐት በቡድን ያረኩ ነበር ተብሏል፡፡

"ሴቶቹ ስራቸውን ሲያጠናቅቁም ቦርሳቸውን በገንዘብ አጭቀው ይወጣሉ፤ የወሲብ ባሪያ ላደረጓቸው የሊቢያ ሴቶች ግን ጨርሶ ገንዘብ ሰጥተዋቸው አያውቁም" ይላሉ - ምንጮች። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የተነሳ ጋዳፊ 3ኛው "ሴት አውል" (ሴሰኛ ይሻላል!) የአፍሪካ መሪ በሚል ተመርጠዋል፡፡ (ቤተመንግስቱን የዝሙት ቤት አድርገው ነበር!)

### 4. ጃኮብ ዙማ

የጋናው ፕሬዚዳንት ጆን ማሃማ "ሴት አውል" አይደለሁም ሲሉ ያስተባብላሉ፡፡ ነገር ግን ከትዳራቸው ውጭ መቅበጣቸውን አይክዱም!!" ልካድ ቢሉም አይችሉም፡፡ በርካታ ከትዳር ውጭ የተወለዱ ልጆች አሏቸው፡፡

"እኔን ሴት አውል አድርጐ የማሰብ ሁኔታ አለ፤ ይሄ ፈፅሞ እውነት አይደለም፡፡ በእርግጥ ከትዳሬ ውጭ ልጆች ወልጄአለሁ፡፡ ይሄን በተመለከተም ከሚስቴ ጋር ሰላም ፈጥሬአለሁ፡፡ እሷ ነገሩ የተከሰተበትን ሁኔታ በደንብ ተረድታለች፡፡ እኔም ለልጆቼ ሃላፊነት የሚሰማው አባት ነኝ፡፡" ብለዋል - ፕሬዚዳንቱ፡፡

ማሃማ ከትዳር ውጭ የተወለዱት ልጆች ቁጥር "ሰባት" መሆናቸውን በይፋ ገልፀዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ ከሌላ ያልታወቀች ሴት (እሳቸውማ ያውቋታል!) የወለዷቸው ልጆች እንዳሉም ይታወቃል፡፡ ከአሁኑ ባለቤታቸው ከሎርዲና ጋር ከመጋባታቸው በፊት የወለዱት አንድ ወንድ ልጅም አላቸው፡፡ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ግን ማሃማ ቢያንስ 5 ከትዳር ውጭ ግንኙነቶች ሲኖራቸው የልጆቹ ቁጥርም ከሰባት በላይ ነው (20 እንኳን አልሞላም እኮ!) እነዚህ ሁሉ ታይተው ጆን ማሃማ 4ኛው "ሴት አውል" ኛ የአፍሪካ ፕሬዚዳንት ተብለዋል፡፡

### 5. ያህያ ጃሜህ

የጋምቢያው ፕሬዚዳንት ያህያ ጃሜህ ሦስት ሚስቶች አሏቸው - አሊማ ሳላህ፣ ዘይነብ ሱማ ጃሜህ እና ቱቲ ፋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ፤ የነፃ ትምህርት እድል አሸናፊ ከነበረችው ፋቶ ጃሮል - ጃሜህ ጋር በነበራቸው ግንኙነት አስረግዘዋት ነበር፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን ህፃኑ "ዳውን ሲንድሮም" (የአዕምሮ እድገት ዝግመት) እንዳለበት በምርመራ በመታወቁ ፅንሱን እንድታቋርጠው ተደረገ። በነገራችን ላይ የፕሬዚዳንቱ ሁለት ልጆችም በተመሳሳይ የጤና ችግር የተጠቁ ናቸው፡፡

ያህያ ጃሜህ የሰው ሚስት በመመንተፍ ይታማሉ፡፡ ከትዳራቸው ውጭም ልጆች ወልደዋል። እድሜ ለሃብታቸውና ለስልጣናቸው! ከወጣት ሴቶችና ኮረዳዎች ጋር እንዳሻቸው ይቀብጣሉ፡፡ ሰውየው በአፍሪካ 5ኛው "ሴት አውል" ፕሬዚዳንት ተብለው ተመርጠዋል፡፡

ወዳጆቼ፤ እንዳያችሁት የአንዳንድ የአፍሪካ መሪዎች ታሪክ በሴትና በወሲብ ገድል የተሞላ ነው። ስልጣን የሙጥኝ የሚሉት እኮ ወደው አይደለም፡፡ ለእነሱ ከኤደን ገነት እንደመባረር ነው - ከቤተ መንግስት መውጣት! ምስኪኑ የአፍሪካ ህዝብ ግን በድህነት ተቆራምዶ ኑሮውን ይገፋል፡፡ ("ወይ መዓልቲ!" አለ ትግሬ!)

ግፋችንን ከገፅ 9 የዞረ

እህቶቻችን ላይ የደረሰውን እናስታውስ፡፡ አሁን ደግሞ በፍጹም ይሆናል ይደረጋል ተብሎ በማይታሰብባት አፍሪካዊ ሀገር በደቡብ አፍሪካ ወንድም እህቶቻችን በእሳት ተቃጥለው ተገደሉ። የቀሩትም ለዓመታት ለፍተው ያተረፉትን ንብረት ተዘረፉ፤ ተንገላቱም፡፡

በዚህ አንብተን እንባችን ከዐይናችን ላይ ሳይደርቅ፣ሠላሳ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ተስፋን ሰንቀው እንጀራ ፍለጋ ሲደክሙ፣ የሰው ልጅ ሊባሉ በማይችሉ አረመኔዎች እጅ እጅግ አሰቃቂና ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ አንገታቸውን ተቀልተው ተገደሉ፡፡ የሆነውና እየሆነው ያለው ሁሉ የምር ልብን ይሰብራል፡፡

ይህን አረመኔያዊ ድርጊት እየፈጸሙብን ያሉት ህዝቦች (አረቦቹም ሆኑ አፍሪካውያኑ) ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ጋር የረጅም ዘመናት የክፉ ጊዜ ወዳጅነት የነበራቸው፣ ይህቺም ሀገር ባለውለታቸውና የክፉ ቀናቸው ናት፡፡ ሁለቱም ህዝቦች ከጠላቶቻቸው ሸሽተውና ይህቺን ሀገር ሀገራቸው አድርገው በክንፏ ስር ተጠልለዋል። ከማዕዷ ቆርሰውና ከመደቧ ጎናቸውን አሳርፈው ከእንግልቱ አርፈዋል። ጎልምሰውና ኃይላቸውን አፈርጥመው በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እንዲቀዳጁ ይህቺ ሀገርና ህዝቦቿ ስለ እነሱ አብዝተው ደክመዋል። ይህንን ዓለም ያውቀዋል፤ ይመሰክረዋልም፡፡

ያም ሆኖ ይህንን ማየት የተሳናቸው አረመኔዎች የለኮሱት ጥፋት ለታሪክና እውነት በተለይም ለወንድማማችነት ግድና እውቀት በሌለው፣ ይልቁንም በባዶ እብሪትና ድንፋት በተሞላ "ጎረምሳ" እየተመራ የሆነው ሁሉ በእኛ ላይ ሆነብን። ይህ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰ ግፍ ሁሉ ለእኛ ጥቃት፣ ቁጭትና ማነስ ሲሆን ለእነሱ ግን መቼም ሊፍቁት የማይችሉት ሃፍረት ነው፡፡ ታላቅ ሃፍረት! ስለ ጠላቶቻችን ከዚህ በላይ ምንም ማለት ምንም አይረባንምና ወደ ራሳችን እንመለስ፡፡ ልብ ካልን የሚረባን እሱ ነው፡፡

ማንም ተጠቂ ከደረሰበት ጥቃት በላይ የሚያመው መጠቃቱን የሚያይለትና የሚሞግትለት አካል ሲያጣ ይመስለኛል። ተጠቂው ህዝብ ሲሆን ደግሞ "መንግስቴ ወዴት አለ?" ብሎ ይጠይቃል። የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ሀዘን ያከፋውም ስለሆነውና እየሆነ ስላለው ሁሉ ጠያቂ ማጣታችን ነው። እናም እንጠይቃለን፡፡ ማን ይገዳደርልናል?! እስከመቼስ እንዲህ እናንሳለን?!...

መሆን ያለበትና እየሆነ ያለው ፍጹም ከመለየቱ የተነሳ ምን እየሆነ ነው? ወይንስ እኛ ያልገባን ጉዳይ አለ? ብለን አብዝተን እንድንጠይቅ ሆነናል። (መልስ የሚሰጠን ባናገኝም፡፡) ደግሞስ መልስ አለመስጠት መነሻው ምንድን ነው? መልስ ማጣት ወይስ ማን አለብኝነት? ይህንንም እንጠይቃለን፡፡ ማንም ህዝብ በማንም የሚከበረውና የሚታፈረው ህዝቡን የሚመራው መንግስት ባለው ቁርጠኝነትና በሚወስዳቸው እርምጃዎች ነው፡፡ ይህንን ባሳለፍነው ታሪክ አይተናል፡፡ በሌሎች ሀገሮች ላይ በሆነውም ታዝበናል፡፡...

ዳተኝነቱ ለምን ሆነ? "የአፍሪካ አንደበት ሆነናል" እስከማለት ድረስ የምናሞካሸው ዲፕሎማሲያችን የኢትዮጵያና የህዝቦቿ አንደበት ለመሆን እንደምን ሰነፈ?! "የበርካታ ሀገራትን ሰላምና መረጋጋት እያመጣ ነው" እያልን ሠርክ የምናወድሰው ኃይላችንስ እንደምን ለዜጎቹ ደህንነት መከታ መሆን ተሳነው?! ይህንን መጠየቅ በደል አይደለምና እንጠይቃለን፡፡

እናውቃለን፡፡ በባዕድ ሀገራት በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ እየደረሱ ያሉት እንግልቶችና ህይወት ማጣቶች በኢትዮጵያውያን ላይ ብቻ የደረሱ አይደሉም፡፡ በአረብ ሀገራት በደረሰው ግፍ የፓኪስታን፣ ፊሊፒንስ፣ ህንድ... ሀገራት ዜጎችም የገፈቱ ቀማሾች ነበሩ፡፡ በደቡብ አፍሪካ ከተሞች በደረሰው ጥቃትም እንዲሁ የዚምባቡዌ፣ ማላዊ፣ ሱማሌና ናይጄርያ ዜጎች ተጠቅተዋል፡፡ በፅንፈኛው ቡድንም የአውሮፓ ሀገራት ዜጎችን ጨምሮ በርካታ የመካከለኛው ምስራቅና የአፍሪካ ዜጎች አንገታቸውን በስለት ተቀልተው ተገድለዋል፡፡ ሆኖም ግን የእነዚህ ሀገራት መንግስታት ቀድመው በወሰዷቸው ጥንቃቄዎችና ችግሩ ከተከሰተም በኋላ አፋጣኝ እርምጃዎችን በመውሰዳቸው በተወሰነ መልኩም ቢሆን ዜጎቻቸውን ለመታደግ ችለዋል።

መንግስታቱ ቀደም ሲል በኤምባሲዎቻቸው አማካይነት ለዜጎቻቸው የሚያደርጉት ከለላ እንደተጠበቀ ሆኖ ችግሩ ሲከሰትም እጅጉን አፋጣኝና ጠንካራ አቋሞችን ሲወስዱና ለችግር አድራሾቹ ሀገራት መንግስታት አስገዳጅ ምላሾችን ሲሰጡ ተስተውለዋል፡፡

የእኛ የኢትዮጵያውን መንግስትስ ምን ቀዳሚ ጥንቃቄዎችን ወሰደ? ለክስተቶቹ የሰጣቸው ምላሾችስ ምንድን ናቸው? መከፋታችን ያህላል ያጣው በዚህ ነው፡፡ የምር ያስከፋል! አንድ መንግስት ካሉበት ዋና ዋና ኃላፊነቶች አንዱ በየትኛውም ሥፍራና ወቅት የዜጎቹን ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡ ይሄ እኮ መንግስት ለዜጎቹ የሚያደርገው ቸሮታ ሳይሆን ስራውና ኃላፊነቱ ነው፡፡

የሆነው ግን የተገላቢጦሽ ነው ማለት ይቀላል። እውነት ለመናገር ችግሩ ከተከሰተበትና አለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ከዘገቡበት ቅጽበት ጀምሮ ለጉዳዩ አስቸኳይ ትኩረት በመስጠት መረጃ ሲለዋወጥና ግፊት ሲያደርግ የነበረው ህዝቡ ነው። መንግስትስ? መንግስትማ አንዴ "እያጣራሁ ነው"፣ አንዴ "ኢትዮጵያውያን መሆናቸው አልተረጋገጠም"... በማለት ዳተኝነት አሳይቶአል፡፡ ችግሩ እኮ ከፍተኛ አደጋ ነው፡፡

መንግስት አውቆም ይሁን ግራ ገብቶት የሚወስዳት የአንድ ደቂቃ መዘናጋት የሺዎችን ህይወት ለማስቀጠፍ በቂ ናት፡፡ ደግሞም በሰዓቱ እንጂ ካለፈ በኋላ የሚሰማ ድምጽ "ብያለሁ" ከማለት ያለፈ ፋይዳ እንደሌለው ለማወቅ ብዙም እውቀትን አይጠይቅም፡፡

ሌላው አሳዛኙ ነገር ደግሞ አሁንም ድረስ በመንግስት በኩል እየተወሰዱ ያሉት እርምጃዎች የምር ችግሩን ለማስቆም የሚያስችሉ አለመሆናቸው ነው፡፡ የችግሩ ሰበዝ እየተሳበ ወዴት እንደሚመጣ ስለሚታወቅ ይመስላል፣ የነገሩን አቅጣጫ ለማስቀየስና ይልቁንም ለፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ለማድረግ እየተሞከረ ነው፡፡ (የሰሞኑን የመንግስት ሚዲያዎች ውትወታ ልብ ይሏል፡፡) ይህም እጅግ ያስከፋል። በሚሊዮኖች ሀዘን ላይ እንጀራን ለመጋገር እንደመሞከር ነው፡፡

ምን እየተደረገ ነው?... ከደረሰብን ግፍ በላይ ያዘነው ግፋችንን የሚጠይቅልንና የሚገዳደርልን በማጣታችን ነው፡፡ ባዕዳን ካደረሱብን ግፍ በላይ "አስተዳድራችኋለሁ" የሚለን "መንግስት" ዝምታ ነው ያስቆጨን፡፡ ማን ይገዳደርልናል?! እስከመቼስ እንዲህ እናንሳለን?!

እስር ከገፅ 18 የዞረ

ጨምሮ የሞት ቅጣት ሊያስጥሉባቸው የሚችሉ ሌሎች ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች እንደተመሰረቱባቸው ያስታወሰው ዘገባው፤ ይሄኛው ፍርድ ቤት ግን የቀረቡለትን የግድያ ክሶች ውድቅ ማድረጉንና ለግድያና ለእስራት ትዕዛዝ መስጠት በሚለው ክስ ብቻ ቅጣቱን እንደጣለባቸው አስታውቋል፡፡

የሙስሊም ብራዘርሁድ የቀድሞ ከፍተኛ ባለስልጣን አምር ዳራግ፤ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ፍትህን ያዛባ ነው ሲሉ ተችተውታል፡፡

ባለፈው ሰኞ 22 የሙስሊም ብራዘርሁድ ደጋፊዎች በካይሮ በሚገኝ የፖሊስ ጣቢያ ላይ ጥቃት አድርሳችኋል በሚል ተከሰው የሞት ቅጣት እንደተላለፈባቸው የገለጸው ዘገባው፤ ታዋቂውን የሙስሊም ብራዘር ሁድ የቀድሞ መሪ ሞሃመድ ባዴን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ የቀድሞው የግብጽ አስተዳደር ባለስልጣናት ከዚህ በፊት የሞት ፍርድ እንደተጣለባቸውም ጨምሮ አስታውሷል፡፡

# ላንቺና ላንተ

ፀሐይ ተፈረደኝ ከኢሶግ

# ህፃናቱን የማዳን ስራ ቀለል ተደርጎ ሊታይ አይገባውም

ተከታዩ ገጠመኝ በቤተዛታ ሆስፒታል (አዲስ አበባ ለገሀር) ያገኘናት እናት ገጠመኝ ነው፡፡

"...የእርግዝና ክትትል ለማድረግ ወደ ሆስፒታል ስሄድ በመጀመሪያ የተነገረኝ የኤችአይቪ ቫይረስ በደሜ ውስጥ መኖር ያለመኖሩን ማረጋጋጥ እንደሚገባኝ ነበር። ሐኪሞቹ ሲነግሩኝ እንደከባድ ነገር አልቆጠርኩትም፡ ፡ ምንም ችግር የለም ...እሺ... በማለት ምርመራውን አደረግሁ። ...ያገኘሁት ውጤት ግን ስሜቴን እንደ መጀመሪያው ይገዤ እንድቀጥል አላስቻለኝም። ደነገጥኩ... ፈራሁ... ተርበተበትኩ...፡፡ የምክር አገልግሎት የምትሰጠኝ ነርስ በጣም ተቸገረች፡፡ የእኔን ስሜት ለመጠበቅ ብዙ ታገለች። እኔም በተቻለ መጠን ስሜቴን አሰባስቤ ወደቤት ተመለስኩ፡፡ ስሜቴን ሊጋራ የሚችል ማንም ሰው አልነበረኝም፡፡ ለማንም መንገር አልፈለግሁም፡፡ እናቴ፣ እህቴ፣ ወንድሞቼ ሁሉ ዙሪያዬን ቢኖሩም ...በቃ ...ለአንድ ሳምንት ብቻዬን በሬን ዘግቼ ተኛሁ፡፡ የሁዋላ ሁዋላ ግን አስቤ... አሰቤ.. እራሴን አበረታትቼ... ወደ ህክምናው ተመለስኩ፡፡

ከዚያ በሁዋላስ? የእኛ ጥያቄ ነበር፡፡

"...ከዚያ በሁዋላ ጉዳዬን ለእራሴ ይዤ... ከነርስዋ እና ከሐኪሜ ጋር ብቻ እየተወያየሁ ልጄን በሰላም ወለድኩ፡፡ እንደአለመታደል ሆኖ የወለድኩለት ሰው አብሮኝ የለም። ባሌም አይደለም፡፡ ለተወሰነ ጊዜ በነበረን የጉዋደኝነት ቆይታ ነበር ያረገዝኩት፡፡ ...ለነገሩ ገና ተመርምሮ ካልሆነ በስተቀር ልጁ የእርሱ ነው ለማለት አልችልም፡፡ ሌላም ጉዋደኛ ነበረኝ፡፡ ለማንኛውም... ችግሩ ሌላ ነው፡፡

ምንድነው ችግሩ?

"...ችግሩማ... ከወለድኩ በሁዋላ በዚያችው በአንድ ከፍል መኝታቤት ውስጥ እህቴ እናቴ ወንድሞቼ ሁሉ ከበውኛል፡፡ እንዴት አድርጌ ለልጄ የምሰጠውን መድሀኒት ልስጥ? የሚያዩትን ነገር ሁሉ ማወቅ ይፈልጋሉ። ለእራሴም በትክክል መድሀኒቴን መውሰድ ...ልጄንም መንከባከብ... አልቻልኩም፡፡ በተለይም እህቴ ለሁሉ ነገር በጣም ቅርቤ ስለሆነች እጅግ በጣም ነበር የተቸገርኩት። እንዳልነግራቸው ...ሁሉም ጥለውኝ ይሄዳሉ ብዬ ፈራሁኝ፡፡ ዝም እንዳልል ሐኪም በነገረኝ መመሪያ መሰረት ልጄንም እራሴንም መጠበቅ አቃተኝ። ስለዚህ ያለኝ አማራጭ የአራስነት ጊዜዬን ሳልጨርስ መነሳት እና እራሴን መርዳት ነበር..."

ከላይ ካነበባችሁት ገጠመኝ ልንማር የምንችለው ነገር ግልጽነት የሚባለው ነገር እና አድሎና መገለል ዛሬም በትክክል አልተለመዱም የሚለውን ነው፡፡ ገጠመኝዋን የገለጸችው እናት ቤተሰቦቹ ምናልባት መገለል ያደርሱብኛል ከሚል እስዋ በበኩልዋ ድብቅ በመሆንዋ ብዙ እንደተቸገረች ነው፡፡ ነገር ግን አድሎና መገለልን አስወግደን ግልፅነት በተመላበት ሁኔታ መኖር ብንችል ቀጣዩ ትውልድ ከኤችአይቪ ቫይረስ ነጻ እንደሚሆን እሙን ነው፡፡

ከኤችአይቪ ነፃ የሆነ ትውልድን በሚመለከት WHO በ2015 ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው በ2010 በኬንያ 20/ የአፍሪካ ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ የተሰበሰቡ ሲሆን ስብሰባው የተቀናበረው በUNFPA'UNAIDS' UNICEF እና WHO ነበር፡፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ በስብሰባው የተሳተፉት 20 የአፍሪካ ሀገራት በአለም ከሚቆጠረው ኤችአይቪ ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ 85% የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ በኬንያ በተደረገው ስብሰባ ህፃናቱን የማዳን ስራ እንደሌላ ስራ ቀለል ተደርጎ ሊታይ የማይገባውና በየአመቱ በመላው አፍሪካ በቫይረሱ የሚያዙ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆኑ ህፃናትን ህይወት ለማዳን እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ ተሰምሮበታል፡፡

ዩኒሴፍ በ2012 ባወጣው መረጃ በኢትዮጵያ የኤችአይቪ ቫይረስ በደማቸው ከሚገኝ እናቶች መካከል 24% የሚሆኑት ብቻ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የሚሰጠውን ህክምና እንደሚያገኙ ጠቁሟል፡፡ በእርግዝና ወቅት ለእናቲቱ የሚሰጠው የኤች አይቪ የምክር አገልግሎት ህክምናውን በማስፋት እንዲሁም ከቫይረሱ ነፃ የሆነ ልጅ እንዲወለድ በማድረግ እረገድ የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው።

ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የማድረግ እርምጃ ባደጉት ሀገራት ትልቅ ለውጥ እንዳመጣና ከሰሀራ በታች ባሉት የአፍሪከ ሀገራት ግን በየአመቱ (300000) ሶስት መቶ ሺህ ያህል አዲስ ህፃናት በቫይረሱ እንደሚያዙ የአለም የጤና ድርጅት መረጃ ያሳያል፡፡

የWHO መረጃ የሚከተለውን እውነታ ያሳያል፡፡

- በ2008 የወጣ መረጃ እንደሚያሳየው በአለም 45% የሚሆኑ እርጉዝ ሴቶች ብቻ ፀረ ኤችአይቪ ህክምና መውሰዳቸው ተረጋግጧል፡፡
- በኢትዮጵያ ከኤችአይቪ ቫይረስ ጋር የሚኖሩ እና ልጆቻቸውን ከቫይረሱ ለመከላከል ART የሚወስዱ እናቶች (18269) አስራ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ዘጠኝ ይሆናሉ፡፡
- ከቫይረሱ ጋር ይኖራሉ ተብለው የሚገመቱ እና ART መጠቀም ያለባቸው እናቶች (ልጆቻቸውን ከቫይረሱ ለመከላከል) VNAID እና WHO ባወጡት አሰራር መሰረት ወደ (33000) ሰላሳ ሶስት ሺህ ይሆናሉ፡፡
- ስለዚህ ART ተጠቃሚ እርጉዝ እናቶች 55% እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡

(World health organization, 2014)

ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ ሊተላለፍ የሚችለው በእርግዝና፣ በምጥ፣ በወሊድ እና ጡት በማጥባት ሲሆን ስያሜውም MTCT ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ይሰኛል፡፡ ይህንን ለመከላከል በሕክምናው ዘርፍ የሚሰራው ስራም PMTCT ወይም ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል በሚል ስራ ላይ ውሏል፡፡ የ PMTCT አገልግሎት በማይሰጥበት ሁኔታ ኤችአይቪ ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ የሚኖረው መተላለፍ እንደየ ሀገራቱ ሁኔታ ከ15-45% ሊደርስ የሚችል ሲሆን የመከላከሉ ስራ ውጤታማ ከሆነ ግን ስርጭቱ እስከ 5% ይወርዳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

አለማቀፉ የጤና ትምህርት እና ስልጠና ማእከል (I-TECH) ከUS president's emergency plan for HIV AIDS Relief ጋር በመተባበር የኤችአይቪ ቫይረስ በደማቸው ለሚገኝ ነብሰጡር እናቶች ድጋፍ ይሰጣል። ይህ ፕግራም ባሳለፍነው የፈረንጆቹ አመት ማለትም በ2014 ያበቃ ሲሆን በአክሱም፣ ጎንደር እንዲሁም ዱፍቲ የሚገኙ እናቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ተጠቃሚ ከሆኑ እናቶች መካከል አንዱዋ የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥታለች፡፡

"...አለምነሽ ቫይረሱ በደሟ እንዳለ ያወቀችው በፈረንጆቹ 2009 ወደ አረብ ሀገር ለመሄድ ባደረገችው ምርመራ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ወደ ውጪ የመሄድ ህልሟ እውን ሳይሆን ቀርቷል፡፡ በ2013 የመጀመሪያ ልጇን ስታረግዝ ትልቁ ጭንቀቷ የነበረው የሚወለደው ህፃን እንዴት ከቫይረሱ ነፃ ሆኖ ይወለዳል? የሚል ነበር። ...ኤችአይቪ ፖዘቲቭ ሆኖ ከቫይረሱ ነፃ የሆነ ልጅ መውለድ እንደሚቻል ሳውቅ በጣም ነው ደስ ያለኝ፡፡ ምናልባት የዚህ ፕሮግራም አካል ባልሆን ኖሮ ልጄ ነፃ ሆና ላትወለድ ትችል ነበር፡፡ ዛሬ ሂያብ የሰባት አመት ታዳጊ ሆናለች፡፡"

በኢትዮ ጠቢብ ሆስፒታል ያነጋገርናት ሲ/ር አልጣሽ ደሳለኝ እንደምትመሰክረው እናቶች ለምርመራ ሲመጡ የሚያሳዩት ፊትና ከውጤት በሁዋላ የሚኖራቸው ምላሽ እጅግ ይለያያል፡፡ ይህንን በምሳሌ ስታስረዳም...

"...አንዲት እናት ለእርግዝና ክትትል ስትመጣ በመጀመሪያው የምክር አገልግሎት ጊዜ ...የኤች አይቪ ቫይረስ በደምዋ ውስጥ ቢገኝ ምንም ማለት እንዳልሆነ ...ከባለቤቷ ጋር በሰላም ተፈቃቅራ እንደምትኖር... ልጅዋንም በሰላም ተረጋግታ እንደምታሳድግ ነበር የነገረችኝ፡፡ ነገር ግን ልክ የደም ውጤትዋ ሊነገራት ሲል ሰውነትዋ ሲደፈርስ ይታይ ነበር፡፡ በጣም ለማግባባት ሞክሬ ሁኔታውን ስነግራት ማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ነበር የተለወጠችው፡፡ እዚያው እኔው ፊት ...ባለቤተዋን መውቀስ... ማልቀስ... ጀመረች፡፡ ለማባበል ብዙ ብሞክርም አልሰማችኝም፡፡ ከዚያ በሁዋላ አልተመለሰችም፡፡ በስልክ... እንዲሁም በተለያየ መንገድ ብከታተልም የት እንደገባች ማወቅ አልቻልኩም፡፡ ለካስ ይህች ሴት ስልኩዋን ከስራ ውጭ አድርጋ በቀጥታ ወደቤተሰቦቿ ጋ ወደገጠር ነበር ያመራችው፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ እራስዋ በአካል ወደ ሆስፒታላችን መጥታ የነገረችኝ ...ሁኔታውን ያወቁት በዚያ የሚኖሩ ወንድሞቿ አግባብተው በቅርብ ወደሚገኘው ጤና ጣቢያ እና ሆስፒታል እያመላለሱ... እያግባቡና እያባበሉዋት ልጅዋን በሰላም እንድትወልድ ማድረጋቸውን ነው፡፡ በሁዋላም ልጁ ከቫይረሱ ነጻ መሆኑ እስኪረጋገጥ እ ዛ ው ቆይታ ልጁን ለቤተሰቦቿ ትታ መምጣትዋን ነገረችኝ፡፡ ስለባለቤትዋ ያለውን ሁኔታም ስጠይቃት... እሱንማ ያኔውኑ ነው የፈታሁት... ምክንያቱም ዋሽቶኛል... ለካስ እሱ አስቀድሞውኑም ቫይረሱ በደሙ ውስጥ እንደሚኖር ያውቅ የነበረና በድብቅም መድሀኒት የሚወስድ ሰው ነበር፡፡ በቃ... አይኑን ማየት አልፈልግም ብላ ለእራስዋ ወዴት መሄድ እንዳለባትና ምን ማድረግ እንዳለባት ጠይቃኝ መክሬአታለሁ፡፡"

ከዚህችኛዋ እናት ታሪክ የምንረዳው አሁንም ግልጽነት በጎደለው መንገድ ባለቤቷ እንደበደላት እና ...ነገር ግን በቤተሰቦቿ በኩል ያለው እውነታ መገለልን ያስወገዱ እና ነገሮችን በአግባቡ የተረዱ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡

*ይቀጥላል*

**ይህንን አምድ አዘጋጅቶ የሚያቀርብላችሁ ESOG-Ethiopian Society of Obstetricians and Gynecologists (የኢትዮጵያ የፅንስና የማህፀን ሀኪሞች ማኅበር) ነው፡፡ (በፖ.ሣ.ቁ 8731 ስልክ 011-5-506068/69 ልታገኙን ትችላላችሁ)**

## ጽንፎች ከገፅ 15 የዞረ

ሆነ፡፡ ግራ ገባት፡፡ አዘነች፡፡ ዮናታን እንዳላት ደሀ አይደለም፡፡ ቱጃር፤ የቱጃር ልጅ ነው፡፡ ራሱን ደሀ አድርጎ የተዋወቃት አውቆ ነው፡፡

ሴቶች ይመጣሉ፡፡ ግን አያምናቸውም፡፡ እሱን ፈልገው ሳይሆን ገንዘቡን ፈልገው የሚጠጉት ይመስለዋል፡፡ ደግሞ እውነቱን ነው፤ ብዙዎች በእሱ ማንነት ተማርከው ሳይሆን በሀብቱ ተደልለው ነው የሚያናግሩት፣ የሚቀጥሩት፣ እወድሃለሁ የሚሉት፡፡

"እኔ ተሳቢዬንና ተለጣፊዬን (ገንዘብ፣ ሀብት) አይታና ፈልጋ ሳይሆን ማንነቴን ወዳና ፈቅዳ የምትመጣ ሴት ነው የምፈልገው" ይላል፡፡

አልሙኒየም የመግጠም ስራ ላይ የተሰማራ "ዮናታን አልሙኒየም" የተሰኘ ድርጅት አለው። የቤት መኪና አለው፡፡ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነው ከሚባል ነገር ውስጥ አንድም የጎደለበት ነገር የለም። እሱ የጎደለ የሚለው "ሀብቴን ሳይሆን እኔን ፈልጋ የምትመጣ ሴት ማግኘት" ነበር፡፡

እንደ ዕድል ሆኖ ህሊናን አገኘ፡፡ ደሀ ሆኖ ተዋወቃት። ድህነቱን ተቀበላ፤ በማንነቱ ብቻ ወደደችው፡፡ "ያሰብኩት ተሳካ፣ ያለምኩት ደረሰ" አለ ዮናታን፡፡ አብዝቶም ወደዳት፡፡

ዮናታን ሀብታም ነው፡፡ የሚኖረው ግን እንደ ደሀ ነው፡፡ ድህነት ውስጥ የሆነ የሚስበው ነገር አለ። ምን እንደሆነ ራሱ ለይቶ አያውቀውም፡፡ ግን ደሀ ይወዳል። በድህነት ይማረካል፡፡ መኪናውን ለጓደኞቹ እየሰጠ በታክሲ ይጠቀማል፡፡ አንዳንዴም የከተማ አውቶብስ ይሳፈራል፡፡ የከተማ አውቶብስ መሳፈር የሚወደው ልጅነቱን ስለሚያስታውሰው ነው፡፡

በልጅነቱ አንዳንዴ አባቱ ተቻኩለው ት/ቤት ሳያደርሱት በሚሄዱ ቀን፤ ለታክሲ ተብሎ የሚሰጠውን ብር ከጓደኞቹ ጋር በአውቶብስ እየተሳፈረ ... የቀረውን ሳንቲም ብስኩት፣ ሳምቡሳ ይበላበት፤ ጀላቲ ይልስበት ነበር፡፡ ከጓደኞቹ ጋር እየተጫወቱ ይጓዙበት ስለነበር - የከተማ አውቶብስ ይወዳል፡፡ ልጅነቱን ስለሚጠራለት።

ህሊናን የተዋወቃት ዕለትም አውቶብስዋ መቆምዋን ሲያይ በቅርብ ርቀት ስለነበር ጥልቅ ብሎ ገባ፡፡ እና ተዋወቁ፡፡

ህሊና ውሸት አትወድም፡፡ ስለማትወድ እንደዋሻት ስታውቅ ተናደደች፡፡ እውነተኛ ማንነቱን ለምን አልነገረኝም ስትል በሸቀች፡፡

"እሱንም ልለየው ወይስ አልለየው?"

ግራ ገባት፡፡

ቀጥራው ስታበቃ የምትነግረውን እያብሰለሰለች የቀጠሮ ሰዓቱን መጠበቅ ጀመረች፡፡

## የሰው ልጅ ከገፅ 11 የዞረ

ይገድሉሃል፡፡ አንገትህን ይቀሉሃል ወይም በጥይት ጭንቅላትህን ይመቱሃል፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስትያኖችን እንደዚያ አድርገዋል" ብሏል - ሃቤን ለሜይልአንላይን፡፡

ሃቤን እና ወንድሙ ህይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው ከኤርትራ ሊቢያ ድረስ የተጓዙት የነገን ብሩህ የአውሮፓ ህይወት አልመው ነው፡፡ ሁለቱ ታዳጊዎች አንገታቸው ላይ ያሰሩትን የእንጨት መስቀል ከልብሶች ስር ደብቀው ክርስቲያን መሆናቸው እንዳይታወቅ በማድረግ ከሞት ተርፈዋል፡፡ ሌሎች ኤርትራውያን ክርስትያኖች ደግሞ ሃይማኖታቸውን ለመለወጥ መገደዳቸውን ለሜይልኦንላይን ተናግረዋል፡፡

የ18 ዓመቱ አማን ሲናገር፤ "አንገቴ ላይ የእንጨት መስቀል አስሬ ነበር፤ ለህይወቴ ስል ግን መጣል ነበረብኝ፡፡ ታጣቂዎቹ ክርስትያኖችን ፍለጋ ነበር የመጡት፡፡ አህዛብን እንገድላለን ሲሉ ከአንገቴ ላይ በጥሼ ጣልኩት" ብሏል፡፡

"አረብኛ እናገራለሁ፤ ስለዚህ ክርስትያን እንዳልሆንኩና የእነሱ እምነት ተከታይ እንደሆንኩ አስመስዬ ቀረብኩ፤ እነሱም አመኑኝ" ሲል ከቡድኑ አሰቃቂ ግድያ ያመለጠበትን ሁኔታ አስረድቷል፡፡

ሃቤን እና ታናሽ ወንድሙ ሳሙኤል እንዲሁም አማን እና ተስፋለም፤የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ሲሆኑ ከ15 ቀናት በፊት አስቸጋሪውን የሜዲትራንያን ባህር በጀልባ በማቋረጥ አውሮፓ ለመግባት ችለዋል፡፡ ባለፈው እሁድ በአሸባሪው ቡድን ISIS አንገታቸውን የተቀሉት ኢትዮጵያውያንም ባህር ተሻግረው አውሮፓ ለመግባት ሲጠባበቁ ነበር ተብሏል፡፡

*ለሟቾች ቤተሰቦችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን እንመኛለን!!*

## ምሽት ከገፅ 8 የዞረ

"ግደፍንዶ" ስትል ልክ ትግርኛው እንዳልገባኝ "እኔምኮ ለመግደፍ ነው አጥብቄ የምዳብስ" ስላት ሳቀችብኝ፡፡

አንደበቷ ማር ማር እንዳለኝ፣ የጥርስዋ ውበት ልቤ ላይ እንደተሰካ፣ ፈገግታዋ የደስታ ሽቱ በሰውነቴ ላይ እንደረጨ፣ ትንፋሽዋ ነዶ እሳት ሆኖ አካሌን እንዳቀጣጠለው በዓይኗ ዕይታ ህይወቴ እንደተማረከ ተለያየን፡፡

እናም እቴማንችን አቅፌ በትዝታ ከርግበ ጋር ስንደንስ ሌሎች ጓደኞቼም እየተቃቀፉ ብልጭ ድርግም በሚለው መብራት በመሽከርከር ላይ እንዳሉ መሬት የሚያናውጥ ተኩስ ተከፈተ፡፡ ተቃቅፎ ይደንስ የነበረው ሁሉ ተለያየ፡፡ በተኩሱ ያለንበት ኢትዮጵያ ሆቴል ብቻ ሳይሆን ከተማዋ ተናወጠች፡፡ ተደናግጠን ስንረበሽ በበሩ በኩል "እጅ ወደ ላይ እጅ ወደ ላይ" የሚል ኃይለኛ ድምጽ ሰማን። ነገሩ ግራ የሚያጋባ ሆነ፡፡ መሳሪያ የያዙ ፖሊሶችና የአብዮት ጥበቃዎች እኛ ወዳለንበት አራስ ነብር መስለው ሲገቡ፣ አቶ ሞላ የተባሉት የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር በቀኝ እጃቸው ማካሮቭ ሽጉጣቸውን ይዘው ወደ እኛ ቀረቡና፤

"አብዮታዊ ሠራዊት በየጦር ግንባሩ በሚፋለምበት በአሁኑ ሰዓት እናንተ እዚህ ጆሊ ጃኪዝም ታካሂዳላችሁ፡፡ ባርቴ መስርታችሁ አገር ታምሳላችሁ፡፡ እኛ ከኢሰፓኮ ሌላ ባርቲ አናውቅም። ፈሽፋሻ ሁላ፡፡ እነዚህ የሠው ህዝብ ልጆች የሆኑት ልጃገረዶች የእናንተ መጫወቻዎች ናቸው እንዴ? ቅደም? ወደፊት? አሉ፡፡ የአዲራት ከተማ የአብዮት ጥበቃ አባላትና ፖሊሶች እያጣደፉ ወስደው ከሌሊቱ በ7 ሰዓት ጨለማ በዋጠው እስር ቤት ወስደው ወረወሩን፡፡ ልጃገረዶችም እኛ ከታሠርንበት ቀጥሎ ባለ ክፍል ታሰሩ፡፡ እስራቱ ለሶስት ቀን ያህል ቀጠለ፡፡ በኋላ እንደተረዳሁት፤ እነ ከንፈ አበራ ፓርቲ ሲደግሱ ቀበሌውን ማስፈቀድ ነበረባቸው፡፡ ታስረን በሀሳብ ስንንገላታ በእኛና በሴቶች እስር ቤት መሃል ባለ ቀዳዳ በኩል አንዲት ወረቀት ወደ እኛ ተወረወረች፡፡

"የአውራጃ አስተዳዳሪውና የፖሊስ አዛዡ ባሉበት ለምርመራ ልንቀርብ ስለሆነ ቃላችሁ አንድ እንዲሆን፡፡ ይኸውም መምህር ኩምሳና ምጽላል ትኩ ለመጋባት ቃል ኪዳን ስለገቡ ይህንኑ ምክንያት አድርገው ራት ስለጋበዙን ነው በምሽቱ ግብዣ ላይ የተገኘነው በሉ" ትላለች ወረቀቲቱ፡፡ ምጽላል የመምህር ኩምሳ የሴት ጓደኛ ስትሆን የወታደር ልጅ ናት፡፡ እናም ዘዴው በአባቷ በኩል የመጣ ይመስለኛል፡፡

እንደተባለው አወራጃ አስተዳዳሪውና የፖሊስ አዛዡ በተገኙበት ለምርመራ ተጠራን፡፡ የአሥራ ሁለታችንም ቃል አንድ ሆነ፡፡ በወቅቱ ስለ ጆሊጃኪዝም አስከፊነት በስፋት በመገናኛ ብዙኀን ይነገር ነበርና በተለይ አውራጃ አስተዳዳሪው


"ፀሐይ ያየቺውን ሰው ሳያየው አይቀርም" የሚባል የትግሪኛ ተረት አለ፡፡ "እናንተ ኢትዮጵያ ሆቴል የተሰባሰባችሁት ኩምሳና ምጽላል ቃል ኪዳን ስለተገባቡ ሳይሆን የሰፌውን ህዝብ ልጆች ለማማገጥ ነው፡፡ ለዚህ እኛ ትዕግሥት የለንም፤ እስከ 6 ወር እና እስከ አንድ ዓመት ልናሳስራችሁ እንችላለን፡፡ ግን የተወሰናችሁት መማህራን/መምህራን ለማለት/ ስለሆናችሁ የመማር ማስተማሩ ሂደት ይጎዳል። ወደፊት ሆቴል ውስጥ ሆነ በሌላ ቦታ ከሴት ጋር ብትገኙ እርምጃችን የከበደ ይሆናል፡፡ ለዚሁ በቂ ዋስ እየጠራችሁ ልትፈቱ ትችላላችሁ" አሉ፡፡

በወቅቱ ሁሉም ዋስ እያቀረቡ ሲፈቱ እኔ እንግዳ ስለሆንኩና ሰውም ገና ስለአላወቅሁ ዋስ አጣሁኝና ተለይቼ ስቀር ምንም የማላውቀውና የአሰፋ ክንደያ ወንድም የማነ የተባለ የአዲግራት ተወላጅ ዋስ ሆኖ አስፈታኝ፡፡ የሰው አገር ሰው ለምን ተለይቶና ታስሮ ቀረ ብለው ከየማነ ጋር የነበሩት ሰዎች በመፈታቱ ተደስተው ይዘውኝ ወደ ቤቴ ስንሄድ፣ በመንገድ ላይ አንድ አውራ ደሮ ተንደረደረና ከአንዲቱ ደሮ ላይ ወጣባት፡፡ በዚህ ጊዜ እኔ፤ "ኸረ አንተ አውራ ዶሮ! ጆሊጃኪዝም አካሄደ ተብለህ እንዳትታሰር!" ስል ሰዎቹ በጣም ሳቁ፡፡ በሌላ ጊዜ አዲግራቶች "አንተ አውራ ዶሮ ተው እንዳትታሰር አለ ዘሥሩግ" እያሉ እንደተረት ያወሩ ጀመር፡፡

በኋላ ላይ እንደተረዳሁት ከእስራት በቶሎ እንድፈታ አውራጃ አስተዳዳሪውንና የፖሊስ አዛዡን ያግባባልን አሁን አሜሪካ ውስጥ የሚኖረውና የቀበሌው ሊቀመንበር የነበረው አቶ ታፈረ ኃይለሥላሴ ነው፡፡


dasani road race 2015
14 JUNE 2015
7.5KM FOR MASS & 15KM FOR ATHLETES
REGISTER NOW!
100 BIRR TO REGISTER
ዳሳኒ የጎዳና ላይ ሩጫ
ሰኔ 7 ይካሄዳል፤ አሁኑኑ ይመዝገቡ !
dasani road race
great ethiopian run

አደጋ ከገፅ 1 የዞረ



ሙሉጌታ አስፋው ተናግሯል፡፡ የእንዳልካቸውን ህልፈት በስልክ ለቤተሰብ ያረዱት ለቀጣዩ የባህር ጉዞ ተረኛ የነበሩና እርሱን በቅርበት የሚያውቁት ስደተኞች ናቸው፡፡

“ወንድማችን ሱዳን ውስጥ ሲኖር የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ራሱን ያስተዳድር ነበር” የሚለው የሟች ወንድም፤ ባጠራቀመው ገንዘብ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ አውሮፓ ለመሻገር ጥረት ሲያደርግ ባደረገበት አጋጣሚ ከቤተሰቡ እንደተነፋፈቀ መቅረቱ ለቤተሰቡ መሪር ሀዘን እንደሆነበት ተናግሯል፡፡ “ዴይሊ ሜይል” ጀልባዋ 950 ኤርትራዊያን፣ ኢትዮጵያውያንና ሶማሊያውያን ስደተኞችን አሳፍራ ስትጓዝ መስጠሟን የዘገበ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 200 ያህሉ ሴቶች እንደነበሩ ጠቁሟል፡፡

ከአደጋው የተረፉት 28 ብቻ መሆናቸውን የዘገበው ጋዜጣው፤ ሲሆኑ አስከሬናቸው የተገኘው የ20ዎቹ ብቻ ነው ብሏል፡፡ “አልጀዚራ” እና “ዘ ጋርዲያን” በበኩላቸው ጀልባዋ 700 ስደተኞችን አሳድራ እንደነበር ጠቁመውየተረፉት 28 አስከሬናቸው የተገኘው 20 ብቻ መሆኑን ዘግበዋል፡፡

አደጋው የተፈጠረው በጀልባዋ ላይ ተፋፍገው የተጫኑት ስደተኞች በርቀት ሌላ የንግድ መርከብ ተመልክተው ጥሪ ለማቅረብ ሲሉ በፈጠሩት ግርግር ጀልባዋ ሚዛኗን በመስጠሟ ነው ብለዋል ዘገባዎች፡፡

ከአደጋው የደረሰው ከሊቢያ የባህር ዳርቻ 96 ኪ.ሜ እንዲሁም ከጣሊያኗ የስደተኞች መዳረሻ ላምፔዱሣ ደሴት 193 ኪ.ሜ ርቀት ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡

ወጣት ከገፅ 1 የዞረ

ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ከቤተሰቦችዋ ጋር አንዳችም ግንኙነት ባለማድረግዋ ቤተሰቦችዋ የትና በምን ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ሊያውቁ እንዳልቻሉ ይገልፃሉ። ወደ ሳውዲ የላካት ኤጀንሲ ሀያት አሊ ያለችበትን ሁኔታና የት እንደምትገኝ እንዲያሳውቃቸው ቤተሰቦቿ ኤጀንሲውን ቢጠይቁም ኤጀንሲው ምላሽ ባለመስጠቱ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማመልከታቸውን ተናግረዋል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ኤጀንሲው ወጣቷ ያለችበትን ሁኔታ በአፋጣኝ ተከታትሎ እንዲያሳውቅ ያሳስባል፡፡ ኤጀንሲውም ሳውዲ ድረስ ሄዶ ወጣቷን ለማግኘት ቢሞክርም እንዳልተሳካለት ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አሳውቋል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሀያት አሊ መሐመድ የተባለችው ወጣት በምን ሁኔታና የት እንደምትገኝ ተጣርቶ ምላሽ እንዲሰጠው ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ለቆንስላዎች ጉዳይ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ጥያቄ ያቀርባል፡፡

የቆንስላ ጉዳይ ክትትል ቢሮው በበኩሉ፤ ወጣቷ የምትገኝበት ሁኔታ ተጣርቶ እንዲገለፅለት ሪያድ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጥያቄ ቢያቀርብም ከኤምባሲው ምላሽ ሊገኝ ባለመቻሉ የሃያት ቤተሰቦች እጅግ በከፋ ሃዘንና ሰቀቃ ውስጥ እንደሚገኙ የወጣቷ እህት የኔነሽ አያሌው ለአዲስ አድማስ ገልፃለች፡፡

የወጣቷ ደብዛ መጥፋት በእጅጉ ያሳሰባቸው ቤተሰቦች፤ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ጨምሮ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በተደጋጋሚ የአፋልጉን ጥሪ ቢያቀርቡም እስካሁን ምላሽ አለማግኘታቸውን የጠቆመችው የኔነሽ፤ ኤጀንሲው ተግባሩን በአግባቡ ባለመውጣቱ የሥራ ፈቃዱ እንዲታገድ በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሐምሌ 24 ቀን 2006 ዓ.ም ትዕዛዝ ቢተላለፍበትም ኤጀንሲው አሁንም በስራ ላይ እንደሚገኝ ገልፃለች፡፡

‹መንግስት ህገ ወጥ ስደትን እቃወማለሁ፤ ዜጎች በህጋዊ መንገድ ወደሚፈልጉበት አገር ለስራ መሄድ ይችላሉ› ባለው መሰረት፣ ዕድሉን ተጠቅማ በህጋዊ መንገድ የሄደችው እህቴ፤ ያለችበት ሳይታወቅ ሁለት ዓመት ከሶስት ወራት ማለፉ እጅግ የሚያሳዝንና ስጋት የሚፈጥር ነው ያለችው የኔነሽ፤ “የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተረባርበው እህቴ ያለችበትን ሁኔታ እንዲያሳውቁንና ከስጋት እንዲያወጡን እማፀናለሁ” ብላለች፡፡ ስለጉዳዩ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ለመጠየቅ ያደረግነው ተደጋጋሚ ሙከራ ሳይሳካልን ቀርቷል፡፡

ሳይንስ ከገፅ 14 የዞረ

ሞሎኪላዊ መዋቅር ያሉ ሞሎኪሎች ትስስር በየቅፅበቱ ይቀያየራል። ሆኖም መዋቅሩ የተለያዩ ሞሎኪሎችን እየተቀበለ እና እየሸኘ ለረጅም ጊዜ ይዘልቃል፡፡ የዚህ ዘላቂ ሞሎኪላዊ መዋቅር መኖር፤ መረጃው ተመዝግቦ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ነገሩን ከፍተኛ የሜሞሪ አቅም ካለው ኮምፒውተር ጋር ያነፃፅሩታል፡፡ እናም «የውሃ ሞሎኪላዊ መዋቅር የውሃ ፊደል ወይም አልፋቤት ነው» የሚሉት ፕሮፌሰር ሩስተም ሮይ፤ «እነዚህን ፊደሎች በመጠቀም ውሃ አረፍተ ነገር ይሰራል፡፡ ይህን አረፍተ ነገርም መቀያየር ይቻላል» ይላሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዶኩመንታሪው የተጠቀሰ አንድ ነገር አለ፡፡ ጉዳዩ በጊዜው በ«ኒዮርክ ታይምስ» ጋዜጣ ተዘግቦ ነበር፡፡ «ላራ» የተሰኘች አንዲት መርከብ በ1881 ዓ.ም (እኤአ) ከሊቨርፑል ወደ ሳንፍራንሲስኮ ጉዞ ጀመረች፡፡ ጉዞ በጀመረች በሦስተኛው ቀን፤ የእሳት ቃጠሎ ተፈጠረና ተጓዦቹ መርከቧን ለቅቀው በመውረድ የነፍስ አድን ጀልባ ላይ በመሳፈር ህይወታቸውን አተረፉ፡፡ የነፍስ አድን ጀልባ በመጠቀም ከተጓዙት ሰዎች መካከል፤ የመርከቧ ካፒቴን አንዱ ነበሩ፡፡ የተወሰኑ ሰዎችን የያዘችው እና የመርከቧ ካፒቴን የተሳፈሩባት ጀልባ የያዘችው ውሃ አለቀ፡፡ የሚጓዙበት የውቂያኖሱ ውሃ ሊጠጣ የሚችል አልነበረም፡፡

ሆኖም ከሦስት ሳምንታት የባህር ላይ ቆይታ በኋላ መሬት ረገጡ፡፡ እናም፤ «ካፒቴኑ ውሃ ጥሙን ተቋቁማችሁ እንዴት በህይወት ልትተርፉ ቻላችሁ?» ተብለው ሲጠየቁ፤ «የአዕምሮ ኃይላችንን በማሰባሰብ፤ የውቂያኖሱን ውሃ እንደ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እናስበዋለን። ከጀልባችን ሥር ያለው ሰማያዊው የውቂያኖስ ውሃ፤አረንጓዴ ቀለም ወዳለው የመጠጥ ውሃ ይቀየርልን ነበር» ብለዋል፡፡ በፍፁም እምነት የውሃን ዐረፍተ ነገር ቀየሩት ማለት ነው፡፡ የባህሩ ውሃ የሚጣፍጥ የመጠጥ ውሃ ይሆንላቸው ነበር፡፡

የሩሲያ የተፈጥሮ ሳይንስ አካዳሚ ፕሮፌሰር የሆኑት ኮንስታንቲን ካርትኮቭ (Konstantin Korotkov)፤ «አንድ በጣም የታወቀ ምሣሌ እናንሳ» ይላሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፡፡ «ኢየሱስ ክርስቶስ ውሃውን ወደ ወይን የቀየረው ስኳር ወይም ላክቶስ ውሃው ውስጥ ጨምሮ አልነበረም፡፡ እኛ የተለያዩ ነገሮች በውሃ ናሙናችን ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለመመርመር ሞክረናል» ይላሉ፡፡ ማግኔቲክ ፊልድ፣ ኤሌክትሪካል ፊልድ፣ ሌሎች ቁሳቁሶች፣ የሰው በውሃ አጠገብ መገኘት፣ እንዲሁም የሰዎች በጎ እና መጥፎ ስሜቶች በውሃ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለማጥናት ሞክረናል» ካሉ በኋላ፤ «ከሁሉም ነገሮች በበለጠ በውሃ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድረው የሰዎች ስሜት መሆኑን ተረድተናል» ብለዋል፡፡

ፕሮፌሰር ካርትኮቭ በላብራቶሪያቸው በርካታ ሙከራዎችን አድርገዋል፡፡ ከእነዚህ ሙከራዎች መካከል፤ ሰዎች የተለያየ ስሜት ይዘው ከውሃው አጠገብ እንዲቀመጡ ማድረግ ነው፡፡ ከተለያዩ ሰዎች ፊት ለፊት በብርጭቆ ውሃ አስቀምጠው፤ ውሃን ፍቅር፣ ርህራሄ እና መሳሳትን የመሳሰሉ አዎንታዊ ስሜቶች ይዘው ውሃውን እንዲመለከቱ አደረጉ፡፡ ከዚያም በሌሎች ብርጭቆዎች ውሃ ሞልተው፤ ጥላቻ እና ቁጣ የመሳሰሉ አሉታዊ ስሜቶች ይዘው እንዲቀመጡ አደረጉ፡፡ ከዚያም ናሙናዎቹን ሲመረምሩ፤ የታየው ሁኔታ ፍፁም የተለያየ ነበር፡፡ ፍቅር የውሃውን የኃይል መጠን (energy level) ከፍ እንዳደረገው እና የተረጋጋ ባህርይ እንደታየበት አረጋግጠዋል፡፡ በተቃራኒው፤ መጥፎው ስሜት የውሃውን የኃይል መጠን በእጅጉ እንደቀየረው አስታውቀዋል፡፡

የጃፓን ተመራማሪዎች ባደረጉት ምርምር፤ ውሃ ለጥሩ እና ለመጥፎ ስሜት እንዲጋለጥ ካደረጉ በኋላ በውሃው ላይ የተፈጠረውን ለውጥ ፎቶ ለማንሳት ሞክረዋል፡፡ ልዩነቱ አስገራሚ ነው፡፡ «ታስጠላኛለህ» የተባለው የብርጭቆ ውሃ በጣም አስፈሪ ወይም አስቀያሚ የተዘበራረቀ መልክ አለው፡፡ «እወድሃለሁ» የተባለው ውሃ ደግሞ በጣም የሚያምር እና የአልማዝ ጌጥ መስሎ ይታያል፡፡

በቦታ ጥበት ሳቢያ፤ ከዚህ በላይ ላጫውታችሁ አልቻልኩም፡፡ መነሻ ካደረግሁት ጉዳይ ጋር የተያያዘ አንድ ነገር አንስቼ ፅሁፌን ልቋጭ፡፡ ተመራማሪዎች፤ በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ፀሎት የተደረገበትን ውሃ፤ ከፀሎት በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር በማነፃፀር ፍፁም የተለያየ ባህርይ እንዳላቸው አረጋግጠዋል፡ ፡ የቤትሆቨን እና የሮክ ሙዚቃ እንዲሰሙ በተደረጉ ውሃዎች መካከል ያለው ልዩነት እጅግ አስገራሚ ነው፡፡ የሰው ልጅ 70 በመቶ ውሃ ነው፡፡ ይቆየን፡፡


# አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ
# የሐዘን መግለጫ

ሰሞኑን በሊቢያ፣ በደቡብ አፍሪካ እንዲሁም በየመን በኢትዮጵያውያን ዜጎቻችን ላይ የተፈጸመውን ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ አጥብቆ ያወግዛል፡፡ በመሆኑም ኩባንያችን በእነዚህ ሃገራት በዜጎቻችን ላይ በደረሰው አረመኔያዊ የግፍ ግድያ ሰለባ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፣ ቤተሰቦችና ለመላው የአገራችን ሕዝቦች የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን እየገለጸ ለሁሉም ልባዊ መጽናናትን ይመኛል፡፡

# የባሬቶ ምትክ ከየት እንደሚገኝ አልታወቀም





ግሩም ሠይፉ

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከአሰልጣኝ ማሪያኖ ባሬቶ ጋር የተፈራረመው የሁለት ዓመታት የኮንትራት ውል እንዲቋረጥ ተደረገ፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከወር በኋላ በተለያዩ አህጉራዊ ውድድሮች የሚሳተፍ ሲሆን የዋና አሰልጣኙ ቅጥር ዝግጅቶችን በትኩረት ለማድረግ ወሳኝ ይሆናል፡፡ የዋና አሰልጣኙ ኮንትራት የፈረሰው ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በደረሱበት የጋራ ስምምነት መሠረት እንደሆነ ያመለከተው የፌዴሬሽኑ ህዝብ ግንኙነት፤ የአሰልጣኙ ስንብት በመከባበር ስሜትና በሠለጠነ አግባብ እንደተፈፀመ እንዲሁም ውሉን በማቋረጥ ሊከሰት የሚችለውን ውጣ ውረድ በማስወገድ ወደፊት በትብብር ለመሥራት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስች ነው ብሏል፡፡

የውል ስምምነቱ መቋረጡን ተከትሎ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አንድ ዓመት በብሄራዊ ቡድኑ ለሰሩት አሠልጣኝ ማሪያኖ ባሬቶ ተጨማሪ የሦስት ወር ደመወዝ ከፍሏቸዋል፡፡ ፌደሬሽኑ እና ማርያኖ ባሬቶ በተተኪ ወጣቶች ላይ የተጀመረው የእግር ኳስ ልማት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ በመተባበር መንፈስና በጋራ ለመሥራት እንደተስማሙ ተገልፆ፤ አሠልጣኙ ወጣት ተጫዋቾች ከፍተኛ ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ የጀመሩትን ጥረት አጠናክረው ለመቀጠል ቃል መግባታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ፖርቱጋላዊው ማርያኖ ባሬቶ በተለይ ለሱፐር ስፖርት በሰጡት አስተያየት በኢትዮጵያ ጥሩ እየሰሩ እንደነበር ተናግረው፤ ከቤተሰብ ጋር ለረጅም ጊዜ በሚያራርቀው ሃላፊነታቸው የተፈጠሩ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለስንብታቸው እንደ ዋና ምክንያታቸው ጠቅሰውታል፡፡ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ዋና አሰልጣኝነት ሲቀጠሩ ገና ከጅምሩ በፌደሬሽኑ በኩል የተፈጠሩባቸው አንዳንድ ውስብስብ ችግሮች መኖራቸውን በማንሳትም በወቅቱ ከፌደሬሽኑ ይፈልጓቸው የነበሩ ድጋፎች በማነሳቸው ስራቸውን ወዲያውኑ ለመልቀቅ አመንትተው እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ በስንብታቸው ምንም ፀፀት እንደማይሰማቸው፤ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ወጣት ተጨዋቾችን በማሳደግ ባበረከቱት አስተዋፅኦ እንደሚደሰቱ ለሱፐር ስፖርት ያሳወቁት ማርያኖ ባሬቶ፤ ለቡድኑ መጭው ጊዜ የተሳካ እና በውጤት ያማረ እንዲሆንም ተመኝተዋል፡፡

የፌደሬሽኑ ፕሬዝዳንት አቶ ጁነዲን ባሻ በበኩላቸው ለሱፐር ስፖርት ሲናገሩ የአሰልጣኙ የቅጥር ኮንትራት የመጀመርያ ምዕራፍ ሊገባደድ የቀሩት 10 ቀናት እንደነበሩ ጠቅሰዋል፡፡ ከዋልያዎቹ በኋላ ለማርያኖ ባሬቶ በስራ ዘመናቸው መልካሙን ሁሉ እንዲገጥማቸው የተመኙት ፕሬዝዳንቱ ምስጋናቸውን ለአሰልጣኙ አቅርበዋል። የፌደሬሽኑ ፕሬዝዳንት ስለ ብሄራዊ ቡድኑ ምትክ አሰልጣኝ ቅጥር ከሱፐር ስፖርት ለቀረበላቸው ጥያቄ ዝርዝር ምላሽ ከመስጠት ተቆጥበዋል፡፡

ማሪያኖ ባሬቶ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በፊት በብሄራዊ ቡድን ደረጃ ያሰለጠኑት ብቸኛው የጋና ብሄራዊ ቡድን ሲሆን የሰባት ወራት ቆይታ አድርገዋል፡፡ ከጋና እግርኳስ ማህበር ጋር የተስማሙትን የአሰልጣኝነት ውል ህገወጥ በሆነ መንገድ በማፍረስ ከሃላፊነት በመልቀቃቸው ፊፋ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ በገብቶ ውል በማፍረሳቸው 83 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ለጋና እግርኳስ ማህበር እንዲከፍሉ ቀጥቷቸው ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ፌዴሬሽኑ ማርያኖ ባሬቶን ካሰናበተ በኋላ ሃላፊነቱን የሚረከብ ባለሙያ ከየት እንደሚገኝ የታወቀ ነገር የለም፡፡ በተለያዩ ሁኔታዎች ለብሄራዊ ቡድኑ አሰልጣኝነት ላለው ክፍት የስራ ቦታ ላይ ሁነኛ ምትክ ለማግኘት አጠያያቂ ይሆናል። የመጀመርያው ባለሙያው የተፈለገው በብዙ አገራት የእግር ኳስ የውድድር ዘመኑ አጋማሽ ላይ ባለበት ወቅት መሆኑ ብቁ አሰልጣኝ የማግኘት እድሉን ስለሚያጠብበው ሲሆን፤ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን ያው የአመራር ክፍተት እና ልዩነት የቅጥሩን ስኬታማነት እንደሚያስተጓጉል አስተያየት እየተሰጠ ነው፡፡

# ዓለም አቀፍ የስፖርት ቀን ይከበራል

ዓለም አቀፍ የስፖርት ቀን ለልማትና ለሰላም በሚል መርህ በአዲስ አበባ ስታዲየም በተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚከበር ታወቀ፡፡ በኢትዮጵያ ለሁለተኛ ጊዜ የሚከበረው የስፖርት ቀኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰላምና የዕድገት መርሆችን መሠረት ያደርጋል። ባለፈው ዓመት ዓለም አቀፍ የስፖርት ቀን ለሰላምና ለልማት በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እና በኢትዮ-ጀርመን የረጅም ጊዜ የእግር ኳስ ፕሮጀክት ትብብር አማካኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ በድምቀት ተከብሯል፡፡ ለስፖርት ቀኑ በወጣው ፕሮግራም መሠረት በስድስት የወንዶችና ሴቶች ታዳጊ እግር ኳስ ክለቦች የእግር ኳስ ውድድሮች ይካሄዳሉ፡፡ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ24 ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የተለያዩ ሀገሮች አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች ፣የፌደራል ስፖርት ከሚሽን ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች፣ የኢትዮጵያ እግር የፌዴሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እና የስፖርት ቤተሰቦች ተሳታፊና ተካፋይ እንደሚሆኑ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ ያመለክታል፡፡ ስፖርት በተለይም እግር ኳስ ሕዝቦችን የማቀራረብ፣ ወዳጅነትን የማጠናከር፣ ፍትሃዊነትን የማስፈን፣ ልዩነቶችን የማቻቻልና መከባበርን የማስፈን ጉልህ ፋይዳ እንዳለው የጠቀሰው መግለጫ፤ ዓለም አቀፍ የስፖርት ቀን ለሰላምና ለልማት በዓል ይህን ከግምት በማስገባት እንደሚካሄድ ታውቋል፡፡

# ለኢትዮጵያ ቡና ስፖርት ክለብ ሩጫ ይካሄዳል

ለኢትዮጵያ ቡና ስፖርት ክለብ ገቢ ማሰባሰቢያ የሚሆንየ 10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ከሳምንት በኋላ ሊካሄድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቡናና የስፖርት ቤተሰቦች የክለቡን የገቢ አቅም ለማጠናከር የጎዳና ላይ ሩጫው በየዓመቱ እንዲደረግ ፍላጎት አላቸው፡፡ በሩጫው ላይ ለመሳተፍ ምዝገባው ሜክሲኮ ቡናና ሻይ የክለቡ ፅ/ቤት እየተከናወነ ሲሆን የመሮጫው ቲሸርት ዋጋ 150 ብር ነው፡፡ የ10 ኪሎሜትር የጎዳና ላይ ሩጫው መነሻው ለክለቡ የመኖርያ ካምፕ በሚገነባበት እና ለስታድየም በተሰጠው ቦታ ላይ እንደሆነ አዘጋጆቹ ገልፀው፤ ጀሞ ኮንደሚንየም ፣ ሚካኤል አደባባይ ፤ አየር ጤና አደባባይ የሚያቋርጣቸው ቦታዎች እንደሆኑና ዞሮ መድረሻው የተነሳበት ቦታ ላይ እንደሚሆን አስታውቀዋል፡፡

በ1975 ዓ.ም በተጠናከረ መልኩ የተመሠረተው የኢትዮጵያ ቡና ስፖርት ክለብ የተጨዋቾች መኖርያ ካምፕን ለመገንባት እና የስታድዬም ስራውን ለማነሳሳት በጎዳና ላይ ሩጫው ከፍተኛ መነቃቃት እንደሚፈጥር ተጠብቋል፡፡

ሃበሻ ስፖርት ከተባለ ድረገፅ ስለክለቡ ታሪክ ከተፃፈው ዘገባ ለመረዳት እንደተቻለው የኢትዮጵያ ቡና ስፖርት ክለብ እንደ አብዛኛዎቹ የሀገራችን ክለቦች የራሱ የሆነ የውድድር ሜዳ የለውም፡፡ በ1997 ዓ.ም የራሱን ስታዲየም ለመገንባት ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት 35.000 ካ.ሜ ቦታ ተረክቧል፡፡ በሌላ በኩል የቡና ክለብ በቀደምት ጊዜያት በቡና ገበያ ኮፕሬሽን ቅጥር ግቢ በኋላም ከመንግስት በጊዜያዊነት በተሰጠው ቦታ የተገነባ የተጨዋቾች መኖሪያ ካምፕ ነበረው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በወር 18.000ብር ከግለሰብ የተከራየው የተጨዋቾች መኖሪያ ካምፕ አለው፡፡

ክለቡ የራሱን መኖሪያ ካምፕ መገንባት እንዲችል ለአዲስ አበባ መስተዳድር የቦታ ጥያቄ አቅርቧ 3.000 ካሬ ሜትር ቦታ አግኝቷል፡፡ በዚህ ዓመትም 10ሚሊዮን ብር በመመደብ ጅምናዚየምን ያካተተ ዘመናዊ የተጨዋቾች መኖሪያ ካምፕ ለመገንባት አስፈላጊው የዲዛይን ስራ አጠናቆ ወደ ትግበራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡



የጎዳና ላይ ሩጫው እነዚህን እንቅስቃሴዎች ለመደገፍ እና ለማነቃቃት እንደተዘጋጀ ተገልጿል፡፡

ከተለያዩ የክለቡን ታሪክ ከሚያወሱ ምንጮች ለመገንዘብ እንደተቻለው የኢትዮጵያ ቡና ክለብን በባለቤትነት የሚያስተዳድሩት ማህበራት እና ድርጅቶች ከስምንት በላይ ይሆናሉ፡፡ እነሱም የቡና ላኪዎች ማህበር፤ የቡና አቅራቢዎች ማህበር፤ የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር፤ የቡና ቆዪዎች ማህበር፤ የቡና ግሮዎርስ ፕሮዲውስ ኤክስፖርተርስ አሶሴሽን፤ የሀገር ውስጥ ቡና ንግድ ማህበር፤ የኢትዮጵያ ቡና ደጋፊዎች ማህበርና ሐበሻ ቢራ አክሲዮን ማህበር ናቸው፡፡ የቡና ማህበራቱ ከሁለት ዓመት በፊት በቶን 5ብር የነበረውን የመዋጮ ድጋፍ ወደ 30 ብር ከፍ በማድረጋቸው የክለቡ ዓመታዊ በጀት ወደ 20.000.000 (ሃያ ሚሊዮን) እንዳደገ ታውቋል፡፡

በአፍቃሪ ደጋፊዎች ብዛት ከኢትዮጵያ ክለቦች ግንባር ቀደም ሆኖ የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ ቡና ስፖርት ክለብ በቀድሞው የኢትዮጵያ ሻምፒዮና በአሁኑ ኢትዮጵያ ፕርሚየር ሊግ እኩል አንድ ጊዜ የዋንጫ ተሸላሚ ነበር። በኢትዮጵያ ጥሎ ማለፍ ውድድር አምስት ጊዜ፤ በኢትዮጵያ ክለቦች አሸናፊዎች አሸናፊም ለስድስት ጊዜ የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ በኢንተርናሽናል ውድድር ተሳትፎው ደግሞ በሦስቱ አህጉር አቀፍ የክለቦች ውድድርና በአንድ የምስራቅ አፍሪካ ክለቦች ዋንጫ ውድድር በመወከል ተወዳድሯል፡፡

በዋናው የአፍሪካ ክለቦች ዋንጫ ሁለት ጊዜ በምስራቅና መካከለኛው ክለቦች ዋንጫ አንድ ጊዜ ኢትዮጲያን በመወከል ሲሳተፍ በኮንፌዴሬሽን ካፕና አሸናፊዎች አሸናፊ ዋንጫ ግን ከሁለት ጊዜ በላይ ተሳታፊም ነበር፡፡

# ገንዘቤ በላውረስ ሽልማት የመጀመርያዋ ኢትዮጵያዊ ሆነች




በስፖርቱ ዓለም የላቀ ብቃት ላሳዩ እና በስኬታቸው ከፍተኛ አድናቆት ላገኙ አትሌቶች በሚሸለሙበት ዓመታዊው የላውረስ የምርጥ ስፖርተኛ ሽልማት አትሌት ገንዘቤ ዲባባ የመጀመርያዋ ኢትዮጵያዊ ተሸላሚ አትሌት ሆነች፡፡ በአትሌቲክስ የላውሬስ የዓመቱ ምርጥ ሴት ስፖርተኛ ሆና የተመረጠችው ገንዘቤ ባለፈው ዓመት በሁለት ሳምንታት ውስጥ ሶስት ክብረ ወሰን መስበርዋ፤ በ5000 እና በ2000 ሜትር የዓመቱን ፈጣን ሰዓት በማስመዝገቧ እና በ3ሺ ሜትር የኢንተርኮንትኔንታል ሻምፒዮና በመሆኗ ነበር፡፡

በ2015 በዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌደሬሽኖች ማህበር የዓለም ኮከብ አትሌቶች ምርጫ ከመጨረሻዎቹ ሶስት እጩዎች አንዷ ለመሆን የበቃችው የመካከለኛ ርቀት ምርጥ ሯጭ ገንዘቤ ዲባባ፤ ለመጀመርያ ጊዜ የላውረስ ሽልማትን የተጎናፀፈች ኢትዮጵያዊ አትሌት ሆናለች፡፡ በተያያዘ ሰርቢያዊው ሜዳ የቴኒስ ተጫዋች ኖቫክ ጆኮቪች የላውሬስ የዓመቱ ምርጥ ወንድ ስፖርተኛ ሆኗል። ለ27 ዓመቱ ኖቫክ ድጅኮቪች የላውረስ ሽልማት ለሁለተኛ ጊዜ ያገኘው ሲሆን የመጀመርያውን የተሸለመው በ2011 እኤአ ላይ ነበር፡፡ ታዋቂው የሜዳ ቴኒስ ኮከብ ኖቫክ በ2015 እኤአ ላይ በተለያዩ ውድድሮች ከ5 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሽልማት ገቢ ሲያስገባ፤ በ2014 እኤአ ላይ ደግሞ 11.6 ሚሊዮን ዶላር ገቢ በማስመዝገብ ከሜዳ ቴኒስ ተጨዋቾች የመጀመርያ ነበር፡፡ ኖቫክ በፎርብስ መፅሄት የሃብት መጠኑ እስከ 90 ሚሊዮን ዶላር ተተምኖለታል፡፡

ለዓመታዊው የላውረስ ሽልማት በሻንጋይ ከተማ በሚገኘው ግራንድ ቲያር አዳራሽ በተዘጋጀው ስነስርዓት ላይ ትልልቅ የሆሊውድ ዝነኛ ተዋናዮች ተገኝተው ነበር፡፡ ከመካከላቸው በሙላቱ አስታጥቄ የማጀቢያ ሙዚቃ በተሰራለት ብሮከን ፍላወርስ ፊልም ላይ የተወነው እውቅ ተዋናይ ቢል ሙራይ እንዲሁም ሱፐር ማን የተባለውን ገፀባህርይ የሚተውነው ሄነሪ ካቪል ይጠቀሳሉ፡፡ የሽልማት ስነስርዓቱ በ100 አገራት የቀጥታ ቴሌቭዥን ስርጭት ሲኖረው ከመሰል የሽልማት ስነስርዓቶች በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ተከታታይ በማግኘት እስከ 2 ቢሊዮን ተመልካች እንደታደመው ተወስቷል፡፡ በላውረስ ሽልማት ከሚጠቀሱ ሌሎቹ አሸናፊዎች መካከል የዓመቱ ምርጥ ቡድን ሽልማትን ያገኘው የዓለም ዋንጫ አሸናፊ የጀርመን ብሄራዊ ቡድን ይጠቀሳል፡፡

የላውሬስ ሽልማት በየዓመቱ በስፖርቱ ጎልቶ ለወጡ ስፖርተኞች የሚሰጥ የክብር ሽልማት ሲሆን ከተለያዩ የዓለም ስፖርቶች የተውጣጡና የላውረስ አካዳሚ አባላት የሆኑ 50 ዝነኛ የዓለማችን ስፖርተኞች ምርጫውን ያከናውናሉ፡፡ በላውረስ አካዳሚ ካሉ ትልልቅ ስፖርተኞች ጀርመናዊው የእግር ኳስ ቄሳር ፍራንዝ ቤከንባወር፤ ታዋቂው የሜዳ ቴኒስ ኮከብ ቦሪስ ቤከር፤፤ ዝነኛው ራሽያዊ የምርኩዝ ዘላይ ሰርጄይ ቡብካና እንግሊዛዊው የእግር ኳስ ባለታሪክ ቦቢ ቻርልተን ይገኙበታል፡፡

የ24 ዓመቷ ገንዘቤ በመካከለኛ ርቀት 1500፤ 3000 እና 5000 ሜትር ውድድሮች በትራክ እና በቤት ውስጥ ውድድሮች 8 የሩጫ ዓመታት አሳልፋለች፡፡ ያስመዘገበቻቸው ሪከርዶች እና የሜዳልያ ውጤቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

- በዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ሻምፒዮና 2 የወርቅ ሜዳልያዎች በ1500 እና በ3000 ሜትር
- በዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና 2 የወርቅ ሜዳልያዎች በወጣቶች ውድድር
- በዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና 1 ወርቅና 1 ብር ሜዳልያ በ5ሺ ሜትር
- በአይኤኤፍ ኮንትኔንታል ካፕ 1 ወርቅ ሜዳልያ


**3 የዓለም ሪከርዶች በቤት ውስጥ አትሌቲክስ**

- 1500 ሜትር 3፡55.17 በካርልሱርሀ ጀርመን በ2014 እኤአ
- 3000 ሜትር 8፡16.6 በስዊድን ስቶክሆልም 2014 እኤአ
- 5000 ሜትር 14፡18.86 በስዊድን ስቶክሆልም 2015 እኤአ

**6 የአፍሪካ አትሌቲክስ ሪከርዶች**

- በ1500ና በ5000 ሜትር ትራክ፤ በ2 ማይል፤ እንዲሁም በቤት ውስጥ አትሌቲክስ በ1500፤ በ3000 እና በ5000 ሜትር ውድድሮች


ፖል ሪየስና ልጆቹ (ኢትዮጵያ) ሊሚትድ
- የፔጆ ብቸኛ ወኪል -
PEUGEOT
2008
አዲሱ ሞዴል ፔጆ 2008!
1200ሲሲ፣ ሁለት የአደጋ ጊዜ የአየር ከረጢት፣ ባለ 16 ኢንች ቸርኬ፣ ሬድዮና የሲዲ ማጫወቻ
የብሉ ቱዝና ፍላሽ ማገናኛዎችን ጨምሮ፣ ሌሎችንም ያካተተ . . .
ስልክ +251 11 155 0233 ፋክስ+251 11 155 1278 ሞባይል +251 91 186 8712


ካቤ CABEY
ኃ.የተ.የግ.ማ. Private Limited Company
BRIDGESTONE
Tel: 011-55-11-138 /Mob. 0911-20-60-44
Fax. 011-46-63-164 /P.o.box. 18192/
e-mail cabey@ethionet.et
BRIDGESTONE
TRUCK TYRE CENTRE